ترجمة معاني القرآن الكريم

የክቡር ቁርኣን መልእክት ትርጉም

በአማርኛ እጅግ ሳይጠብ ወይም ሳይሰፋ
ተመጥኖ የተዘጋጀ

በሸኽ ሰዒድ አህመድ ሙስጠፋ

(30ኛዉ ጁዝእ)

تاليف:
الشيخ سعيد أحمد مصطفى

الأمهرية

የከቡር ቁርአን መልእክት ትርጉም

الترجمة لمعاني القرآن الكريم باللغة الأمهرية

በአማርኛ ቋንቋ እጅግ ሳይጠብ ወይም ሳይሰፋ
ተመጥና የተዘጋጀ በሸይኽ ሰዒድ አሕመድ ሙስጠፋ

30ኛው ጁዝእ

2ኛ ዕትም

የተርጓሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።
جميع الحقوق محفوظة للمترجم
All Rights Reserved

አድራሻ:- ሸህ ሰይድ አህመድ ሙስጠፋ
ምባይል ቁጥር 0507494402
ሳዑዲ ዓረቢያ

በኢትዮጵያ ተወካይ
ሐጂ ቢላል ተማም
ምባይል ቁጥር 09-1166097
ኢትዮጵያ

ح المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد بالمعذر وأم الحمام، ١٤٢٩هـ

فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر

مصطفى، سعيد أحمد

ترجمة معاني العشر الأخير من القرآن الكريم. / سعيد أحمد مصطفى.- الرياض، ١٤٢٩هـ

٩٦ ص ، ١٤ × ٢٠ سم

ردمك : ٨-٨-٩٦٠٣-٩٩٦٠-٩٧٨

(الكتاب باللغة الأمهرية)

١- القرآن - ترجمة　　　أ- العنوان

ديوي ٢٢١,٤　　　١٤٢٩/٣٢٨١

رقم الإيداع : ١٤٢٩/٣٢٨١

ردمك : ٨-٨-٩٦٠٣-٩٩٦٠-٩٧٨

حقوق الطبع للمترجم

ማውጫ

ተራ ቁ.	ርዕስ	ገጽ
1	መግቢያ	1
2	ሱረቱ-ነበእ	4
3	ሱረቱ-ናዚዓት	9
4	ሱረቱ-ዐበሰ	14
5	ሱረቱ-ተክዊር	18
6	ሱረቱል-ኢንፊጣር	21
7	ሱረቱል-ሙጠፊፊን	24
8	ሱረቱል-ኢንሺቃቅ	29
9	ሱረቱል-ቡሩጅ	32
10	ሱረቱ-ጧሪቅ	35
11	ሱረቱል-አዕላ	37
12	ሱረቱል-ጋሽያ	39
13	ሱረቱል-ፈጅር	42
14	ሱረቱል-በለድ	46
15	ሱረቱ-ሽምስ	49
16	ሱረቱ-ለይል	51
17	ሱረቱ-ዱሐ	53
18	ሱረቱ-ሽርሕ	55

19	ሱረቱ-ቲን..	57
20	ሱረቱል-ዐለቅ..	58
21	ሱረቱል-ቀድር..	62
22	ሱረቱል-በይና..	64
23	ሱረቱ-ዘልዘላ...	67
24	ሱረቱል-ዓዲያት......................................	68
25	ሱረቱል-ቃሪዓ..	70
26	ሱረቱ-ተካሡር..	71
27	ሱረቱል-ዓስር..	73
28	ሱረቱል-ሁመዛ.......................................	75
29	ሱረቱል-ፊል..	76
30	ሱረቱ-ቁረይሽ..	78
31	ሱረቱል-ማዑን.......................................	79
32	ሱረቱል-ከውሠር.....................................	80
33	ሱረቱል-ካፊሩን.....................................	81
34	ሱረቱ-ነስር..	82
35	ሱረቱል-መሰድ.......................................	83
36	ሱረቱል-ኢኽላስ......................................	85
37	ሱረቱል-ፈለቅ..	86
38	ሱረቱ-ናስ...	89

መግቢያ

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እጀምራለሁ::)

ቀደም ሲል ያልነበርኩትን ፈጥሮ ላስገኘኝ፣ የአካል ክፍሎቼን አሟልቶ እስካሁን ድረስ በጤንነት ላቆየኝ፣ ከዚህም በላይ ኢስላማዊ እምነትን ሰጥቶ ቁርአንን ላሳወቀኝ፣ እንዲያውም ሐቁን አውቄ ለሌሎችም ማሳወቅ ላስቻለኝ፣ በተለይ በቁርአን ትርጉም እንድሰማራ ያደለኝ ለሆነው ሩህሩህ ጌታ፣ ሰፊ ምስጋና ይገባው ያለመጠን እጅግ በርካታ:: ርህራሄ ሰላሙም የነቢያት መደምደሚያ ላደረጋቸው መሪያችን ለነቢዩሏህ ሙሐመድ ይድረሳቸው፣ እስከ ቤተሰቦቻቸው፣ እንዲሁም ለመላው የእምነት ተከታይ ወዳጆቻቸው!!

ከዚህ በኋላ ለመግለጽ የምወደው ማንኛውም ሰው በአመነበት ዓላማ ተግቶ ከሠራ በዕውነት፣ ሰበቡን አድርሷልና ሳይበቃ አይቀርም ለውጤት አላህ ከሻለት:: እኔም ታዲያ ከህጻንነት እስካሁን ባደረግኩት ቀጣይ ጥረቴ፣ የአላህ መልካም ፈቃድ ሆኖ ለዚህ ውጤት በመብቃቴ፣ ደስታዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው ስለተሳካ ምኞቴ::

ይህም ግዙፍ የአላህ ፀጋ ለወገኖቼ ደርሷቸው፣ በሱ ሐቁን ተመላክተው ኢስላም እንደሚገባቸው ተስፋዬ ነው:: እዚህ ላይ ላሳስብ የምወደው፣ ሥራው እስከዛሬ እከተለው ከነበረው አቀራረብ የተለየ መሆኑን ነው:: ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ የሚፈለገው በጥቂት ቃላት ግልጽ መልዕክትን ማድረስ ነው:: ቁርአን እራሱም የሚከተለው ይህን ስልት ነው:: አንባቢንም በትንታኔ

ከማስልቸት ፍሬ ነገሩን በመጠቆም የአእምሮ ስራ ለመስጠት ስል ነው።

ዋናው ትኩረቴም የሆነው ቁርአንን በመመሪያነት እንደተቀበልነው ሁሉ ተግባራችንን በሙሉ ከሱ ማጣጣም እንዳለብን ማስገንዘብ ላይ ነው። ሆኖም ሀሳቡ ጭፍን እንዳይሆን መልዕክቱን ግልጽ ለማድረግ መሠረታዊ ሀሳቦችን መግለጫና ማብራሪያዎችን በቅንፍ መሃል ጣልቃ እንደማስገባ ነው። እንዲሁም የምዕራፋት መግቢያዎችና ለአንቀጾች መውረድ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በአጭሩም ቢሆን በየጣልቃው መጥቀሴ የማይቀር ነው። ይህም በቁርአን ተርጓሚዎች ዘንድ የተለመደ አሠራር ነው።

ሌላው ደግሞ እዚህ ላይ ላሳስብ የምወደው ቁርአን ምን ጊዜም ለሁሉም ሰዎች የበላይ አስተማሪና መሪ እንጂ የማንንም ሀሳብና ፍልስፍና በመቀበል የሚከተል አይደለምና ይህ ስራዬ በአላህ ስሞችም ሆነ በሌሎች መሰል ነገሮች ቃላትን በማጣመም ከመተርጎም የራቀ ነው።

እንዲያውም በዚህ ፋንታ ከአንቀጾች ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸውን ትክክለኛ ሐዲሶች አግባብ ባለው ቦታ ሁሉ እንደምጠቅሳቸው ነው።

ለዚህም *ሥራ* መሳካት በዋቢነት የተጠቀምኩባቸው ዋነኛ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

አንደኛ፡- ተፍሲር ኢብኑ ከሢር የሸይኽ ኢስማዒል ዒማዱዲን ድርሰት የሆነው እውቁ መጽሐፍ፣

ሁለተኛ፡- ተፍሲሩ ዛዱል-መሲር የሸይኽ ዓብዱረሕማን ዓሊ አቡል-ፈረጅ *ሥራ* ውጤት፣

ሦስተኛ:- ተፍሲሩ ፈትሁል-ቀዲር የሸይኽ ሙሐመድ ዓሊ አሸውካኒ ድርሰት የሆነው፣

አራተኛ:- ተይሲሩል-ከሪሚ-ረሕማን የሸይኽ ዓብዱረሕማን ናስር አሰዕዲ ድርሰት የሆነው፣

አምስተኛ:-ተፍሲሩል-ጀላለይን በሸይኽ ሙሐመድ መሐሊና በሸይኽ ዓብዱረሕማን ሱዩጢ የተሰራው፣

ስድስተኛ:- ተፍሲሩ ተስሂል በሸይኽ ሙሐመድ አሕመድ አቡል-ቃሲም የተዘጋጀው ሲሆን፣

ሰባተኛ:- ሰፍወቱ ተፋሲር በሸይኽ ሙሐመድ ዓሊ ሳቡኒ የተሠራው በተለይ የምዕራፋት መግቢያዎችን የተጠቀምኩት ከእሱ ነው።

ለአንቀጾች መውረድ ሰበብ በሆኑት ጉዳዮች ደግሞ በአመዛኙ የተከተልኩት የሱዩጢና የዋሒዲን መጽሐፍት ነው።

እዚህ ላይ ቸሩን ጌታዬን አጥብቄ የምለምነው ይህን መጽሐፍ ለእኔ የተባረከ ለአንባቢዎቹም ጠቃሚ እንዲያደርገው ለወላጆቼና ለሸይኾቼም በእሱ ሰበብ ታላቅ ምንዳን እንዲለግሳቸው ነው።

ተርጓሚው ሸይኽ ሠዒድ አሕመድ ሙስጠፋ
አል መዲነቱል ሙነወራ 16/8/1428 ዓ.ሂ.

ሱረቱ-ነበእ سورة النبأ

የከባዱ ዜና ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አርባ አንቀፆችን የያዘች አጠር ያለች ምዕራፍ ናት:: እሷም ገና በመግቢያዋ በጥያቄ መልክ አጠንክራ የምታወሳው ከሃዲያኑ የሚጠራጠሩበትን የቂያማ ቀንን ጉዳይ ነው:: በማያያዝም ለዚያ ቀን መምጣት በዋቢነት የምትጠቅሰው ከፍጥረታቱ መካከል ለአላህ ኃይል መገለጫ የሆኑትን ነገሮች ነው:: ያም የቀጠሮ ዕለት ሲደርስ ሰዎች ከመቃብር ወጥተው የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚቀበሉ፣ ከዚያም ለሁለት ተከፍለው ጠማማዎች ወደ ጀሀነም፣ ጥንቁቃኑ ወደ ጀነት መልላካቸው እንደማይቀርና ያኔም ከሃዲው ሰው «ምነው አፈር ሆኜ ብቀር!» እያለ ከንቱ እንደሚመኝ ነው:: ስያሜዋም የመነጨው ከሁለተኛው አንቀጽ ነው::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

عَمَّ يَتَسَآءَلُونَ ﴿١﴾ عَنِ ٱلنَّبَإِ ٱلۡعَظِيمِ ﴿٢﴾ ٱلَّذِي هُمۡ فِيهِ مُخۡتَلِفُونَ ﴿٣﴾

ስለምኑ ነው ለመሆኑ እነርሱ እያወላወሉ በመጠያየቅ ላይ ያሉ? ስለታላቁ ዜና ስለቂያማ ነውን? እነርሱ አሁንም እየተጨቃጨቁ ያሉ?:-

كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ﴿٤﴾ ثُمَّ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ﴿٥﴾

ይልቁንስ የሚሻለው ይህን ነገር ቢተው ነው፤ እምቢ ካሉ ግን የሚያጋጥማቸውን ቆያይተው እንደሚያውቁ ነው:: አሁንም ያለባቸው ይህን ነገር መተው ነው:: አለበለዚያ ሰነባብተው ውጤቱን እንደሚያውቁ ነው::

أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ مِهَٰدٗا ﴿٦﴾ وَٱلۡجِبَالَ أَوۡتَادٗا ﴿٧﴾

ምድርን ለኑሮ አመቺ አድርገን አልደለደልናትምን? ጋራዎችንስ እሷን ረግጠው የሚይዙ ችካሎች አላደረግናቸውምን?

وَخَلَقۡنَٰكُمۡ أَزۡوَٰجٗا ﴿٨﴾ وَجَعَلۡنَا نَوۡمَكُمۡ سُبَاتٗا ﴿٩﴾

እናንተንም በጾታችሁ ወንድና ሴት አድርገን በመፍጠር ባልና ሚስቶች አደረግናችሁ:: እንቅልፍንም ለአካላችሁ ማረፊያ፣ ለድካማችሁ ማጥፊያ አደረግንላችሁ::

وَجَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ لِبَاسٗا ﴿١٠﴾ وَجَعَلۡنَا ٱلنَّهَارَ مَعَاشٗا ﴿١١﴾

ሌሊቱንም ለዕረፍት እንዲመቻችሁ እንደ አልባሳት ሆኖ እንዲሸፍናችሁ፣ ቀኑንም ለኑሯችሁ አመቺ ብርሃናማ አደረግንላችሁ::

وَبَنَيۡنَا فَوۡقَكُمۡ سَبۡعٗا شِدَادٗا ﴿١٢﴾ وَجَعَلۡنَا سِرَاجٗا وَهَّاجٗا ﴿١٣﴾

ከበላያችሁም ሰባት ጠንካሮች ሰማያትን ገነባናቸው:: ከዚያም ደማቁን (የፀሐይ) ብርሃን ፈጥረን መደብናት በላቸው::

وَأَنزَلۡنَا مِنَ ٱلۡمُعۡصِرَٰتِ مَآءٗ ثَجَّاجٗا ﴿١٤﴾ لِّنُخۡرِجَ بِهِۦ حَبّٗا وَنَبَاتٗا ﴿١٥﴾ وَجَنَّٰتٍ أَلۡفَافًا ﴿١٦﴾

ከዚያም ዝናብን ካረገዙት (ዳመናዎች) በእሱ አዝዕርቶችና በቆልቶች የዳበሩ የሆኑንም አትክልቶች ከምድር ልናበቅልላችሁ፣ ተንዠቅዣቂውን ውሃ እንዲወርድ አደረግንላችሁ፤ (ታዲያ ይህን ሁሉ በቀላሉ ማድረግ የቻለው ጌታችሁ እናንተንስ ከሞት ማስነሳት ያቅተው መሰላችሁ? ማለቱ ነው ቢገባቸው::)

إِنَّ يَوۡمَ ٱلۡفَصۡلِ كَانَ مِيقَٰتٗا ﴿١٧﴾

ወሳኙ ፍርድ ቀን እኮ ዝንፍ የማይል ቀጠሮ

እንደተያዘለት ነው:: (ስለዘገየ የሚቀር አይምሰላችሁ ማለቱ ነው::)

يَوْمَ يُنفَخُ فِي ٱلصُّورِ فَتَأْتُونَ أَفْوَاجًا ﴿١٨﴾

እሱም በገሃድ የሚሆነው በቀንዱ በሚነፋና እናንተንም ኑ! ስንላችሁ ከባዱን ጥሪ ስምታችሁ፣ ከቀብሮቻችሁ ቶሎ በመውጣት በቡድን በቡድን እየተግተለተላችሁ በምትመጡበት ቀን ነው::

وَفُتِحَتِ ٱلسَّمَآءُ فَكَانَتْ أَبْوَٰبًا ﴿١٩﴾ وَسُيِّرَتِ ٱلْجِبَالُ فَكَانَتْ سَرَابًا ﴿٢٠﴾

ያኔም ሰማይ በመቀዳደድ ተሸንቋቁራ ክፍትፍት እንዳሉ በሮች እንደምትሆን ነው:: ተራራዎችም ከቦታቸው እንደሚወገዱና ከዚያም ውልብልቢት ሆነው ከዓይን ዕይታ እንደሚሰወሩ ነው በላቸው::

إِنَّ جَهَنَّمَ كَانَتْ مِرْصَادًا ﴿٢١﴾ لِّلطَّٰغِينَ مَـَٔابًا ﴿٢٢﴾ لَّٰبِثِينَ فِيهَآ أَحْقَابًا ﴿٢٣﴾

ጀሀነምም በዚያ ቀን ደንበኞቿን ለመረከብ ተዘጋጅታ አፏን ከፍታ በመጠባበቅ ላይ ናት:: እሷም ለአጉራ ዘለሎቹ የመጨረሻ መመለሻና በእሷ ውስጥ ዘመናትን እያስቆጠሩ የሚኖሩባት አገር ናት::

لَّا يَذُوقُونَ فِيهَا بَرْدًا وَلَا شَرَابًا ﴿٢٤﴾ إِلَّا حَمِيمًا وَغَسَّاقًا ﴿٢٥﴾ جَزَآءً وِفَاقًا ﴿٢٦﴾

በእሷም ውስጥ ሲኖሩ እሳቸው ቀዝቃዛ አየርንና ጥም ቆራጭ መጠጥንም ጭራሽ የማይቀምሱ ናቸው:: ሆኖም የፈላ ውሃና የሰዎች እዥና መግል ይሆናል የሚሰጣቸው፣ እሱም ለመጥፎ ስራቸው ተስማሚ ዋጋ ነውላቸው::

إِنَّهُمْ كَانُوا۟ لَا يَرْجُونَ حِسَابًا ﴿٢٧﴾ وَكَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا كِذَّابًا ﴿٢٨﴾

ምክንያቱም ሳሉ በህይወታቸው፣ የማይነሱ መስሏቸው ሂሳብ አይፈሩም ነበርና ነው በላቸው:: እንዲያውም ያ!

ሳይበቃቸው አንቀጾቻችንን ሁሉ ማስተባበልን ያስተባበሉ ግፈኞች ናቸው::

وَكُلَّ شَيْءٍ أَحْصَيْنَاهُ كِتَابًا ﴿٢٩﴾ فَذُوقُوا فَلَن نَّزِيدَكُمْ إِلَّا عَذَابًا ﴿٣٠﴾

የሠራችሁትን ሁሉ በመዝገብ አጠናቀን አስፍረንላችኋል:: በሉ እንካችሁ! ቅመሱ! ለእናንተ ቅጣት እንጂ ምን እንጨምርላችሁ ይመስላችኋል? ይባላሉ::

إِنَّ لِلْمُتَّقِينَ مَفَازًا ﴿٣١﴾ حَدَائِقَ وَأَعْنَابًا ﴿٣٢﴾ وَكَوَاعِبَ أَتْرَابًا ﴿٣٣﴾ وَكَأْسًا دِهَاقًا ﴿٣٤﴾

لَّا يَسْمَعُونَ فِيهَا لَغْوًا وَلَا كِذَّابًا ﴿٣٥﴾ جَزَاءً مِّن رَّبِّكَ عَطَاءً حِسَابًا ﴿٣٦﴾

ለእነዚያ ጥንቁቅ ለሆኑት አማኞችማ ጌታቸውን በመፍራታቸው፣ ከዚያ ቅጣት ነፃ ሆነው በደስታ የሚዝናኑባቸው ልዩ ቦታዎች አሏቸው:: እነዚያም ቦታዎች የአትክልት ዛፎች ሁሉ የተከማቹባቸው፣ በተለይ ወይኖች የበዙባቸው የፍስሃ አገሮች ናቸው:: በዚያም ውስጥ የሚያዝናኗቸው ጡተ-ጎቻማ በዕድሜያቸው እቻ የሆኑ ወጣት ሚስቶችም አሏቸው:: ቢጠጡ የማይቋረጡ ሁልጊዜ የሚሞሉ የጀነት ጠጅ ዋንጫዎችም በየፊቶቻቸው አሉ:: ሆኖም በእሷ ውስጥ አላስፈለጊ ቃልና በሀሰት መወንጀልንም ጭራሽ የማይሰሙ ናቸው:: ይህም ለእነርሱ ከጌታህ ምንዳ ሲሆንላቸው በቂ እንዲያውም ላቅ ያለ ስጦታ ነው ሲነፃፀር ከሥራቸው::

رَّبِّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا الرَّحْمَٰنِ

እጅግ ሩህሩህ የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያሉ ፍጥረታት ሁሉ፣ ባለቤት ከሆነው ጌታ ነውኮ የሚቸራቸው ዕድሉ፤

لَا يَمۡلِكُونَ مِنۡهُ خِطَابٗا ﴿٣٧﴾ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلرُّوحُ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ صَفّٗاۖ لَّا يَتَكَلَّمُونَ

إِلَّا مَنۡ أَذِنَ لَهُ ٱلرَّحۡمَٰنُ وَقَالَ صَوَابٗا ﴿٣٨﴾

እርሱኮ ኃያልነቱ ግርማው ስለሚከብዳቸው ካልጋበዛቸው በስተቀር አስቀድመው ሊያናግሩት ጭራሽ አይችሉም በላቸው:: በቂያማም ቀን ጂብሪልና መላዕክት ሰልፍ በሚቆሙ ጊዜ አል-ራሕማን ፈቃድ አድርጎለት፣ እርሱም በህይወት ላይ ሳለ ተናግሮ እንደሆን ነው እውነት፣ እንጂ ከዚያ ውጭ ያሉማ አይናገሩም በዚያ ወቅት:: (እዚህ ላይ እውነት የሚለው የተውሒድ መርሆ የሆነውን ቃል:- ላኢላሀ ኢለ-ሏህን ነው::) አለዚያማ ጌታ እንዲናገሩ ካልጋበዛቸው፣ ምንም ያህል ቢልቅ እንኳን ደረጃቸው፣ ብድግ ብለው ሊናገሩ ወይ «እገሌን ማረው!» ሊሉ አይደሉምኮ የሚችሉ ማለቱ ነው:: (እዚህ ላይ ብዙ ሰዎች ይህን በመዘንጋታቸው፣ ትልቅ የሚሉትን ሁሉ «እባክህ እርዳን!» እያሉ፣ ደጅ ይጠናሉ፤ እርሱ ቀጥታ የሚሸመግል መስሏቸው::)

ذَٰلِكَ ٱلۡيَوۡمُ ٱلۡحَقُّۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ مَـَٔابًا ﴿٣٩﴾

ያ! እኮ ከባድ ቀን መምጣቱ የማያጠራጥር የተረጋገጠ ቀን ነው፤ የፈለገ ሰው እህን ጊዜ ወደ ጌታው መመለሻውን መስመር መያዝ እንዳለበት ነው::

إِنَّآ أَنذَرۡنَٰكُمۡ عَذَابٗا قَرِيبٗا يَوۡمَ يَنظُرُ ٱلۡمَرۡءُ مَا قَدَّمَتۡ يَدَاهُ وَيَقُولُ ٱلۡكَافِرُ

يَٰلَيۡتَنِي كُنتُ تُرَٰبَۢا ﴿٤٠﴾

እኛኮ በእርግጥ (እናንተ ብትሆኑ ኖሮ የሚገባችሁ) ቅርብ የሆነን ቅጣት ነው የምናስጠነቅቃችሁ:: (ይህም ዛቻ ገቢራዊ የሚሆነው) ሰው ሁሉ እጆቹ ያስቀደሙትን በሚያይበት ዕለት ነው:: ከሃዲውም ሰው (የሚያየው ቅጣት ሲዘገንነው) ምነው አፈር ሆኜ ብቀር! እያለ ከንቱ ምኞቱን የሚገልጸው በዚያ ቀን ነው::

ሱረቱ-ናዚዓት سورة النازعات

የነፍስ መዛዦች ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አርባ ስድስት አንቀጾች ያሏት አጠር ያለች ምዕራፍ ናት:: እሷም እንደሌሎቹ ቢጤዎቿ የምታተኩረው በዕምነት ነክ ነጥቦች ላይ ነው:: በተለይም ከሞት በኋላ ተነስቶ በሥራ መመንዳት አለ በሚለው ቁም ነገር ላይ ነው:: ከሃዲያኑ ዛሬ ስለሱ ሲነገራቸው ምንም ባይዋጥላቸው፣ ነገ በገሃድ ሲመጣላቸው፣ ልቦቻቸው እየተርበተበቱ አይኖቻቸው ሲርገበገቡባቸው ይሆናል የሚገባቸው ትላለች:: የመካ ጣዖታዊያን እጅግ ወብርተው በነብዩ ላይ ድንበር በማለፋቸው፣ በአጭሩም ቢሆን ከወትሮ ቢጤዎቻቸው፣ የነፈርዖንን ታሪክ በማስገንዘብ ነው የምትገስፃቸው:: ስለዚህ እነርሱም ከቀጠሉ በድርቅናቸው እንደሚሰባብራቸው ጠቆማቸው:: ለዚህም ማረጋገጫ እንኳን እነርሱን መዳኘት ሰማይ ምድርን መገንባት እንዳላቃተው ነገራቸው:: ስያሜዋም ሊሆን የቻለው የመጀመሪያው ቃል ነው::

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَالنَّازِعَاتِ غَرْقًا ﴿١﴾ وَالنَّاشِطَاتِ نَشْطًا ﴿٢﴾ وَالسَّابِحَاتِ سَبْحًا ﴿٣﴾

فَالسَّابِقَاتِ سَبْقًا ﴿٤﴾ فَالْمُدَبِّرَاتِ أَمْرًا ﴿٥﴾

የከሃዲያንን ነፍሶች በሃይል መንጭቀው በሚያወጡት የመላዕክት ቡድኖች፣ የአማኞችንም ነፍሶች ቀስ አድርገው በሚመዙት መላዕክት፣ በህዋም ላይ መዋኘ ትን በሚዋኙት ተወካዮች፣ ትዕዛዛችንን ሊከውኑ በሚሽቀዳደሙትም አገልጋዮች፣ በዓለም ዙሪያ

የተለያዩን ጉዳዮች በሚያስተናግዱትም የመላዕክት ተጠሪዎች እምልላችኋለሁ!!

يَوْمَ تَرْجُفُ الرَّاجِفَةُ ﴿٦﴾ تَتْبَعُهَا الرَّادِفَةُ ﴿٧﴾ قُلُوبٌ يَوْمَئِذٍ وَاجِفَةٌ ﴿٨﴾

أَبْصَارُهَا خَاشِعَةٌ ﴿٩﴾

በመጀመሪያዋ ንፋት ዓለም ስትርገፈገፍ እየተናጠች፣ ሁለተኛዋም ተፈናጣጯ ንፋት ብዙ ሳትቆይ እሷኑ ትከተላለች:: ልቦች በዚያ ቀን ደንግጠው ፈርተው በጣም የሚዘሉ ናቸው:: ዓይኖቻቸውም በዚያ ዕለት ፈሪ ተጨናቂ ናቸው (ምንም አሁን ቢያሾፉባት የማትደርስ መስላቸው)::

يَقُولُونَ أَإِنَّا لَمَرْدُودُونَ فِي الْحَافِرَةِ ﴿١٠﴾ أَإِذَا كُنَّا عِظَامًا نَّخِرَةً ﴿١١﴾ قَالُوا

تِلْكَ إِذًا كَرَّةٌ خَاسِرَةٌ ﴿١٢﴾

(አሁንማ ስለእሷ ሲነገራቸው በመሳለቅ እርስ በርሳቸው) እውን እኛ ከሞት ድነን ወደ መጀመሪያዋ ሁኔታ ተመላሾች ነን? እኛ ብስባሽ አጽሞች ስንሆን እንደገና ታዳሾች ነን? ይህችማ ብትሆን ኪሳራ አዘል የሆነች መመለስ ናት የሚሉ ናቸው:: ያኔ ግን እኛ ደግሞ የምንላቸው:-

فَإِنَّمَا هِيَ زَجْرَةٌ وَاحِدَةٌ ﴿١٣﴾ فَإِذَا هُم بِالسَّاهِرَةِ ﴿١٤﴾

እምን እንዴታ! ያውም ለዚያ የምታበቃቸው፣ አንዲት ጩኸት ብቻ እኮ ናት! ሌላም አያስፈልጋቸው:: ያኔ ወዲያው እሳቸው እንቅልፍ አልባ በሆነችው ነጭ ብር በምትመስለው አውላላ ሜዳ ላይ ናቸው::

هَلْ أَتَاكَ حَدِيثُ مُوسَىٰ ﴿١٥﴾ إِذْ نَادَاهُ رَبُّهُ بِالْوَادِ الْمُقَدَّسِ طُوًى ﴿١٦﴾ اذْهَبْ إِلَىٰ

فِرْعَوْنَ إِنَّهُ طَغَىٰ ﴿١٧﴾

ቀጥሎ ደግሞ አላህ ለነብዩ ታሪካዊ እውቀትን እየገበዩ እንዲበረቱ በትግላቸው፣ የነብዩ ሙሳ ወሬ ደረሰህን? አላቸው፤ በጥያቄ መልክ ጉጉት ሲያሳድርባቸው፤ ጌታው በሲና ጎራ ሥር በቅዱስ ጡዋ ሸለቆ በድንገት በጠራው ጊዜ የሆነውን አውሳላቸው:: ወደ ፈርዖን ሂድና እሱ ወሰን አልፏልና፣ በኃይል ሳይሆን ለዘብ ባለ አቀራረብ ጠጋ በልና:-

فَقُلْ هَل لَّكَ إِلَىٰٓ أَن تَزَكَّىٰ ﴿١٨﴾ وَأَهْدِيَكَ إِلَىٰ رَبِّكَ فَتَخْشَىٰ ﴿١٩﴾

እባክህ አንተ ሰውዬ! የምትሻ ከሆንክ መንፈሳዊ ንፅህና፣ ወደ ጌታህ ፈቃድ ልምራህ ምናልባት እሱን ብታውቀው ትፈራው ይሆናልና፤ ብለህ ጠይቀው::

فَأَرَىٰهُ ٱلْءَايَةَ ٱلْكُبْرَىٰ ﴿٢٠﴾ فَكَذَّبَ وَعَصَىٰ ﴿٢١﴾ ثُمَّ أَدْبَرَ يَسْعَىٰ ﴿٢٢﴾

فَحَشَرَ فَنَادَىٰ ﴿٢٣﴾ فَقَالَ أَنَا۠ رَبُّكُمُ ٱلْأَعْلَىٰ ﴿٢٤﴾

ሆኖም ሰውየው አሁን አንተ ለምትለው ምንድን ማስረጃ አለህ? ሲለው ታላቋን ተዓምራዊ ዘንግ እባብ ስትሆን አሳየው፤ ቢሆንም አስተባበለው ይባስ አመፀበት እንጂ አልሆነም የሚቀበለው:: ከዚያም ከሐቁ በመሸሽ ወደ ኋላ በመቻኮል አሸገሸገ ትዕቢት እየኮለኮለው፣ ከዚያም ህዝቦቹን ሰብስቦ ቆመና ፊት ለፊታቸው እኔኮ ነኝ! ከሁሉ በላይ ወሳኝ ጠቅላይ ጌታችሁ! አላቸው::

فَأَخَذَهُ ٱللَّهُ نَكَالَ ٱلْءَاخِرَةِ وَٱلْأُولَىٰٓ ﴿٢٥﴾

(በዚህ መልክ ፈርዖን አለቅጥ መጠን አልፎ ሲያቅነዘንዘው) አላህም ወዲያው በመጨረሻዋና በመጀመሪያዋም ቃሉ ያየህ ተቀጣ! እንዲሉ እንቅ ፍጥርቅ አድርጎ ያዘው::(ማለትም ከዚያ ቀደም ሲል «ያለኔኮ ጌታ አላውቅላችሁም» ማለቱ ሳያንሳቸው፤ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ ይህን ሲጨምርላቸው፣ እነርሱም ሳይቃወሙ ለዚህ ባለጌ መሪያቸው ድጋፍን በመስጠታቸው፣ ተቀየመና ጌታቸው ሁሉንም እንደ

አሸዋ አፍሶ ባሕር ውስጥ ጨመራቸው፤ ለሌሎች ህዝቦች መቀጣጫ እንዲሆን ታሪካቸው ማለቱ ነው::)

إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَعِبْرَةً لِّمَن يَخْشَىٰٓ ﴿٢٦﴾

በዚህም ድርጊት ጌታውን በዕውነት ለሚፈራ ሰው ሁሉ፣ ትልቅ ትምህርት ነው ያለው ልብ ያላቸው ልብ ይበሉ! ማለቱ ነው::

ءَأَنتُمْ أَشَدُّ خَلْقًا أَمِ ٱلسَّمَآءُ ۚ بَنَىٰهَا ﴿٢٧﴾ رَفَعَ سَمْكَهَا فَسَوَّىٰهَا ﴿٢٨﴾

(ከዚያም ተረኞቹን ጥጋበኞች ሲገስፃቸው:- ለመሆኑ እናንተ ናችሁ በአፈጣጠር የምትበረቱት ወይስ ሰማይ ናት? አላቸው:: እሷንኮ አላህ ነው በህዋ ላይ የገነባት፤ ድንዳኔዋንም አወፍሮ ዳር እስከዳር ያስተካከላት (ያለምንም ዕረዳት::)

وَأَغْطَشَ لَيْلَهَا وَأَخْرَجَ ضُحَىٰهَا ﴿٢٩﴾ وَٱلْأَرْضَ بَعْدَ ذَٰلِكَ دَحَىٰهَآ ﴿٣٠﴾ أَخْرَجَ

مِنْهَا مَآءَهَا وَمَرْعَىٰهَا ﴿٣١﴾ وَٱلْجِبَالَ أَرْسَىٰهَا ﴿٣٢﴾ مَتَٰعًا لَّكُمْ وَلِأَنْعَٰمِكُمْ ﴿٣٣﴾

ሌሊቷንም ድቅድቅ ጨለማ ያደረጋት፣ በቀኗም ደማቋን ብርሃን (ፀሐይን) ያወጣባት፣ ከዚያም በኋላ ምድርን ደለደላት፤ አስተካከላት፤ ከእሷም ውሃን አፈለቀባት፤ ግጦሽንም አበቀለባት፤ ጎራዎችንም ረግጠው እንዲይዟት ደረደረባት:: ይህን ሁሉኮ ያደረገው ለእናንተና ለእንስሳዎቻችሁ መጠቀሚያ እንድትሆን ብሎ ነው::

فَإِذَا جَآءَتِ ٱلطَّآمَّةُ ٱلْكُبْرَىٰ ﴿٣٤﴾ يَوْمَ يَتَذَكَّرُ ٱلْإِنسَٰنُ مَا سَعَىٰ ﴿٣٥﴾ وَبُرِّزَتِ

ٱلْجَحِيمُ لِمَن يَرَىٰ ﴿٣٦﴾

ከዚያም ነገ በገሃድ ስትመጣ አንጋፋይቱ የመከራዎች ሁሉ አውራ፣ ያኔ ነው ትዝ የሚለው ሰው የሠራው ሁሉ ሥራ:: ሲያልም ያኔ ትገለጣለች፣ ለሚያያት ሁሉ እየጋመች፤ ስትጎደራ::

فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلْجَحِيمَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٣٩﴾

ያማ! ጌታውን በመካድ ወሰን የተላለፈና ቅርቢቷን ህይወት አብልጦ የመረጠው፣ ሲያል ናትኮ በእውነት የእርሱ መኖሪያው (እስከወዲያው የምታርመጠምጠው::)

وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفْسَ عَنِ ٱلْهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلْجَنَّةَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ ﴿٤١﴾

ያ! ደግሞ ጌታው ፊት ለምርመራ መቆሙን ፈርቶ ነፍሱን ከመጥፎ ዝንባሌዋ ያቀበው፣ ጀነት ናት በእርግጥ የእርሱ መኖሪያ የምትሆነው::

يَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلسَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَىٰهَا ﴿٤٢﴾ فِيمَ أَنتَ مِن ذِكْرَىٰهَآ ﴿٤٣﴾ إِلَىٰ رَبِّكَ مُنتَهَىٰهَآ ﴿٤٤﴾

(ታዲያ ከሃዲያኑ ጅልነታቸው) ሰዓቷ መቼ እንደምትደርስ ይጠይቁሃል (ለመሳለቅ ቀላል ነገር መስላቸው):: አንተ ስለእሷ መከሰቻ ዕለት ምን ዕውቀት አለህና ነው የምታወሳላቸው? የእሷኮ ሚስጥር መጨረሻ፣ ጌታህ ዘንድ ብቻ ነው (ለማንም የለውም ድርሻ::)

إِنَّمَآ أَنتَ مُنذِرُ مَن يَخْشَىٰهَا ﴿٤٥﴾ كَأَنَّهُمْ يَوْمَ يَرَوْنَهَا لَمْ يَلْبَثُوٓا۟ إِلَّا عَشِيَّةً أَوْ ضُحَىٰهَا ﴿٤٦﴾

አንተኮ ላይ የሚኖረው:- ቀጠሮ መወሰን ሳይሆን እሷን ለሚፈራው ሰው አስጠንቃቂ መሆን ብቻ ነው:: እሷም ደርሳ በሚያዩዋት ጊዜ የሚሰማቸው፣ የአንዲት ምሽት ወይም የረፋዷን ሰዓት ያህል እንጂ እንዳልቆዩ ነው ባለፈችው ህይወታቸው::

ሱረቱ-ዐበሰ سورة عبس

ዐበሰ በመባል የታወቀችው ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አርባ ሁለት አንቀጾች ያሏት አጠር ያለች ምዕራፍ ናት:: እሷም እንደ መካዊነቷ ዕምነት ነክ ነጥቦችን ትዳስሳለች:: የአላህን ኃይልና ጥበብ ብቸኛ አምላክነቱንም በማስረጃ ትገልጻለች:: ዐበሰ እንደሚታወቀው ዓብደላህ ኢብኑ ኡሚ መክቱም የተባሉት ሰሓብይ ከነብዩ ዘንድ ሊማሩ ፈልገው በመጡ ጊዜ ያጋጠማቸውን ነገር አበክራ ትጠቅሳለች:: ጉዳዩንም በማስመልከት መመሪያን ታስቀምጣለች:: ቀጥላ ደግሞ አላህ ለሰዎች ባለ ብዙ ውለታ ሆኖ ሳለ፣ ከሃዲው የሰው ልጅ ግን እርሱን የማያመሰግን ወስላታ በመሆኑ መረገሙን ትገልጻለች:: በማገባደጃው ደግሞ ስለትንሳኤ በማስገንዘብ የአሳሯን ክብደት ለመግለጽ ሰው ከሚወደው ወንድሙ፣ ከእናት ከአባቱ፣ ከልጆቹም፣ ከባለቤቱ እንደሚሸሽ ነው ትላለች:: (ምክንያቱም እነዚህን ሰዎች ቢገናኛቸው፣ ችግር ይጨምሩብኛል ብሎ ስለሚፈራቸው::)

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ﴿١﴾ أَن جَآءَهُ ٱلْأَعْمَىٰ ﴿٢﴾

(ዐይነ-ሥውሩ ሰውዬ ባልሆነው ሰዓት ስለመጣበት) እርሱ ፊቱን ጨፍገግ አድርጎ ዘወር አለ:: በማለት (ለነብዩ ጌታቸው እንዳይደነግጡበት የራሳቸውን ሥራ የሌላ በማስመሰል ወቀሳውን ለዘብ አድርጎ በስልት ነገራቸው::

ይህም የሆነው አንድ ቀን የመካ ባላባቶች ከነብዩ ዘንድ ተሰባስበው ሲመጡላቸው፣ እርሳቸውም ስለኢስላም ሊያስረዷቸው ቁጭ እንዳሉ አብረዋቸው፣ ዓብደላህ ኢብኑ ኡሚ መክቱም የተሰኘው ዐይነ-ሥውር አማኝ ተከታያቸው፣ ሊማር ፈልጎ ከእርሳቸው፣ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጌታ ከቸረዎት ዕውቀት ያካፍሉኝ!» እያለ ሲመጣባቸው፣ እንግዶቹ ደግሞ «እኛን ትቶ ይህን ደካማ ያናግራል!» ብለው እንዳይሄዱባቸው በመፍራታቸው፣ በጉዳዩ ተጨንቆ ስሜታቸው፣ ፊታቸውን ኮስተር አድርገው ዘወር በማለታቸው፤ ወዲያው ጌታ ይህችን ምዕራፍ በማውረድ ተገቢውን መመሪያ ነገራቸው::)

وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ﴿٣﴾ أَوْ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكْرَىٰٓ ﴿٤﴾

ለመሆኑ ይህ ዕውቀት ሽቶ የመጣው ሰው በምትሰጠው ምክር ሊፀዳ ወይም ስትገስፀው ተግሳጿ ትጠቅመው እንደሆነ ምን አሳወቀህ? አላቸው::

أَمَّا مَنِ ٱسْتَغْنَىٰ ﴿٥﴾ فَأَنتَ لَهُۥ تَصَدَّىٰ ﴿٦﴾ وَمَا عَلَيْكَ أَلَّا يَزَّكَّىٰ ﴿٧﴾

ያማ! በሥልጣን በሀብቱ፣ እየተኩራራ የተብቃቃውን ከዕምነቱ፣ አንተ ቀረብ ጠጋ አልከው (ላይቀበልህ በክንቱ):: ለመሆኑ አንተ ምንድን ነው ያለብህ ዕዳ ይህ ጥጋበኛ ከጭቅቅቱ ባይፀዳ? እገፋበታለሁ ካለ (በክህደት በማጋራቱ?!!)

وَأَمَّا مَن جَآءَكَ يَسْعَىٰ ﴿٨﴾ وَهُوَ يَخْشَىٰ ﴿٩﴾ فَأَنتَ عَنْهُ تَلَهَّىٰ ﴿١٠﴾

ያማ! አላህን እየፈራ ወደ አንተ ሊማር የመጣው፣ አንተ ችላ ብለህው አረፍክ በመንፈግ ከትምህርት ዕጣው::

كَلَّآ إِنَّهَا تَذْكِرَةٌ ﴿١١﴾ فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ﴿١٢﴾

በል ከእንግዲህ እንደዚህ አይለመድህ! ይህች በእርግጥ ጠቃሚ ማስታወሻ ናት:: ስለዚህ የሚሻ ሰው ይገሰፅባት::

فِي صُحُفٍ مُّكَرَّمَةٍ ﴿١٣﴾ مَّرْفُوعَةٍ مُّطَهَّرَةٍۭ ﴿١٤﴾ بِأَيْدِي سَفَرَةٍ ﴿١٥﴾ كِرَامٍۭ بَرَرَةٍ ﴿١٦﴾

ይህችኮ ተግሳፅ በተከበረው መዝገባችን ውስጥ የሰፈረች ናት:: ደረጃዋም እጅግ የላቀ እንከን የሌላት ንፁህ ናት:: በክቡራን ጥንቁቃን ባለሟሎች እጅ ከአላህ ወደ ነብዩ የተላከች ናት:: በማለት ጥበበኛው ጌታቸው የተግሳፂን ደረጃ ገለጸላቸው::

قُتِلَ ٱلْإِنسَٰنُ مَآ أَكْفَرَهُۥ ﴿١٧﴾ مِنْ أَىِّ شَىْءٍ خَلَقَهُۥ ﴿١٨﴾ مِن نُّطْفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ ﴿١٩﴾

ثُمَّ ٱلسَّبِيلَ يَسَّرَهُۥ ﴿٢٠﴾ ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقْبَرَهُۥ ﴿٢١﴾ ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ ﴿٢٢﴾ كَلَّا لَمَّا

يَقْضِ مَآ أَمَرَهُۥ ﴿٢٣﴾

ያኮ! ከሃዲ የሆነው ሰው፣ ተረገመ ከአላህ ፀጋ ተባረረ ርህራሄ እንዳይደርሰው:: ለመሆኑ እርሱን ምንድን ነው እንዲህ የከፋ ጭቡ ከሃዲ ያደረገው?! መጀመሪያስ ጌታው እርሱን የፈጠረው ከምንድን ነው?! ከደካማዋ ጠብታ ውሃ እኮ ነው ፈጥሮ ያስገኘው:: ከዚያም አካሉን መጥኖ አቀናበረው:: ብሎም መንገዱን ገራና መውጣት አስቻለው:: ከዚያም ዕድሜው ሲጠናቀቅ ሙት አደረገና አስቀበረው:: ከዚያም እርሱ ሲሻ ደግሞ ቀስቅሶ እንደሚያስነሳው ነው:: ይልቁንስ የሚሻለው ይህን ትዕቢቱን ቢተው ነው:: ሆኖም እርሱ እስካሁን ድረስ ፈጣሪው ያዘዘውን ያልፈፀመ ልግመኛ ነው::

فَلْيَنظُرِ ٱلْإِنسَٰنُ إِلَىٰ طَعَامِهِۦٓ ﴿٢٤﴾ أَنَّا صَبَبْنَا ٱلْمَآءَ صَبًّا ﴿٢٥﴾ ثُمَّ شَقَقْنَا ٱلْأَرْضَ

شَقًّا ﴿٢٦﴾ فَأَنۢبَتْنَا فِيهَا حَبًّا ﴿٢٧﴾ وَعِنَبًا وَقَضْبًا ﴿٢٨﴾ وَزَيْتُونًا وَنَخْلًا ﴿٢٩﴾ وَحَدَآئِقَ

غُلْبًا ﴿٣٠﴾ وَفَٰكِهَةً وَأَبًّا ﴿٣١﴾ مَّتَٰعًا لَّكُمْ وَلِأَنْعَٰمِكُمْ ﴿٣٢﴾

ደግሞ ይህ ከሃዲ ሰው፣ እስኪ ምግቡን ይመልከተው የሚመጣለት ከየት ነው? እኛ እኮ ነን በዕውነቱ ውሃ

አርከፍክፈን፣ ምድርን መቅደድን ቀደን፣ ከእሷ አዝዕርቶችን ወይንና ፍራፍሬንም የምናበቅለው:: በተጨማሪም ዘይቱንን እና የተምርን ዛፎች በአጠቃላይም የዳበሩን አትክልቶች በዚያም ላይ ደግሞ እሸቶችና መኖዎች ያስገኘነው፣ ለእናንተና ለከብቶቻችሁ መጠቀሚያ እንዲሆኑ ነው (ታዲያ ለዚህ ሁሉ ፀጋ እናንተ የምትከፍሉት ዋጋ ክህደት መሆኑ ተገቢ ነው?! እነዚህን ሁሉ ማብቀል የቻለውስ ጌታ እናንተን ከቀብር አድኖ ማውጣቱ የሚያቅተው ነው?

فَإِذَا جَآءَتِ ٱلصَّآخَّةُ ﴿٣٣﴾ يَوْمَ يَفِرُّ ٱلْمَرْءُ مِنْ أَخِيهِ ﴿٣٤﴾ وَأُمِّهِۦ وَأَبِيهِ ﴿٣٥﴾

وَصَٰحِبَتِهِۦ وَبَنِيهِ ﴿٣٦﴾ لِكُلِّ ٱمْرِئٍ مِّنْهُمْ يَوْمَئِذٍ شَأْنٌ يُغْنِيهِ ﴿٣٧﴾

በሉ ይህን ካልሰማችሁ አደንቋሪዋ ጩኸት ስትመጣላችሁ ውጤቱን ታገኛላችሁ:: በዚያ ቀን እኮ የሰው ልጅ ከወንድሙና ከእናት ከአባቱ፣ ከሚወዳትም ባለቤቱ፣ ከልጆቹም እንኳ ሳይቀር እንደሚሸሸ ነው ስለሚከፋ ስጋቱ:: በዚያ ዕለት እኮ ለሁሉም ሰው ሌላውን ሁሉ የሚያስረሳው በቂ አስጨናቂ የሆነ ጉዳይ ነው ያለው በላቸው::

وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ مُّسْفِرَةٌ ﴿٣٨﴾ ضَاحِكَةٌ مُّسْتَبْشِرَةٌ ﴿٣٩﴾

በዚያ ቀን እኮ ዕድለኞቹ ፊቶች በደስታ ፈክተው በውጤታቸው ረክተው የሚስቁ ደስተኞች ናቸው::

وَوُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ عَلَيْهَا غَبَرَةٌ ﴿٤٠﴾ تَرْهَقُهَا قَتَرَةٌ ﴿٤١﴾ أُولَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْكَفَرَةُ ٱلْفَجَرَةُ ﴿٤٢﴾

ሌሎቹ ፊቶች ደግሞ በዚያ ቀን ገፅታቸው አቧራ የለበሱ ፅልመት የሰፈነባቸው ጎስቋሎች ናቸው:: እነሱኮ ሳሉ በህይወታቸው፣ በአቋማቸው ከሃዲያን በተግባራቸው እርኩሳን የሆኑት ናቸው::

ሱረቱ-ተክዊር سورة التكوير

የፀሐይ መጠቅለል ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሃያ ዘጠኝ አንቀፆችን የያዘች አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም በሁለት ቁም ነገሮች ላይ ታተኩራለች:: እነሱም ብትል ምን ምን ናቸው? የትንሳኤ ቀንና የነቢዩ ተልዕኮ ናቸው::

አተክዊር ስለቂያማ ክስተትና ስለምታስከትላቸው በርካታ ከባድ ችግሮች በመደዳው ታወሳለች:: ቀጥላ ደግሞ የነብዩን ተልዕኮና ያመጡትን ብሩህ መመሪያ የህዝቦቻቸውም አቋም ምን ይመስል እንደነበር በሚገባ ትገልጻለች::

በማያያዝም ከሃዲያን እንደሚሉት ቁርአን የሰይጣን ቃል ሳይሆን ከወደ አላህ ለዓለማት የተላከ ታላቅ ተግሳፅ መሆኑን ታስረዳናለች:: ስሟም የተወሰደው ከመጀመሪያው አንቀጽ ነው::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

إِذَا ٱلشَّمۡسُ كُوِّرَتۡ ﴿١﴾

ፀሐይ ብርሃኗ ከስሞ (እንደ አሮጌ ኳስ ስትወድቅ ዋጋ ቢስ ሆና)፤

وَإِذَا ٱلنُّجُومُ ٱنكَدَرَتۡ ﴿٢﴾

ከዋክብትም (እንደ ዛፍ ቅጠል በመርገፍ) በአየር ላይ ተበታትነው ሲቀሩ መና፤

وَإِذَا ٱلۡجِبَالُ سُيِّرَتۡ ﴿٣﴾

ተራራዎችም (ካሉበት በመንቃቀል ወዲያው አፈር ዱቄት ሆነው) ሲኼትኑ (እንደ ደመና)፤

وَإِذَا ٱلْعِشَارُ عُطِّلَتْ ﴿٤﴾

እርጉዞቹ ግመሎችም (ፈቃጅ ባለቤት በማጣት) ወልደው ሲጥሉ (በወና)፤

وَإِذَا ٱلْوُحُوشُ حُشِرَتْ ﴿٥﴾

የዱር እንስሳትም ሁሉ (ተደናግጠው) ሲከማቹ (መፈራራቱ ይቀርና)፤

وَإِذَا ٱلْبِحَارُ سُجِّرَتْ ﴿٦﴾

ባሕሮቹም በእሳት ሲጋዩ (ልክ እንደ ቤንዚን ይሆኑና) ወይም በአንድ ሲዋሃዱ (ገደቦች ይወገዱና)፤

وَإِذَا ٱلنُّفُوسُ زُوِّجَتْ ﴿٧﴾

ነፍሶችም ተገናኝተው ሲጣመሩ (መጥፎው ከመጥፎ ደህናው ከደህና)፤

وَإِذَا ٱلْمَوْءُۥدَةُ سُئِلَتْ ﴿٨﴾ بِأَىِّ ذَنۢبٍ قُتِلَتْ ﴿٩﴾

ከነህይወቷ የተቀበረችውም ልጅ (በደሏ ለፍትህ ቀርቦ) ለምን እንደተገደለች ስትጠየቅ (ቀባሪዋ ፍርዱን ሊቀበል ጌታ ፊት ይቀርብና)፤

وَإِذَا ٱلصُّحُفُ نُشِرَتْ ﴿١٠﴾

የሥራ መዛግብቶችም በይፋ ሲከፈቱ (ገሀድ ሊወጣ ድብቁ የሰው ገበና)፤

وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ كُشِطَتْ ﴿١١﴾

ሰማይም ደግሞ ከሀዋ ላይ ስትገሸለጥ (ተጠቅልላ እንደ ብራና)፤

وَإِذَا ٱلْجَحِيمُ سُعِّرَتْ ﴿١٢﴾

ሲያልም ነዳ ስትግም (ከሃዲያን ደንበኞቿን በአሻጋሪዋ ታይና)፤

وَإِذَا ٱلْجَنَّةُ أُزْلِفَتْ ﴿١٣﴾

ጀነትም ለደንበኞቿ ተዘጋጅታ ስትቀርብ (እጅግ ያማረች ውብ ሆና)፤

عَلِمَتْ نَفْسٌ مَّآ أَحْضَرَتْ ﴿١٤﴾

ያኔ ነው! ነፍስ ሁሉ ያቀረበችውን ነገር የምታውቀው (ደህና ሆና፣ በዛም አነሰ ውጤቱ ይታያልና)::

فَلَآ أُقْسِمُ بِٱلْخُنَّسِ ﴿١٥﴾ ٱلْجَوَارِ ٱلْكُنَّسِ ﴿١٦﴾ وَٱلَّيْلِ إِذَا عَسْعَسَ ﴿١٧﴾

وَٱلصُّبْحِ إِذَا تَنَفَّسَ ﴿١٨﴾ إِنَّهُۥ لَقَوْلُ رَسُولٍ كَرِيمٍ ﴿١٩﴾

የቁርአን ጉዳይ እናንተ እንደምትሉት አለመሆኑን ላረጋግጥላችሁ:- በቀን ብርሃን ተሰዋሪ፣ በአየር ላይ ተሽከርካሪ፣ በአድማስ ጀርባ ደፍጠው ዟሪ በሆኑት ከዋክብቶችም ነው የምምልላችሁ:: በተጨማሪም ከፈለጋችሁ የሌሊቱ ክፍለ ጊዜ ጨለማውን አግበስብሶ ሲመጣባችሁ፣ በንጋቱም ወጋገን ብርሃኑ ደምቆ ሲወጣላችሁ ልማልላችሁ:: እሱ በእርግጥ ማለትም ቁርአን የተከበረው የራዕያችን ደንበኛ፣ ታማኙ ጂብሪል የተቀበለው ቃል ነው ከእኛ::

ذِى قُوَّةٍ عِندَ ذِى ٱلْعَرْشِ مَكِينٍ ﴿٢٠﴾ مُّطَاعٍ ثَمَّ أَمِينٍ ﴿٢١﴾

ያም! መልዕክተኛ ከዙፋኑ ባለቤት ዘንድ ብርቱ ኃይለኛ የማዕረግ ባለቤት ነው:: እርሱም በላይኛው ዓለም በሁሉ ዘንድ ተሰሚና ተከባሪ ለጌታው እጅግ ታማኝ ታታሪ ነው::

وَمَا صَاحِبُكُم بِمَجْنُونٍ ﴿٢٢﴾

የእናንተው ወገን የሆነው (ሙሐመድ ደግሞ ሁሉም በግልፅ እንደሚያውቀው ሙሉ ጤናማ ብልህ መሪ እንጂ) እብድ ነው ማለት ዘበት ነው። (ይህንም ያለው የአላህን ነብይ እርሱኮ እብድ ነው አትስሙት! ይሉ ስለነበር ነው።)

وَلَقَدْ رَآهُ بِالْأُفُقِ الْمُبِينِ ﴿٢٣﴾

ወላሂ እርሱኮ ጂብሪልን በተፈጥሮው መልኩ ሆኖ በግልፅ አድማስ ላይ እያለ ያየው በእርግጥ ነው።

وَمَا هُوَ عَلَى الْغَيْبِ بِضَنِينٍ ﴿٢٤﴾

እርሱም የራዕይ መልዕክቱን ለማንም ሰው ከማካፈል ንፉግ እንዳላይደለ ነው። (ማለትም ነብያችሁ ለሁላችሁም ያለ አድልዎ ቁርአንን የሚያስተምር ነው ማለቱ ነው።)

وَمَا هُوَ بِقَوْلِ شَيْطَانٍ رَّجِيمٍ ﴿٢٥﴾ فَأَيْنَ تَذْهَبُونَ ﴿٢٦﴾

ይህም የማነበው ቁርአን የአላህ ፀጋ ነው እንጂ የተረገመው ሰይጣን ቃል ጭራሽ እንዳላይደለ ነው። ታዲያ ዕውነቱን ችላ ብላችሁ የምትሄዱት ወዴት ነው?

إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ لِّلْعَالَمِينَ ﴿٢٧﴾ لِمَن شَاءَ مِنكُمْ أَن يَسْتَقِيمَ ﴿٢٧﴾

እሱም ለዓለማት ህዝቦች ጠቃሚ ተግሳፅ እንጂ አሉባልታ እንዳላይደል ነው። ስለዚህ ከእናንተ መሃል ሐቅን የሚፈልግ ካለ፣ በእሱ ቀጥ ብሎ መጓዝ ነው (ይህንን ሲላቸው ደግሞ «ለሚሻ ሰው ብሏልና እኛ እንሻም» ሲሉ ጊዜ በለየለት ድርቅናቸው፦)

وَمَا تَشَاءُونَ إِلَّا أَن يَشَاءَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ ﴿٢٩﴾

ወትሮም የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻኮ በስተቀር እናንተ ምንንም ነገር መሻት አትችሉም አላቸው።

ሱረቱል-ኢንፊጣር سورة الإنفطار

የሰማይ መሰንጠቅ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ ዘጠኝ አንቀፆች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም እንደ ጓደኛዋ የተክዊር ምዕራፍ የትንሳኤን ክስተትና ከእሷ የሚወለዱትን አጠቃላይ ውጥንቅጦች ታወሳለች:: ቀጥላ ደግሞ የሰው ልጅ የጌታን ፀጋ ተጎናፅፎ ሳለ፣ እርሱ ግን ምስጋና ቢስ መሆኑን ታወግዛለች:: ከዚያም ሰዎች በዚያ ቀን ለሁለት ይከፈላሉ:- ከፊሎች ደጎች ለጀነት የተመደቡ ሲሆኑ፣ ሌሎች ጭቡዎች የሲያል ድርሻ ይሆናሉ:: ያኔ ሰዎች ማንም ለማንም እንደማይጠቅም ተገንዝበው ሥልጣን በሙሉ የአላህ ብቻ መሆኑን ይረዳሉ ትላለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنفَطَرَتْ ۝١ وَإِذَا ٱلْكَوَاكِبُ ٱنتَثَرَتْ ۝٢ وَإِذَا ٱلْبِحَارُ فُجِّرَتْ ۝٣ وَإِذَا ٱلْقُبُورُ بُعْثِرَتْ ۝٤

ሰማይ ስትሰነጣጠቅ ከዋክብቶችም ሲረግፉ፣ ባሕሮችም (ተደበላልቀው) አንድ ወጥ ሆነው ሲያርፉ፣ ከዚያም እሳት ጋማ ሆነው ከነጭራሹ ሲጠፉ፣ ቀብሮችም ተገለባብጠው (አስከሬኖችን ሲተፉ)፤

عَلِمَتْ نَفْسٌ مَّا قَدَّمَتْ وَأَخَّرَتْ ۝٥

ያኔ! ነፍስ የተባለች ያስቀደመችውንና ያስቆየችውንም ነገር ሙሉ በሙሉ ታውቃለች:: (ማለትም እነዚህ ነገሮች በዚያ ዕለት ሲከሰቱ፣ ማንኛውም ሰው በደንብ ይረዳል ስለሥራ ውጤቱ፤ ብርቱውም እንደትጋቱ፣

ሰነፉም እንደ ድክመቱ ከሀዲውም ባለዕምነቱ፣ ይለያል ግርዱ ከምርቱ::)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ﴿٦﴾ ٱلَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ

فَعَدَلَكَ ﴿٧﴾ فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ﴿٨﴾

ኧረ አንተ ሰው! ለመሆኑ ምንድን ነው? በቸሩ ጌታህ እንድታምፅ ያነሳሳህ? እሱኮ ነው! ያልነበርከውን ፈጥሮ ያስገኘህ፤ የአካል ክፍሎችህንም መጥኖ በሚገባ አስተካክሎ ተክልህንም አመዛዝኖ ቀጥ ያደረገልህ፤ በፈለገው ቅርጽ ዓይነት ሰውነትህን በማዋቀር አሳምሮ የገነባልህ፤ (ታዲያ ጌታህ በችሮታው ይህን ሁሉ አድርጎልህ ከእርሱ ሌላ ምንድን ነው ማምለክ የሚያምርህ? ማለቱ ነው:: ይህ መለኮታዊ ጥያቄኮ በእውነት ረጋ ብሎ ለሚያስተውለው የሰውን ልጅ ጌታው ሳይፈርድበት በፊት በቀጥታ ወደገዛ ህሊናው ራሱን ከሶ በራሱ እንዲዳኝ የሚያደርግ ጥልቅ የሆነ ተግሳጽ ነው::

كَلَّا بَلۡ تُكَذِّبُونَ بِٱلدِّينِ ﴿٩﴾ وَإِنَّ عَلَيۡكُمۡ لَحَٰفِظِينَ ﴿١٠﴾ كِرَامٗا كَٰتِبِينَ ﴿١١﴾

يَعۡلَمُونَ مَا تَفۡعَلُونَ ﴿١٢﴾

ኧረ እናንተ ሰዎች ተው! ይህ ትዕቢታችሁ ይቅርባችሁ! እንዲያውም እናንተኮ ይህ ሳይበቃችሁ የፍርዱንም ቀን መምጣት ጭራሽ ታስተባብላላችሁ! በእናንተኮ ላይ በእርግጥ የማታይዋቸው ተቆጣጣሪዎች አሉባችሁ:: እነርሱም በጌታቸው ዘንድ ክቡራን ባለማዕረጎች፣ ብቁ ንቁ ፀሃፊዎች ሲሆኑ በሙያቸው፣ የምትሠሩትን ሁሉ ጠንቅቀው ነው የሚያውቁ እኮ በላቸው::

إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٖ ﴿١٣﴾ وَإِنَّ ٱلۡفُجَّارَ لَفِي جَحِيمٖ ﴿١٤﴾ يَصۡلَوۡنَهَا يَوۡمَ ٱلدِّينِ ﴿١٥﴾ وَمَا

هُمۡ عَنۡهَا بِغَآئِبِينَ ﴿١٦﴾

እነዚያኮ በእርግጥ ጌታቸውን ይፈሩ መልካም ተግባራትንም ይሠሩ የነበሩት አማኞች ሳሉ በህይወታቸው፣ እጅግ በተዋበችው ፀጋማዋ ጀነት ውስጥ ነው መኖሪያቸው በላቸው:: እነዚያ ጠማማዎቹ ደግሞ በክህደታቸው፣ እጅግ በጋመው የሲያል እሳት ውስጥ ናቸው:: በመሆኑም ያች ከባድ ቀን ስትደርስላቸው፣ ይጋፈጧታል በአፍጢማቸው:: እነርሱም በምንም በኩል ከእሷ ማምለጫ የላቸው::

وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ﴿١٧﴾ ثُمَّ مَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ﴿١٨﴾ يَوۡمَ لَا تَمۡلِكُ نَفۡسٞ لِّنَفۡسٖ شَيۡـٔٗاۖ وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ ﴿١٩﴾

ለመሆኑ ነብዩ አንተስ የፍርድ ቀኑን ምንነት እኛ ካልነገርንህ በቀር የሚያሳውቅህ ምንድን ነው? አሁንስ ያ! የፍርድ ቀን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የሚያሳውቅህ ምንድን ነው? (ማለትም የእሱን ምንነት ማገኛውም ሰው ይቅርና አንተ እንኳ እንደማታውቀው ነው ማለቱ ነው::) እሱም በአጭሩ ማንኛዋም ነፍስ ለሌላዋ ነፍስ ምንም ልታደርግ የማትችልበት ቀን ነው:: በዚያ ቀን እኮ ፍፁም ትዕዛዝና ሥልጣን የአላህ ብቻ ነው፤ ሌላው ሁሉ በዚያ ቀን አቅሙን አውቆ ፀጥ ለጥ ብሎ ውሳኔ ፍርዱን ተቀባይ ነው ማለቱ ነው::

ሱረቱል-ሙጠፊፊን سورة المطففين

የሰላቢዎች ምዕራፍ ከፊሏ በመካ ከፊሏ በመዲና የወረደች፣ ሰለሳ ስድስት አንቀጾች ያሏት አጠር ያለች ምዕራፍ ናት:: ከመሆኑም ጋር ስለዕምነት ነጥቦችና በተጓዳኝም ስለማህበራዊ እንዲሁም ስለኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ታወሳለች:: ከዚያም ሰዎችን በሁለት ጎራ በመክፈል የሁላቸውንም ዋጋ ምን እንደሚሆን ትገልጻለች:: ዛሬ መሳቂያ መሳለቂያ ሆነው ያሉት አማኞች ነገ ደግሞ በተራቸው፣ ከሃዲያን ሲከስሩ እንደማይቀር መሳቃቸው ታረጋግጥልናለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም
(እንጀምራለን።)

وَيْلٌ لِّلْمُطَفِّفِينَ ﴿١﴾ ٱلَّذِينَ إِذَا ٱكْتَالُوا۟ عَلَى ٱلنَّاسِ يَسْتَوْفُونَ ﴿٢﴾ وَإِذَا كَالُوهُمْ
أَو وَّزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ ﴿٣﴾

እነዚያ በተንኮላቸው ሰውን የሚበዘብዙ የሆኑት ሰላቢዎች ወየውላቸው!! እነዚያ ከሌሎች ሰዎች ሲያሰፍሩ ሲገዙ ለራሳቸው፤ በደንብ የሚያስሞሉ ናቸው። ግን እነርሱ ለሌሎች ሲሰፍሩና ሲመዝኑ ሊሸጡላቸው፤ በስውር ዘዴ እያምታቱ በመስለብ ይሆናሉ የሚያከስሯቸው።

أَلَا يَظُنُّ أُو۟لَٰٓئِكَ أَنَّهُم مَّبْعُوثُونَ ﴿٤﴾ لِيَوْمٍ عَظِيمٍ ﴿٥﴾ يَوْمَ يَقُومُ ٱلنَّاسُ لِرَبِّ
ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦﴾

ስመሆኑ እነዚያ ወስላቶች እንደዚህ ማድረጋቸው! ሰዎች በከባዱ ቀን ተነስተው ከቀብራቸው፣ ከዓለማት ፈጣሪ ፊት የሚቆሙበትን ዕለት ዕውነት የማይሉ ናቸው? (እዚህ ላይ የመዲና ነዋሪዎች በቅድመ ኢስላም ይህ ዓይነት ባሕሪ ስለነበረባቸው፣ ነብዩ መጥተው ይህችን ምዕራፍ ሲያነቡላቸው፣ ወዲያው ታረሙ ከመጥፎው ልማዳቸው፤ ቀናዒዎች በመሆናቸው የመለኮታዊው ተግሳፅ ሚስጥሩ ስለገባቸው። አሁንም እኮ አማኞች እንዲህ መሆን ነው የሚገባቸው።)

كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلْفُجَّارِ لَفِى سِجِّينٍ ﴿٧﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا سِجِّينٌ ﴿٨﴾ كِتَٰبٌ مَّرْقُومٌ ﴿٩﴾ وَيْلٌ
يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ ﴿١٠﴾ ٱلَّذِينَ يُكَذِّبُونَ بِيَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿١١﴾ وَمَا يُكَذِّبُ بِهِۦٓ إِلَّا كُلُّ مُعْتَدٍ
أَثِيمٍ ﴿١٢﴾

ከዚህ መጥፎ ተግባራቸው አሁን መቆጠብ አለባቸው:: የከፋተኞች መዝገብ እኮ በጭቡ ማህደር ውስጥ ነው መከማቻው በላቸው:: ያ! ማህደርስ ምን ዓይነት ነገር እንደሆነ አንተስ ምን አሳወቀህ? አላቸው:: ብቻ እርሱ በልዩ ቁጥር የተዘገበ ሰነድ መሆኑን ንገራቸው ቢገባቸው:: በዚያ ቀን አስተባባዮቹ ወየውላቸው!! (ማለትም) እነዚያ የፍርዱን ቀን አስተባባዮች የሆኑት (ቀላል መስሏቸው) ወይ ጥፋታቸው! በእርሱ የሚያስተባብለው ድንበር ዘለል ወንጀለኛ የሆነው ሰው ሁሉ እንጂ ሌላ እንዳላይደለ ነው::

إِذَا تُتْلَىٰ عَلَيْهِ ءَايَـٰتُنَا قَالَ أَسَـٰطِيرُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿١٣﴾

አንቀጾቻችን በእርሱ ላይ ሲነበቡለት ያለ ይሉኝታ በለየለት ሴረኝነት ይህማ እኮ የወትሮ ሰዎች ተረት ነው:: የሚልም ነው (ነብዩን ላለመቀበል ታውሮ በምቀኝነት::)

كَلَّا ۖ بَلْ ۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا۟ يَكْسِبُونَ ﴿١٤﴾ كَلَّآ إِنَّهُمْ عَن رَّبِّهِمْ يَوْمَئِذٍ لَّمَحْجُوبُونَ ﴿١٥﴾

እረ! ይህ አይበጃቸውም ቢተውት ነው የሚሻላቸው፤ ይልቅ እነርሱ ሲሠሩት የነበረው ወንጀላቸው ልቦቻቸውን መርጎ አዝጎባቸው ነው (ሐቁን መመልከት የተሳናቸው):: አሁንም ይህን ነገር ቢተው ነው የሚሻላቸው፤ እነርሱ ዛሬ ሐቁን አናይም በማለታቸው፣ በዚያኛው ዓለም ሲነሱ ከቀብራቸው፣ ጌታቸውን ከማየት ፀጋ የተጋረዱ ከንቱዎች ናቸው::

ثُمَّ إِنَّهُمْ لَصَالُوا۟ ٱلْجَحِيمِ ﴿١٦﴾ ثُمَّ يُقَالُ هَـٰذَا ٱلَّذِى كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ﴿١٧﴾

ከዚያም እነርሱ ጌታን የማየቱ ዕድል መነፈግ ሳይበቃቸው፣ በሲዖል ውስጥ ተጋፍጠው የሚርመጠመጡ ናቸው:: ከዚያም አስተናጋጆቹ ሲኮንኗቸው፣ ይህ ነው እኮ ስታስተባብሉት የነበረው የሲዖል ቅጣት ነው የሚሏቸው::

كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلْأَبْرَارِ لَفِى عِلِّيِّينَ ﴿١٨﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا عِلِّيُّونَ ﴿١٩﴾ كِتَٰبٌ
مَّرْقُومٌ ﴿٢٠﴾ يَشْهَدُهُ ٱلْمُقَرَّبُونَ ﴿٢١﴾

(እነርሱና እነዚያ ደጎቹ አማኞች በጌታቸው፣ በደረጃ አቻዎች አይምሰሏቸው) የእነዚያ የደጎቹማ የሥራ መዝገብ እጅግ በላቀው ማህደር ውስጥ ነውላቸው:: የላቀው ቦታ የተሰኘውስ ምን ዓይነት ቦታ እንደሆነ ምን አሳወቀህ? አላቸው:: (ብቻ በአጭሩ) የእነርሱ መዝገብ በልዩ ቀለም የተፃፈ ነውላቸው:: የአላህ ባለሟሎች ሁሉ እርሱን በአድናቆት በደስታ ይጎበኛሉ በላቸው::

إِنَّ ٱلْأَبْرَارَ لَفِى نَعِيمٍ ﴿٢٢﴾ عَلَى ٱلْأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ﴿٢٣﴾ تَعْرِفُ فِى وُجُوهِهِمْ نَضْرَةَ
ٱلنَّعِيمِ ﴿٢٤﴾

እነዚያኮ ደጋግ የአላህ ወዳጆች ብታያቸው፣ በልዩ ፀጋ ውስጥ ሆነው በተዋቡት ባለ ሽፋን አልጋዎቻቸው በመሰየም ዕድላቸውን በፀጋ የሚመለከቱ ናቸው:: አንተም ገና ስታያቸው በፊቶቻቸው የምቾትን ውበት ነው የምታነብባቸው (ማለትም አንፀባራቂው ውበታቸው በቀጥታ ጠቋሚ ነው፣ ፍፁም ምሉዕ ወደ ሆነው ፀጋቸው ማለቱ ነው:: ያድርገንና ከአደላቸው::)

يُسْقَوْنَ مِن رَّحِيقٍ مَّخْتُومٍ ﴿٢٥﴾ خِتَٰمُهُۥ مِسْكٌ وَفِى ذَٰلِكَ فَلْيَتَنَافَسِ
ٱلْمُتَنَٰفِسُونَ ﴿٢٦﴾

ከታሸገችው ልዩ የጀነት ጠጅም እንዲጠጡ የሚጋበዙ ናቸው:: በመጠጡም ፍፃሜ የሚስክ ሽታ እኮ ነው የሚቀረው በአፎቻቸው:: በመሆኑም ለዚያ ዓይነቱ ታላቅ ዕድል እህን ጊዜ ነው ንቁ ተወዳዳሪዎች ተግተው መሳተፍ ያለባቸው::

وَمِزَاجُهُۥ مِن تَسۡنِيمٍ ﴿٢٧﴾ عَيۡنٗا يَشۡرَبُ بِهَا ٱلۡمُقَرَّبُونَ ﴿٢٨﴾

መበረዣዋም የሚሆነው ከልዩዋ የተስኒም ምንጭ እኮ ነው:: ይህም ለደጋጎች ጠጅ ቅመም የሆነው ተስኒም ባለሟሎች እንደፈለጉ እየጠጡ የሚረኩበት መደበኛ መጠጣቸው ነው በላቸው::

إِنَّ ٱلَّذِينَ أَجۡرَمُواْ كَانُواْ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يَضۡحَكُونَ ﴿٢٩﴾ وَإِذَا مَرُّواْ بِهِمۡ

يَتَغَامَزُونَ ﴿٣٠﴾ وَإِذَا ٱنقَلَبُوٓاْ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِمُ ٱنقَلَبُواْ فَكِهِينَ ﴿٣١﴾

እነዚያማ የገረሩት በጥመታቸው (ሲያምኑ ቀርቶ ራሳቸው) በአማኞቹም የሚሳለቁ የለየላቸው ግፈኞች ናቸው:: በአጠገባቸው ሲተላለፉም ሲያዩዋቸው እየተጠቃቀሱ ነው የሚያሽሟጥጡባቸው፣ ከዚያም መልሰው ሲመጡ ወደ ቤተሰቦቻቸው እነሱን ማማት እኮ ነው እንደ እሸት የሚያረካቸው::

وَإِذَا رَأَوۡهُمۡ قَالُوٓاْ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ ﴿٣٢﴾ وَمَآ أُرۡسِلُواْ عَلَيۡهِمۡ

حَٰفِظِينَ ﴿٣٣﴾

በአጠቃላይም አማኞቹን በየትም ቦታ ሲያይዋቸው፣ እነዚህ እኮ የተወናበዱ ከንቱዎች ናቸው ይላሉ በትችታቸው፣ በእነርሱ ላይ ተቆጣጣሪዎች ሆነው ያልተላኩትን በመዘባረቅ ያለሥራቸው::

فَٱلۡيَوۡمَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنَ ٱلۡكُفَّارِ يَضۡحَكُونَ ﴿٣٤﴾ عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ﴿٣٥﴾ هَلۡ

ثُوِّبَ ٱلۡكُفَّارُ مَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ﴿٣٦﴾

ታዲያ ዛሬ (ማለትም በትንሳዔ ቀን) አማኞቹ በተራቸው፣ በክብር አልጋዎች ላይ ሆነው እየተያዩ እርስ በርሳቸው፣ አስተያየት በመስጠት ስለጠላቶቻቸው፣ እነዚህ ከሃዲያን ይሰሩት የነበረውን ተመነዱ አይደል? እያሉ ነው የሚሳሳቁባቸው::

ሱረቱል-ኢንሺቃቅ سورة الإنشقاق

የሰማይ መቀደድ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሃያ አምስት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት። እሷም እንደ ቢጤዎቿ በዕምነት በክህደት ጉዳይ ላይ ታተኩራለች። አል-ኢንሽቃቅ ዓለም ፍፃሜ ላይ ስትደርስ ከሚከሰቱት ከባድ አስደንጋጭ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዳንዶቹን ትጠቅሳለች። ቀጥላ ደግሞ ማንም ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ በአመነበት መስክ መባተሉ እንደማይቀር አውስታ ከሞት በኋላ ምርመራ እንደሚጠብቀው ታስታውሳለች። ከዚያም የሥራ መዝገቡን በቀኙ ወይም በግራው መቀበሉ እንደማይቀርም ታረጋግጥለታለች።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنشَقَّتۡ ﴿١﴾ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ﴿٢﴾ وَإِذَا ٱلۡأَرۡضُ مُدَّتۡ ﴿٣﴾
وَأَلۡقَتۡ مَا فِيهَا وَتَخَلَّتۡ ﴿٤﴾ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ﴿٥﴾

ሰማይ በምትቀዳደድበት ዕለት፣ የጌታዋን ትዕዛዝም በምታዳምጥበት ወቅት ማዳመጧም ተገቢ ነውና (በዕውነት)፣ ምድርም ጎራ ተራራዋ ጠፍቶ (እንደተለጠጠ ቆዳ ስትሆን ለጥ ያለች ሜዳ)፣ በከርሷ ያለውን ሁሉንም አውልቃ ጥላ ባዶዋን ስትቀር (እንደተራገፈ አቅማዳ)፣ የጌታዋንም ትዕዛዝ ስትሰማና ለመፈራረስ (ስትሰናዳ) መስማትም ይገባታል (ተሰሚ አዛዥ የለምና ከእርሱ ወዲያ)፣ ያኔ ነው (የሰውን ልጅ የሚያጋጥመው ያልጠበቀው ከባድ ዕዳ)።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ﴿٦﴾

የሰው ልጅ ሆይ! አንተ በእርግጥ በየዕለቱ ወደ ጌታህ በመጓዝ ላይ እያለህ፣ ለትሮህ በመጨነቅ መልፋትን ትለፋለህ፤ (ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን ጉዞህ ይጠናቀቅና) ከእርሱ ጋር ትገናኛለህ (የሥራ ዋጋህንም ያኔ ታገኛለህ::)

فَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ﴿٧﴾ فَسَوْفَ يُحَاسَبُ حِسَابًا يَسِيرًا ﴿٨﴾

وَيَنقَلِبُ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦ مَسْرُورًا ﴿٩﴾

በዚያ ቀን የሥራ መዝገቡን በቀኝ እጁ የተሰጠ ሰው እድለኛ ነውና ቀላል የሆነ ምርመራን እንደሚመረመር ነው፤ ከዚያም ወደ ቤተሰቡ በደስታ እንደሚመለስ ነው::

وَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهْرِهِۦ ﴿١٠﴾ فَسَوْفَ يَدْعُوا۟ ثُبُورًا ﴿١١﴾ وَيَصْلَىٰ

سَعِيرًا ﴿١٢﴾ إِنَّهُۥ كَانَ فِىٓ أَهْلِهِۦ مَسْرُورًا ﴿١٣﴾

ያ! ደግሞ የሥራ መዝገቡን ከጀርባው ኋላ የተሰጠው በውጤቱ በመደንገጥ ወየው ጥፋቴ እንደሚል ነው፤ እንደፈራውም በተንቀልቃዩዋ እሳት ውስጥ ገብቶ እንደሚርመጠመጥ ነው:: ምክንያቱም እርሱ በቤተሰቡ ውስጥ ሳለ፣ ጌታ በማይወደው ሁሉ ሲደሰት የነበረ ነው::

إِنَّهُۥ ظَنَّ أَن لَّن يَحُورَ ﴿١٤﴾ بَلَىٰٓ إِنَّ رَبَّهُۥ كَانَ بِهِۦ بَصِيرًا ﴿١٥﴾

እነሆ እንዲያውም እሱ ከሞት እንደማይመለስ ይገምት የነበረ ነው:: እንዴታ! የእርሱኮ ጌታ ጉዳዩን በጥልቅ ተመልካች፣ ድብቅ ሚስጥር አዋቂ ነው:: (በመሆኑም ሠራተኛን በሥራው መመንዳቱ የማይቀር ነው ማለቱ ነው::)

فَلَآ أُقْسِمُ بِٱلشَّفَقِ ﴿١٦﴾ وَٱلَّيْلِ وَمَا وَسَقَ ﴿١٧﴾ وَٱلْقَمَرِ إِذَا ٱتَّسَقَ ﴿١٨﴾

لَتَرْكَبُنَّ طَبَقًا عَن طَبَقٍ ﴿١٩﴾

ቁም ነገሩ እንዳላይደለ እናንተ እንደሚመስላችሁ፣ በምሽቱ ወጋገን እየማልኩ ነው የማረጋግጥላችሁ:: በሌሊቱና በጨለማው በሚሸፍነውም ነገር ሁሉ፣ በጨረቃውም ብርሃኑ ሲሆን ሙሉ፣ ጨምሬ ልማልላችሁ:: እናንተ በእርግጥ በተከታታዮቹ የተለያዩ ከባድ ጉዳዮች ትሸጋገራላችሁ (ለምሳሌ ከህይወት ኋላ ወደ ሞት፣ ከዚያም ወደ መነሳትና ወደ መመርመር፣ ቀጥሎም ወደ መመንዳት መሸጋገር አይቀርላችሁ:: ወደዳችሁም ጠላችሁ ማለቱ ነው::)

فَمَا لَهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿٢٠﴾ وَإِذَا قُرِئَ عَلَيْهِمُ ٱلْقُرْءَانُ لَا يَسْجُدُونَ ۩ ﴿٢١﴾

ታዲያ ጉዳዩ እንዲህ ግልጽ ሆኖላቸው ለምንድን ነው የማያምኑት (በነገርናቸው)? ቁርአንስ በንባብ ሲቀርብላቸው ዝቅ የማይሉት በትህትና ለጌታቸው?

بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ يُكَذِّبُونَ ﴿٢٢﴾ وَٱللَّهُ أَعْلَمُ بِمَا يُوعُونَ ﴿٢٣﴾ فَبَشِّرْهُم

بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ﴿٢٤﴾

እንዲያውምኮ እነዚያ ከሓዲያን አሁን ጭራሹን ብሶባቸው ምንም ነገር ብትላቸው፣ ሳያስተውሉ ፈጥነው በማን አለብኝ የሚያስተባብሉ ናቸው:: አላህኮ እነርሱ የሚያምቁትን ጥላቻ በልባቸው፣ እጅግ ነው የሚያውቅባቸው:: ስለዚህ እነርሱን በዚህ መጥፎ ባህሪያቸው፣ አሳማሚ በሆነው ቅጣት አብስራቸው::

إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمْ أَجْرٌ غَيْرُ مَمْنُونٍ ﴿٢٥﴾

ዳሩ ግን እነዚያ ያመኑትና መልካም ሥራዎችን ያከናወኑት ለጌታቸው፣ ለእነርሱ የማይቋረጥ ታላቅ ምንዳ ነው ያላቸው::

ሱረቱል-ቡሩጅ سورة البروج

የፈለክ ኬላዎች ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሃያ ሁለት አንቀጾችን የያዘች አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም እንደ ጓደኞቿ ኢስላማዊ ዕምነት ነጥቦች ላይ ታተኩራለች:: በተለይ እሷ እጅግ የምታነጣጥረው በእሳቱ ምሽግ ታሪክ ላይ ነው:: በአጠቃላይ ይዘቷም የምታስገነዝበው ማንም ጥጋበኛ ሰው ደካሞችን ሲጨፈጭፍ ለጊዜው ጌታ ዝም ያለውም ቢመስለው አንድ ቀን ድንገት መያዙ አይቀሬ መሆኑን ነው::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلۡبُرُوجِ ١ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡمَوۡعُودِ ٢ وَشَاهِدٖ وَمَشۡهُودٖ ٣

قُتِلَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأُخۡدُودِ ٤

የፈለካዊ መናኸሪያ በሆነችው ሰማይና በታላቋም ቀጠሮ ቀን (ማለትም በቂያማ ዕለት) እምላለሁ፤ ከዚያም ሌላ በመስካሪና በሚመሰከርበትም ሁሉ ቃለ-መሃላን አፈፅማለሁ፤ የምሽጉ ባለቤቶች እኛ ዘንድ ተረግመዋል አላችኋለሁ::

ٱلنَّارِ ذَاتِ ٱلۡوَقُودِ ٥ إِذۡ هُمۡ عَلَيۡهَا قُعُودٞ ٦ وَهُمۡ عَلَىٰ مَا يَفۡعَلُونَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ

شُهُودٞ ٧

ምሽግም ያልነው የጋመ እሳት የተሞላበት የሆነውን ጉድጓድ ነው:: በእነርሱም ላይ እርግማኑን ያስፈረው በጉድጓዱ ዙሪያ ላይ ተኮልኩለው በመቀመጥ በአማኞቹ

ላይ በፈፀሙት ግፍ ደስተኞች ሆነው በተገኙበት ሰዓት ነው:: (ይህም ግፍ የተፈፀመው በተደጋጋሚም ቢሆን በተለይ በሙስሊም ሐዲስ የተዘገበው በአንድ ወቅት አንድ ወጣት ለዕምነቱ በሠራው ጀብዱ ዜጎቹን ለጅምላ ዕምነት ሲያበቃቸው፣ አምባገነኑ ንጉሳቸው ««እኔ አልፈቀድኩም ተው!» ቢላቸው፣ «እምቢ!» ብለው በዕምነታቸው በመጽናታቸው፣ በየሰፈሩ ጥልቅ ጉድጓድ አስቆፍሮ እንጨት በመሙላት እሳቱ እንደተጋጋመ በወታደሮች እያሳፈሰ ሲጨምራቸው፣ ፍንክች አላሉም ከዕምነታቸው:: አንዲት ሴት ብቻ አራሱን ልጇን ይዞ መግባቱ ጨንቋት እያለች በማመንታት፣ «እማዬ! በሐቅ ላይ ነን ግዴለሽም እንግባ!» ሲላት፣ እርሷም ወረደች ደስ እያላት፤ ያኔ ታዲያ ግፈኞቹ ባለሥልጣናት፣ በአካባቢው ተደርድረው በደስታ ይዝናኑ ነበር በእነርሱ ስቃይ በመርካት)

وَمَا نَقَمُوا مِنْهُمْ إِلَّا أَن يُؤْمِنُوا بِاللَّهِ الْعَزِيزِ الْحَمِيدِ ﴿٨﴾ الَّذِي لَهُ مُلْكُ

السَّمَٰوَٰتِ وَالْأَرْضِ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ ﴿٩﴾

እነርሱንም እንዲጠሉ ያደረጋቸው በአሸናፊው ምስጉን ጌታቸው በአላህ ማመናቸው ቢሆን እንጂ ሌላ ምክንያት አልነበረም በላቸው:: (እስካሁንም በዓለም ዙሪያ በአማኞች ላይ እየተደገመ ያለው ይኸው በደል ነው::) እውነተኛ አሸናፊ ምስጉንም የሚባለው ያ! የሰማያትና የምድር ንግስና የእርሱ ብቻ የሆነለት አላህ እኮ ነው:: አላህም በሁሉም ነገር ቅርብ ታዛቢ መስካሪ ነው:: ስለዚህ ኃያሉ አላህ ይህን ታሪክ እዚህ ላይ የጠቀሰው አማኞቹን ለማፅናናት ግፈኖቹን ለመገሰፅ ነው::

إِنَّ الَّذِينَ فَتَنُوا الْمُؤْمِنِينَ وَالْمُؤْمِنَاتِ ثُمَّ لَمْ يَتُوبُوا فَلَهُمْ عَذَابُ جَهَنَّمَ

وَلَهُمْ عَذَابُ الْحَرِيقِ ﴿١٠﴾

እነዚያኮ ወንዶች አማኞችን እና ሴት ምዕመናትን ያሰቃዩት በዕምነታቸው፣ ከዚያም በኋላ ተፀፅተው

ያልተመለሱት ከጥፋታቸው፤ በክህደታቸው ሳቢያ የሲያል ቅጣት ሲገባቸው፣ አማኞችንም በማቃጠላቸው አንፃር ተጨማሪ አቃጣይ ቅጣት አለባቸው::

إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ لَهُمْ جَنَّاتٌ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ

ذَٰلِكَ الْفَوْزُ الْكَبِيرُ ﴿١١﴾

እነዚያማ በዕውነት አምነው መልካም ሥራዎችን የሠሩት (ጌታቸው እንዳዘዛቸው) ለእነርሱ ከስሮቻቸው ጅረቶች እየጎረፉ የሚሰራጩባቸው አትክልታማ የደስታ አገሮች አሏቸው:: ይህ ነውኮ ለቀናው ሰው ታላቅ ዕድል በላቸው::

إِنَّ بَطْشَ رَبِّكَ لَشَدِيدٌ ﴿١٢﴾ إِنَّهُ هُوَ يُبْدِئُ وَيُعِيدُ ﴿١٣﴾ وَهُوَ الْغَفُورُ الْوَدُودُ ﴿١٤﴾

ذُو الْعَرْشِ الْمَجِيدُ ﴿١٥﴾ فَعَّالٌ لِّمَا يُرِيدُ ﴿١٦﴾

ማስጠንቀቂያ ተግሳፅም እኮ ለማይበግረው የጌታህ የቁጣ አያያዝ እጅግ አሸመድማጅና ከባድ ነው:: እነሆ እርሱኮ በመጀመሪያ ፈጣሪ እንደገናም ከሞት በኋላ መልሶ አዳኝ ነው:: እርሱም ለአማኝ ባሪያዎቹ እጅግ መሐሪ፣ በጣም አፍቃሪ ወዳጅም ነው:: እርሱም ባለግዙፉ ዙፋን ከሁሉ በላይ የሆነ ፍፁም ታላቅ ነው:: የፈለገውንም ጉዳይ ያለምንም አስተጓጓይ በቀጥታ ፈፃሚ ነው::

هَلْ أَتَاكَ حَدِيثُ الْجُنُودِ ﴿١٧﴾ فِرْعَوْنَ وَثَمُودَ ﴿١٨﴾

የገናናዎቹ ሰራዊቶችስ ዜና ደረሰህን (ምን እንዳጋጠማቸው)? እነርሱም ካልከኝ እነማን ናቸው? ፈርዖንና ሰሙዶች ናቸው እጅግ በመባለጋቸው፣ (ጌታህ ባላሰቡት ነገር እንኮታኩቶ የጣላቸው::)

بَلِ الَّذِينَ كَفَرُوا فِي تَكْذِيبٍ ﴿١٩﴾ وَاللَّهُ مِن وَرَائِهِم مُّحِيطٌ ﴿٢٠﴾

እነዚህ ከሃዲያን ከእነዚያ የቀድሞ ቢጤዎቻቸው ታሪክ ሊማሩ ሲገባቸው፣ ይልቅ እነርሱም በተራቸው ይባስ

ብለው በማስተባበል ላይ ናቸው፤ አያውቁም እንጅ ሞኝነታቸው አላህ እኮ እነርሱንም ከቧቸዋል ከኋላቸው።

بَلْ هُوَ قُرْءَانٌ مَّجِيدٌ ﴿٢١﴾ فِي لَوْحٍ مَّحْفُوظٍ ﴿٢٢﴾

ይልቅ ሐቁ ቢገባቸው፣ ይህ አንተ አምጥተህ የምታነብላቸው ታላቅ ቁርአን ነው የወረደ ከጌታቸው። እርሱኮ ገና ዱሮ በጥብቁ ሰሌዳ ውስጥ የነበረ ክብር መርሆ ነው በላቸው። (አልባሌ ተራ ነገር አይምሰላቸው)።

ሱረቱ-ጧሪቅ سورة الطارق

የጧሪቅ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ ሰባት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት። እሷም እንደ ጓደኞቿ ከሞት በኋላ መቀስቀስን ታረጋግጥልናለች። በዚያ ቀን ሚስጥሮች ሁሉ፣ ይጋለጣሉ በሙሉ፤ ተከሳሽም አቅም የለው የሚረዱትም አይኖሩ ስትል ታስጠነቅቃለች። ቁርአንም ሐቅን አብራሪ፣ ቁም ነገርን አስተማሪ መሆኑን ትነግረናለች።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

وَٱلسَّمَآءِ وَٱلطَّارِقِ ﴿١﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا ٱلطَّارِقُ ﴿٢﴾ ٱلنَّجْمُ ٱلثَّاقِبُ ﴿٣﴾ إِن كُلُّ نَفْسٍ لَّمَّا عَلَيْهَا حَافِظٌ ﴿٤﴾

በሰማይና በሌሊት ቀርቋሪውም ነገር እምላለሁ። የሌሊት ቀርቋሪው ምን እንደሆነ (ካልነገርንህ) ምን ታውቃለህ? እርሱም ድቅድቁን ጨለማ በብርሃኑ ሸንቋሪ

የሆነው ኮኮብ ነውልህ:: ታዲያ በእነዚህ ነገሮች ምዬ የማረጋግጥልህ ነፍስ ሁሉ በእሷ ላይ ተቆጣጣሪ ያለባት ብትሆን እንጂ እንዲያው ልቅ የተተዎች አትምሰልህ::

فَلْيَنظُرِ ٱلْإِنسَٰنُ مِمَّ خُلِقَ ﴿٥﴾ خُلِقَ مِن مَّآءٍ دَافِقٍ ﴿٦﴾ يَخْرُجُ مِنۢ بَيْنِ ٱلصُّلْبِ وَٱلتَّرَآئِبِ ﴿٧﴾

እስኪ ይህ ሰው ከምን እንደተፈጠረ ማንነቱን ረጋ ብሎ ያስተውለው:: መጀመሪያኮ የተፈጠረው በስሜት ተነሳስታ ከምትፈነጠረው ቅንጣት ጠብታ ውሃ ነው:: እሱም የሚመነጨው ከወንዶች የጀርባ አጥንትና ከሴቶች ደረት መሃል ነው::

إِنَّهُۥ عَلَىٰ رَجْعِهِۦ لَقَادِرٌ ﴿٨﴾ يَوْمَ تُبْلَى ٱلسَّرَآئِرُ ﴿٩﴾ فَمَا لَهُۥ مِن قُوَّةٍ وَلَا نَاصِرٍ ﴿١٠﴾

እነሆ ነገም ጌታህ እኮ እሱን ከሞት ለመመለስ በእርግጥ ቻይ ነው:: ያም የሚሆነው ሚስጥሮች ሲጋለጡና እሱም ጉልበተ ቢስ ሲሆን ረዳትም በሚገድበት ዕለት ነው በላቸው::

وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلرَّجْعِ ﴿١١﴾ وَٱلْأَرْضِ ذَاتِ ٱلصَّدْعِ ﴿١٢﴾ إِنَّهُۥ لَقَوْلٌ فَصْلٌ ﴿١٣﴾ وَمَا هُوَ بِٱلْهَزْلِ ﴿١٤﴾

የተደጋጋሚ ዝናብ ባለቤት በሆነው ሰማይ በበቆልት ተሰንጣቂ በሆነውም ምድር እምላለሁ:: ይህ ቁርአን በእርግጥ እውነትን ከሀሰት ለይቶ የሚያበጥር ልዩ መመሪያ ነው እንጂ እናንተ እንደምታስወሩት አሉባልታ ቀልድ አይደለም እላችኋለሁ::

إِنَّهُمْ يَكِيدُونَ كَيْدًا ﴿١٥﴾ وَأَكِيدُ كَيْدًا ﴿١٦﴾ فَمَهِّلِ ٱلْكَٰفِرِينَ أَمْهِلْهُمْ رُوَيْدًۢا ﴿١٧﴾

ይሁን እንጂ ጠላቶቹ እሱን ከንቱ ጭራሽ ዋጋ ቢስ ሊያስመስሉ ከባድ ሴራን በመቀመር ያሴራሉ:: እኔም

ደግሞ በበኩሌ (ስላልኩ እጠብቀዋለሁ) የእነርሱን ተንኮል ለማምከን ወሳኝ የሆነ ልዩ ዘዴዬን እቀይሳለሁ:: ስለዚህ ከሃዲያኑ ምንም ቢከፉ ደባቸው አትበሳጭ! ዝም በልና አዘግያቸው! (ማለትም) ለትንሽ ጊዜ አቆያቸው (ቀጠሮው እስኪደርስላቸው፤ እንዳለውም ቀጠሮው ሲደርስ ውጤቱን አሳያቸው::)

ሱረቱል-አዕላ سورة الأعلى

የላቀው ጌታ ስም ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ ዘጠኝ አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም ከፃዕምነት ጉዳዮች ሦስት ነጥቦችን ታወሳለች::

አንደኛ:- የአላህን ማንነትና ባህሪያቱን (ማለትም የእርሱን ኃይልና ጥበብ ፍፁም ዕውቀቱን) ታስገነዝበናለች::

ሁለተኛ:- አላህ ቁርአንን ለነብዩ በፊቃዱ እንደቸራቸው፣ ጥናቱንም እንደሚያገራላቸው ቃል መግባቱን ታወሳለች::

ሦስተኛ:- ቀናዒዎቹ አማኞች ተግሳፅ ይጠቅማቸዋልና ምንጊዜም አስታውሳቸው ትላለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

سَبِّحِ ٱسْمَ رَبِّكَ ٱلْأَعْلَى ﴿١﴾ ٱلَّذِى خَلَقَ فَسَوَّىٰ ﴿٢﴾

ነብዩ ሆይ! ከሁሉም በላይ የላቀውን ጌታህን ስም ከመጥፎው ሁሉ በማጥራት አወድሰው:: እርሱኮ ነው

ያ! ፍጥረታትን ያስገኘና ሥነ-ፍጥረቱንም የተሟላ በማድረግ ቅርፁን ያስተካከለው::

وَٱلَّذِي قَدَّرَ فَهَدَىٰ ﴿٣﴾ وَٱلَّذِيٓ أَخۡرَجَ ٱلۡمَرۡعَىٰ ﴿٤﴾ فَجَعَلَهُۥ غُثَآءً أَحۡوَىٰ ﴿٥﴾

እርሱም ነው ያ! ሁሉን ነገር በተለያየ ቅርፅ የመጠነና ከዚያም ጥቅሙን የመራና ያሳወቀው:: እርሱኮ ነው ለእንስሳትም ግጦሽን ያበቀለው:: ከዚያም በኋላ እርሱኮ ነው ቀዘባ ለምለም የነበረውን የገረጣ ድቃቂ መና ያደረገው::

سَنُقۡرِئُكَ فَلَا تَنسَىٰٓ ﴿٦﴾ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۚ إِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلۡجَهۡرَ وَمَا يَخۡفَىٰ ﴿٧﴾

ይህንም ቁርአን አስነብበን እንደምናሳውቅህና ከዚያም በኋላ እንደማትረሳው ነው:: ግን አላህ ሊሽረው የፈለገውን አንቀጽ ሊያስረሳህ እንደሚችል ነው:: እነሆ እርሱኮ ጮኸ ያለና ደከም የሚለውንም ድምጽ በሚገባ ለይቶ የሚያውቅ ነው::

وَنُيَسِّرُكَ لِلۡيُسۡرَىٰ ﴿٨﴾ فَذَكِّرۡ إِن نَّفَعَتِ ٱلذِّكۡرَىٰ ﴿٩﴾

እኛኮ ለአንተ ያቀድነው ለስላሳዋን ቀላል መስመር ልንገጥምህ ነው:: በመሆኑም በዚህ ቁርአን ሰውን መምከር ጠቃሚ ነው:: ይህም እስከሆነ ድረስ ሰዎችን መምከር መገሰፅ እንዳለብህ ነው:: (ማለትም ይህ ሰው ይሰማል ተብሎ ተስፋ የሚጣልበትን መገሰፅ አስፈላጊ ነው ማለቱ ነው::)

سَيَذَّكَّرُ مَن يَخۡشَىٰ ﴿١٠﴾ وَيَتَجَنَّبُهَا ٱلۡأَشۡقَى ﴿١١﴾

ያኔ እኛን የሚፈራው ምክሩን እንደሚቀበል ነው:: ያ! መጥፎ ደራቃው ደግሞ ምክሯን እንደሚርቃት ነው::

ٱلَّذِي يَصۡلَى ٱلنَّارَ ٱلۡكُبۡرَىٰ ﴿١٢﴾ ثُمَّ لَا يَمُوتُ فِيهَا وَلَا يَحۡيَىٰ ﴿١٣﴾

እሱኮ ነው ከባዷ እሳት ውስጥ ተጋፍጦ እስከወዲያው እንዳይሞትም እንዳይድንም የሚሆነው::

قَدْ أَفْلَحَ مَن تَزَكَّىٰ ﴿١٤﴾ وَذَكَرَ اسْمَ رَبِّهِ فَصَلَّىٰ ﴿١٥﴾

ነፍሱንም በዕምነት አንፆ የጌታውን ስም እያወደሰ የሚሰግደው በእርግጥ የቀናው ዕድለኛ ሰው እርሱ ነው:: ሆኖም ብዙዎቻችሁ ቁም ነገሩ ይህ መሆኑን ዘንግታችሁ:-

بَلْ تُؤْثِرُونَ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا ﴿١٦﴾ وَالْآخِرَةُ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰ ﴿١٧﴾

ይልቅ ቅርቢቱን ህይወት አብልጣችሁ ትመርጣላችሁ:: ያችኛዋ ዓለም ለእናንተ እጅግ የተሻለችና ዘላለማዊ ሆና ሳለ ሞኝነታችሁ ችላ ትሏታላችሁ::

إِنَّ هَٰذَا لَفِي الصُّحُفِ الْأُولَىٰ ﴿١٨﴾ صُحُفِ إِبْرَاهِيمَ وَمُوسَىٰ ﴿١٩﴾

ይህም አሁን ለእናንተ የጠቀስነው በቀድሞ መጽሐፎችም ውስጥ የሰፈረ ቁም ነገር ነው:: (ማለትም ለምሳሌ) በነብዩ ኢብራሂምና በነብዩ ሙሳም መጽሐፍት የተዘገበ ጠቃሚ ገንቢ ተግሳፅ ነው ማለቱ ነው::

ሱረቱል-ጋሽያ سورة الغاشية

የሸፋኝቷ ቀን ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሃያ ስድስት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን ትዳስሳለች:-

አንድ:- ስለቂያማ ቀንና በዚያ ዕለት ስለሚከሰቱት ከባድ አስደንጋጭ ተከታታይ ጉዳዮች እና

ሁለት:- የዓለማት ጌታ ፍፁም ቻይና አጋር አልባ ብቸኛ አምላክ መሆኑን የሚያስታውሱን ነገሮች ትጠቅሳለች:: ከዚያም በመጨረሻ የሁሉም ነገር መመለሻ ወደ እርሱ ነው ትላለች::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلۡغَٰشِيَةِ ﴿١﴾

(አላህ ለመልዕክተኛው ስለቂያማ ቀን ሊነግራቸው፣ በጥያቄ መልክ እንዲሳብ ትኩረታቸው) ነብዩ ሆይ! ሁሉን ሰው በመከራዋ የምትሸፍነው ከባድ ቀን ወሬ ደረሰህን? አላቸው::

وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٍ خَٰشِعَةٌ ﴿٢﴾ عَامِلَةٞ نَّاصِبَةٞ ﴿٣﴾ تَصۡلَىٰ نَارًا حَامِيَةٗ ﴿٤﴾

تُسۡقَىٰ مِنۡ عَيۡنٍ ءَانِيَةٖ ﴿٥﴾

ፊቶችኮ በዛ ዕለት የተጨነቁ ናቸው:: ከዚያም እነሱ እልህ አስጨራሽ ከባድ የሆኑ ሥራዎችን የሚሠሩ ለፊዎች ናቸው:: ያም ሳይበቃቸው በጋመው እሳት የሚጋፈጡ፣ እጅግ ከፈላው ምንጭ ውሃም ተገደው የሚጠጡ ይሆናሉ (አማራጭ ስለሌላቸው::)

لَّيۡسَ لَهُمۡ طَعَامٌ إِلَّا مِن ضَرِيعٖ ﴿٦﴾ لَّا يُسۡمِنُ وَلَا يُغۡنِي مِن جُوعٖ ﴿٧﴾

እነርሱም ደግሞ ረሃብ ሲለቀቅባቸው ሰውነትን የማያዳብር–የማያስበላቸው ረሃብንም የማይከላከልላቸው እጅግ አስቀያሚና እሾካም ከሆነው ዶሪእ ዛፍ እንጂ ሌላ ምግብም የላቸው::

وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٖ نَّاعِمَةٞ ﴿٨﴾ لِّسَعۡيِهَا رَاضِيَةٞ ﴿٩﴾ فِي جَنَّةٍ عَالِيَةٖ ﴿١٠﴾ لَّا تَسۡمَعُ

فِيهَا لَٰغِيَةٗ ﴿١١﴾

ሌሎቹ ፊቶች ደግሞ በዚያ ቀን ያማሩ የተዋቡ ለስላሶች ናቸው:: የረኩ ደስተኞች ሆነው በሥራ ውጤታቸው

በከፍተኛዋ ጀነት ነዋሪዎች ናቸው:: በእሷም ውስጥ መጥፎ ቃልን ጭራሽ አይሰሙም በላቸው::

فِيهَا عَيْنٌ جَارِيَةٌ ﴿١٢﴾ فِيهَا سُرُرٌ مَّرْفُوعَةٌ ﴿١٣﴾ وَأَكْوَابٌ مَّوْضُوعَةٌ ﴿١٤﴾ وَنَمَارِقُ مَصْفُوفَةٌ ﴿١٥﴾ وَزَرَابِيُّ مَبْثُوثَةٌ ﴿١٦﴾

በእሷ ውስጥ እኮ ገንፍላ የምትጎርፍ ልዩ ምንጭም አለቻቸው:: በእሷም ውስጥ እጅግ የጓኑ ክቡር አልጋዎችና በአጠገባቸው የተደረደሩ ኩባያዎች፣ በመደዳው የተሰየሙም ትራሶች፣ በሰፊው የተዘረጉ እጅግ ብርቅ ድንቅ የሆኑ ስጋጃዎችም አሏቸው::

أَفَلَا يَنظُرُونَ إِلَى ٱلْإِبِلِ كَيْفَ خُلِقَتْ ﴿١٧﴾ وَإِلَى ٱلسَّمَآءِ كَيْفَ رُفِعَتْ ﴿١٨﴾ وَإِلَى ٱلْجِبَالِ كَيْفَ نُصِبَتْ ﴿١٩﴾ وَإِلَى ٱلْأَرْضِ كَيْفَ سُطِحَتْ ﴿٢٠﴾

ቀጥሉ ደግሞ የአላህን ኃይልና ጥበብ ዙሪያውን ባሉት ፍጡራን ሊያስታውሳቸው፣ ለመሆኑ ወደ ግመሏ አይመለከቱምን? እንዴት እንደተፈጠረች (ለጥቅማቸው)? ወደ ሰማይስ አያዩምን? እንዴት ከፍ እንደተደረገች (ከበላያቸው)? ወደ ተራራዎችስ አይመለከቱምን? እንዴት እንደተተከሉ (በዙሪያቸው)? ወደ ምድርስ አይመለከቱምን? እንዴት እንደተዘረጋችላቸው? (ታዲያ እነዚህን ሁሉ የፈጠረው ጌታቸው ሙታንንስ ማንሳት ያዳግተው መሰላቸው ማለቱ ነው ቢገባቸው::)

فَذَكِّرْ إِنَّمَآ أَنتَ مُذَكِّرٌ ﴿٢١﴾ لَّسْتَ عَلَيْهِم بِمُصَيْطِرٍ ﴿٢٢﴾

ይህንም ሁሉ ባያስተውሉ ዝም በልና ገስፃቸው፤ አንተ አስታዋሽ ገሳጭ እንጂ አስገዳጅ ሹም አይደለህም ለሳቸው::

إِلَّا مَن تَوَلَّىٰ وَكَفَرَ ﴿٢٣﴾ فَيُعَذِّبُهُ ٱللَّهُ ٱلْعَذَابَ ٱلْأَكْبَرَ ﴿٢٤﴾

ግን ያን ከተግሳፅ የሸሸና ጭራሽ የካደውን ሰው ኃያሉ አላህ እርሱን ነገ ከባድ ቅጣት በእርግጥ እንደሚቀጣው ነው::

إِنَّ إِلَيْنَا إِيَابَهُمْ ﴿٢٥﴾ ثُمَّ إِنَّ عَلَيْنَا حِسَابَهُم ﴿٢٦﴾

ዝም በላቸው ዞረው ዞረው መመለሻቸው ወደኛው ነው፡፡ ከዚያም በኋላ ምርመራቸው በእኛው ላይ ነው፡፡

ሱረቱል-ፈጅር سورة الفجر

የጎህ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሰላሳ አቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት፡፡ እሷም በአጭሩ ልክ እንደሌሎቹ ሦስት የተለያዩ ጉዳዮችን ታወሳለች፡፡

አንድ፡- የዱሮዎቹን ከሃዲያን ስም በመጥራት ግፍና እስከፊ ውድቀታቸውን ታስታውሳለች፡፡

ሁለት፡- አላህ ሰዎችን በዚህች አጭር ህይወታቸው በመልካምና በመጥፎ ነገሮች ሁሉ እንደሚፈትናቸው በሚገባ ትገልፃለች፡፡

ሦስት፡- ትንሳዔንና ምስቅልቅል መከራዎቿን ታስገነዝበናለች፡፡ ከዚያም ሰዎች የታደሉና ያልታደሉ እየተባሉ ለሁለት ይከፈላሉ፡፡ ከዚያም እንደ ሥራ ውጤታቸው ዋጋቸውን ያገኛሉ ትላለች፡፡

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን፡፡)

وَالْفَجْرِ ﴿١﴾ وَلَيَالٍ عَشْرٍ ﴿٢﴾ وَالشَّفْعِ وَالْوَتْرِ ﴿٣﴾ وَاللَّيْلِ إِذَا يَسْرِ ﴿٤﴾ هَلْ فِي ذَٰلِكَ قَسَمٌ لِذِي حِجْرٍ ﴿٥﴾

በንጋቱ ወጋገንና በአስሮቹ የዙል-ሒጃ ሌሊቶች፣ ጥንድ ነጠላ በሆኑትም ነገሮች፣ ሌሊቱም ሲጓዝ በጨለማው ሽፍኖ ሁሉን ፍጡራን በእነዚህ ሁሉ እምላለሁ!! ጥጋበኛ ከሃዲ ዋለም አደረ መያዙ አይቀርም እላለሁ:: ታዲያ አሁን እዚህ በጠቀስነው በቂ መሃላ አይኖርምን (ጤናማ) አእምሮ ላለው?! (ከአሁን ቀደም ደጋግመን እንዳወሳነው ጌታ የማለው በፈለገው ነገር ሁሉ ነው:: እኛ ግን ልንምል የምንችለው በእርሱ ስሞች ብቻ ነው:: አሁን አላህ በዚህች ምዕራፍ መግቢያ የሚምለው በአምስት ነገሮች ነው:: አንደኛ:- የሌሊትና ቀን መፈራረቂያ ኬላ የሆነው ተዓምራዊው የንጋት ወጋገን ነው:: ሁለተኛ:- በዙል-ሒጃ ወር መግቢያ ላይ የሚገኙት አስሩ ሌሊቶች ናቸው፤ አላህ ከዓመቱ ሌሊቶች ሁሉ አብልጦ የመረጣቸው ታላቁም የሐጅ ተግባር የሚከናወንባቸው::

ለዚህ ነው ነብዩም በበኩላቸው ለአማኝ ተከታዮቻቸው፣ መልካም ሥራዎች በውስጣቸው አላህ ዘንድ እጅግ የሚወደድባቸው፣ ከእነዚህ ቀናት የተሻለ ምንም የለኮ ሲሏቸው፣ ሰሓቦቹ ገርሟቸው «የተፈፀመው ተግባር በአላህ መንገድ መታገል ቢሆንም እንኳ?» ብለው ሲጠይቋቸው «አዎን! እንዲህ ነው፤ ባይሆን ከታጋዮቹ ነፍሱንም፣ ገንዘቡንም ይዞ ዘምቶ ሁሉንም ለአላህ ሰውቶ ምንም ነገር ያልመለሰው ብቻ ሲቀር ነው» አሏቸው:: ሦስተኛና አራተኛ በማድረግ ደግሞ የማለባቸው ጥንድና ነጠላ የተባሉት ነገሮች ናቸው:: እነሱም የተለያየ ትርጓሜ ሲኖራቸው ሁሉንም የሚያካትተው ፈጣሪና ፍጡራን ለማለት ነው የሚለው ነው:: ማለትም ፍፁም ብቸኛ፣ ምንም ቢጤ አንድም ጓደኛ የሌለው አላህ ብቻ ነው:: ሌላው ሁሉ በሙሉ አጣማጅ ቢጤ ያለው ነው:: ቀጥሎ ደግሞ አምስተኛ መማያ ሲሆን የቻለው በአላህ ኃይል ወደ ንጋት እየተገፋ የሚኳትነው የሌሊቱ ክፍለ ጊዜ ነው:: ይህንም ያለው ሁልጊዜ ሌሊቱን ወደ ንጋት የሚነዳው በቀጥታ እርሱ መሆኑን ለመጠቆም ነው:: የማለበትንም ጉዳይ ለማረጋገጥ ታሪካዊ መረጃዎችን ሊጠቅስልን ነው::)

أَلَمْ تَرَ كَيْفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِعَادٍ ﴿٦﴾ إِرَمَ ذَاتِ الْعِمَادِ ﴿٧﴾ الَّتِي لَمْ يُخْلَقْ مِثْلُهَا فِي الْبِلَادِ ﴿٨﴾

በማዝፈት በጉልበታቸው በየትም አገር ወደር ያልተገኘላቸው፣ የረጃጅም ምሰሶዎች ባለቤቶች ኢረም በመባል የሚጠራው ልዩ ብሔረሰባቸው፣ የዐድ ህዝቦች በጥጋባቸው፣ ጌታህ ምን እንዳደረጋቸው አላወቅክም ከታሪካቸው? (በነፋስ ኃይል ጠራርጎ ከምድረ-ገፅ እንዳጠፋቸው)

وَثَمُودَ الَّذِينَ جَابُوا الصَّخْرَ بِالْوَادِ ﴿٩﴾ وَفِرْعَوْنَ ذِي الْأَوْتَادِ ﴿١٠﴾ الَّذِينَ طَغَوْا فِي الْبِلَادِ ﴿١١﴾ فَأَكْثَرُوا فِيهَا الْفَسَادَ ﴿١٢﴾ فَصَبَّ عَلَيْهِمْ رَبُّكَ سَوْطَ عَذَابٍ ﴿١٣﴾ إِنَّ رَبَّكَ لَبِالْمِرْصَادِ ﴿١٤﴾

ሰሙዶችም በተራቸው ዋዲል-ቁራ በተሰኘው ክልላቸው፣ የጎራን ቋጥኝ ቦርቡረው ያደርጉ የነበሩት ቤቶቻቸው፣ የብዙ ችካሎችና ሰራዊቶች ባለቤት የነበረው ፊርዖንም ጠገበና እንደሳቸው፣ እነዚህ ሁሉ በየአገሩ ልክ አልፈው ባልገው ጥፋት በማብዛታቸው፣ ጌታህ የቅጣትን ዓይነት ሁሉ በላያቸው ላይ ለቀቀባቸው፤ (ማለትም ዐዶችን በነፋስ ጠራረጋቸው፤ ሰሙዶችንም በከባድ ጩኸት ዝም አደረጋቸው፤ ፊርዖንና ኃይሎቹንም ባህር ውስጥ ወስዶ ጨመራቸው::) የአንተ ጌታ እኮ በእርግጥ ምንጊዜም ቢሆን ጥጋበኞችን በመጠባበቅ ላይ ነው:: (የሚተዋቸው አይምሰላቸው::)

فَأَمَّا الْإِنسَانُ إِذَا مَا ابْتَلَاهُ رَبُّهُ فَأَكْرَمَهُ وَنَعَّمَهُ فَيَقُولُ رَبِّي أَكْرَمَنِ ﴿١٥﴾

ያማ! ሚስጥሩ ያልገባው የዋሁ ሰው፣ ጌታው ሲያከብረው ማለትም ሲፈትነው በሃብት ሲያቀማጥለው፣ ይመስለውና እሱን ወዶ ያደለው፣ ጌታዬ እኔን አከበረኝ የሚገባኝም ይህ ነው እንደሚል ነው::

وَأَمَّآ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ فَقَدَرَ عَلَيۡهِ رِزۡقَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَهَٰنَنِ ﴿١٦﴾

እሱን ደግሞ ሲሳዩን አጥብቦበት በችግር ሲፈትነው ተስፋ ቢስ ሆኖ በመበሳጨት ጌታዬ እኮ አዋረደኝ ነው የሚለው:: (ነገሩ ግን አልነበረም እርሱ እንደሚለው:: ምክንያቱም አላህ ገንዘብን የሚሰጠው ለወዳጅ ጠላት መለያ ሳይሆን ሁሉንም ባሪያዎቹን ለመፈተን ነው::

كَلَّاۖ بَل لَّا تُكۡرِمُونَ ٱلۡيَتِيمَ ﴿١٧﴾ وَلَا تَحَٰٓضُّونَ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ﴿١٨﴾

وَتَأۡكُلُونَ ٱلتُّرَاثَ أَكۡلٗا لَّمّٗا ﴿١٩﴾ وَتُحِبُّونَ ٱلۡمَالَ

حُبّٗا جَمّٗا ﴿٢٠﴾

ጉዳዩ እንዲህ አይደለም፤ ተሳሳታችሁ! ይልቅ እናንተ ይህ ብቻ ሳይሆን ስህተታችሁ ድሃ አደግ የሙታንን ልጅ የማታከብሩ፣ ሚስኪንንም በማብላት ላይ ሰውን የማታግባቡና የማታስተባብሩ ጨካኞች ናችሁ:: ከዚያም ይባስ ብላችሁ የውርስን ገንዘብ በማምታታት ሰብስባችሁ ትበላላችሁ:: ገንዘብንም እጅግ ሲበዛ (ከልክ አልፋችሁ) ትወዳላችሁ::

كَلَّآ إِذَا دُكَّتِ ٱلۡأَرۡضُ دَكّٗا دَكّٗا ﴿٢١﴾ وَجَآءَ رَبُّكَ وَٱلۡمَلَكُ صَفّٗا

صَفّٗا ﴿٢٢﴾ وَجِاْيٓءَ يَوۡمَئِذِۭ بِجَهَنَّمَۚ يَوۡمَئِذٖ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ وَأَنَّىٰ لَهُ

ٱلذِّكۡرَىٰ ﴿٢٣﴾

ከእነዚህ ዓይነት ባህሪዎቻችሁ ብትርቁ ነው የሚሻላችሁ! አለዚያ አሁን ማስጠንቀቂያውን ካልሰማችሁ (ነገ) ምድር ተናውጣ ከስራቸው መንኮታኮትን ስትንኮታኮትባቸው፣ ጌታህም ይፋ ሲመጣ ፍርደ ውሳኔ ሊሰጣቸው፣ መላዕክትም በሰልፍ በሰልፍ ሲቆሙ ከበዋቸው፣ ጀሃነምም መጥታ ስትቀረብ

አጠገባቸው፣ ያኔ ነው! ተሳላው ሰው እንደ አዲስ የሚባንነው:: ታዲያ ያኔ መገንዘቡ የሚፈይደው ምንድን ነው?

يَقُولُ يَٰلَيْتَنِي قَدَّمْتُ لِحَيَاتِي ﴿٢٤﴾

ያኔ ኪሳራውን በግልፅ ሲያየው ምነው ቀደም ሲል (እያለሁ በጤንነቴ) የሚበጀኝን ባስቀድም ኖሮ! ለዘላቂዋ ህይወቴ፣ ምንኛ ይሳካ ነበር እህን ጊዜ ምኞቴ እንደሚል ነው::

فَيَوْمَئِذٍ لَّا يُعَذِّبُ عَذَابَهُۥٓ أَحَدٌ ﴿٢٥﴾ وَلَا يُوثِقُ وَثَاقَهُۥٓ أَحَدٌ ﴿٢٦﴾

ቢልም ያንጊዜ ፀፀቱ ስለማይጠቅመው አላህ እርሱን እንደሚቀጣው ሊቀጣ የሚችል አንድም ቀጭ ኃይል እንደሌለ ነው:: እርሱንም ጌታ እንደሚያስረው አድርጎ ማሰር የሚችል ማንም ኃይል እንደሌለ ነው::

يَٰٓأَيَّتُهَا ٱلنَّفْسُ ٱلْمُطْمَئِنَّةُ ﴿٢٧﴾ ٱرْجِعِيٓ إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةً مَّرْضِيَّةً ﴿٢٨﴾ فَٱدْخُلِي

فِي عِبَٰدِي ﴿٢٩﴾ وَٱدْخُلِي جَنَّتِي ﴿٣٠﴾

በአንፃሩ ደግሞ ለአማኝቷ ነፍስ ቸሩ ጌታ የሚለው አንቺ በጌታሽ ተስፋ ቃል የተረጋጋሽ የሆንሽው ደጊቷ ነፍስ ሆይ! ዛሬ አትፍሪ! አይዞሽ! በዕድልሽ እየተደሰትሽ፣ እኛ ዘንድ ወዳጅ ተወዳጅም ሆነሽ፣ ወደ ጌታሽ ተመለሽ፤ ከዚያም ከደጋጎቹ ባሪያዎቼ ተቀላቅለሽ ወደ ጀነቴ ግቢ አብረሽ፤ በማለት ነው ዕድሏን የሚወስነው::

ሱረቱል-በለድ سورة البلد

የአንጋፋይቷ አገር ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሃያ አንቀጾች ብቻ ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም እንደ ጓደኞቿ የዕምነት ነጥቦችን በማጠናከር ታተኩራለች::

በተለይም ከሞት በኋላ መነሳት፣ በሠሩት ሥራ መጠየቅና መመንዳት፣ ከዚያም እንደ ውጤቱ ከፊሉ ወደ ጀነት ሌላው ወደ ጀሃነም መነዳቱ እንደማይቀር ትገልጻለች::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም
(እንጀምራለን::)

لَآ أُقۡسِمُ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ١ وَأَنتَ حِلُّۢ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ٢ وَوَالِدٖ وَمَا وَلَدَ ٣ لَقَدۡ خَلَقۡنَا
ٱلۡإِنسَٰنَ فِي كَبَدٍ ٤

በዚህ አገር ማለትም በመካ ክልል አንተ ነዋሪ ሆነህ እያለህ እምላለሁ! (ወይም በሌላ አነጋገር ለአንተኮ በዚህ አገር ክልከል የነበረው ነገር ተፈቀደልህ::) በወላጅና በወለደውም (ማለትም በአደምና በትውልዶቹም) እምላለሁ! ሰውን ወላሂ በእርግጥ ለፋ አድርገን ነው የፈጠርነው እላችኋለሁ:: (ማለትም ማንኛውም ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ዕድሜው ዘወትር በልፋትና በድካም ላይ ነው:: ታዲያ መድከሙ ካልቀረ ልፋቱን በሚበጀው ላይ ቢያደርገውኮ መልካም ነው ማለቱ ነው::)

أَيَحۡسَبُ أَن لَّن يَقۡدِرَ عَلَيۡهِ أَحَدٞ ٥ يَقُولُ أَهۡلَكۡتُ مَالٗا لُّبَدًا ٦

ለመሆኑ ያ! ግብዙ ሰው የሚገምተው እርሱን ሊያሸንፍ የሚችል አንድም ነገር እንደሌለ ነው? ሙሐመድን በመቃወም ብዙን ገንዘብ አወደምኩኝ የሚልም ጅል ነው:: (ይህንም ያለው አቡል-አሹድ የተባለው ጥጋበኛ ነው:: እርሱም አላህ ልዩ ጉልበት ስላደለው እርጥቡን የበሬ ቆዳ ይዘረጋና በሜዳ፣ መሃሉ ላይ ይቆምና እግሮቹን አጠንክሮ እንደ ግድግዳ፣ «አሁን ይህን ቆዳ ስባችሁ ካለሁበት ፈቀቅ ማድረግ የምትችሉ ካላችሁ፣ ከእኔ ልዩ ሽልማት ታገኛላችሁ::» ሲላቸው አስር ጎረምሳዎች ተረባርበው ባለው ሁሉ አቅማቸው

ቢሞክሩም ቆዳው ተበጣጥሶ አለቀ እንጂ በእጃቸው፣ ሰውዬው ምንም ካለበት ፍንክች አላለላቸው:: ለዚህ ነው በአል-ሙደሲር የጀሃነም ዘበኞች አስራ ዘጠኝ መላዕክት ናቸው:: የሚለው አንቀጽ ሲወርድላቸው እናንተ ተረባርባችሁ ሁለቱን ከያዛችሁ እኔ ለአስራ ሰባቱ አለሁላችሁ ያላቸው::)

أَيَحْسَبُ أَن لَّمْ يَرَهُۥٓ أَحَدٌ ﴿٧﴾ أَلَمْ نَجْعَل لَّهُۥ عَيْنَيْنِ ﴿٨﴾ وَلِسَانًا وَشَفَتَيْنِ ﴿٩﴾

وَهَدَيْنَٰهُ ٱلنَّجْدَيْنِ ﴿١٠﴾

ለመሆኑ ይህ ከሃዲ ሰው ኢስላምን ለማደናቀፍ የሚያደርገውን እኩይ እንቅስቃሴ ማንም እንደማያየው ነው የሚያስበው?! እኛ አይደለንምን ለእርሱ ሁለት ዓይኖችንና ምላስን ሁለት ከንፈሮችንም ፈጥረን ያደልነው?! ከዚያም ሁለት መንገዶችን መርተነው በመረጠው እንዲጓዝ ያደረግነው?! (ማለትም ዕምነትና ክህደትን እስከ ውጤቱ አሳወቅነው:: ታዲያ የዚህ ሁሉ ፀጋ አፀፋ ምላሽ መሆን ያለበት ይሄ ነው?!)

فَلَا ٱقْتَحَمَ ٱلْعَقَبَةَ ﴿١١﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا ٱلْعَقَبَةُ ﴿١٢﴾ فَكُّ رَقَبَةٍ ﴿١٣﴾ أَوْ إِطْعَٰمٌ

فِى يَوْمٍ ذِى مَسْغَبَةٍ ﴿١٤﴾ يَتِيمًا ذَا مَقْرَبَةٍ ﴿١٥﴾ أَوْ مِسْكِينًا ذَا مَتْرَبَةٍ ﴿١٦﴾

ይልቅ ያን ሁሉ ጉልበት ንብረት ያለ አግባብ ከሚያባክነው ከባዷን አድካሚ አቀበት ሊወጣበት ያልሞከረው ለምንድን ነው?! ፈታኟ ከባድ አቀበት ምን እንደሆነች ያሳወቀህስ ምንድን ነው? እሷማ በባርነት ሥር ያለችን ነፍስ ነፃ ማውጣት ነው:: ወይም በረሃብ ወቅት የወገንን ድሃ አደግ ልጅ በማደርጎት መመገብ ነው:: ወይም ምንጣፍ አልባ ሆኖ በአፈር ላይ የወደቀውን ችግረኛ መርዳትና መደገፍ ነው:: (ታዲያ ይህ ሁሉ ሰናይ ተግባር እያለ፣ ላፍራሽ ተልዕኮ መሰለፉ ለምንድን ነው ማለቱ ነው::)

ثُمَّ كَانَ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلصَّبْرِ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلْمَرْحَمَةِ ﴿١٧﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلْمَيْمَنَةِ ﴿١٨﴾

ከዚያም ደግሞ ከአማኞቹ አባል ሆኖ በትዕግስት አደራ ከሚባባሉትና በርህራሄ ከሚተባበሩት ቢሆን ነበር ይልቅ ተገቢ የሚሆነው፤ እነዚያኮ ጉበዞች ናቸው፣ የሥራ መዝገባቸውን በቀኝ እጃቸው የሚቀበሉ ዕድለኞች በመሆናቸው፣ የቀኝ ጓዶች የምንላቸው::

وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا هُمْ أَصْحَٰبُ ٱلْمَشْـَٔمَةِ ﴿١٩﴾ عَلَيْهِمْ نَارٌ مُّؤْصَدَةٌۢ ﴿٢٠﴾

እነዚያ አንቀጾቻችንን የካዱት ደግሞ መልዕክቱ ሲደርሳቸው እነርሱ ናቸው የግራ ጓዶች የምንላቸው:: በመሆኑም በእነርሱ ላይ በጥብቅ የምትዘጋው መፈናፈኛ የሌላት ከባዷ እሳት አለችባቸው::

ሱረቱ-ሽምስ سورة الشمس

የፀሐይ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ አምስት አንቀፆች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: አሽምስ የምታተኩረው በሁለት ነጥቦች ላይ ነው:: አንደኛ የሰው ነፍስና የተፈጥሮ ባህሪዋን የተመለከተ ሲሆን፣ ሁለተኛ የክህደትና የበደል ውጤት አደገኛ መሆኑን ለሰዎች ማስገንዘብ ነው::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም
(እንጀምራለን::)

وَٱلشَّمْسِ وَضُحَىٰهَا ﴿١﴾ وَٱلْقَمَرِ إِذَا تَلَىٰهَا ﴿٢﴾

በፀሐይና በደማቁ ብርሃኗ፣ በረፋድ ሰዓት፣ በጨረቃውም እሷን ተከቶ በማብራት ሲከተላት፤

وَٱلنَّهَارِ إِذَا جَلَّىٰهَا ﴿٣﴾ وَٱلَّيْلِ إِذَا يَغْشَىٰهَا ﴿٤﴾

በቀኑም ክፍለ ጊዜ እሷን አጉልቶ ሲገልጻት፣ በሌሊቱም ወቅት በጨለማው ሲሸፍናት፤

وَٱلسَّمَآءِ وَمَا بَنَىٰهَا ﴿٥﴾ وَٱلْأَرْضِ وَمَا طَحَىٰهَا ﴿٦﴾

በሰማይና እሷንም አጠንክሮ በገነባት፣ በምድርም እሷንም አስተካክሎ በዘረጋት፤

وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّىٰهَا ﴿٧﴾ فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَىٰهَا ﴿٨﴾

በነፍስና በአካሏ ውስጥም በሚገባ አስተካክሎ በመደባት፣ ልቅነትና ጥንቁቅነትንም በስሜቷ ያሳወቃት በሆነው ጌታ እምላለሁ::

قَدْ أَفْلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ﴿٩﴾ وَقَدْ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ﴿١٠﴾

በእርግጥ የቀናው ዕድለኛ ነው እርሷን ከመጥፎ ፀባዩ አጥቦ ያፀዳት፣ እሷን ደግሞ ያቆሸሻት በእርግጥ አፈረ ከሰረ እላችኋለሁ::

كَذَّبَتْ ثَمُودُ بِطَغْوَىٰهَآ ﴿١١﴾ إِذِ ٱنۢبَعَثَ أَشْقَىٰهَا ﴿١٢﴾

ሰሙዶች በጥጋባቸው ጥሪያችንን ሀሰት ብለው ሲደርሳቸው፤ ብሉም ከባዱን ወንጀል ሊፈፅም ፈጥኖ ሲነሳ መናጢው አባላቸው:-

فَقَالَ لَهُمْ رَسُولُ ٱللَّهِ نَاقَةَ ٱللَّهِ وَسُقْيَٰهَا ﴿١٣﴾ فَكَذَّبُوهُ فَعَقَرُوهَا

የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ ሳሊሕ ግመሏንና የመጠጥ መብቷን ከመተናኮል ተጠንቀቁ ሲላቸው፣ በማን አለብኝ ስሜት ነብዩን አስተባብለው ግመሏንም ቋንጃዋን ቆርጠው በመግደላቸው:-

فَدَمْدَمَ عَلَيْهِمْ رَبُّهُم بِذَنۢبِهِمْ فَسَوَّىٰهَا ﴿١٤﴾ وَلَا يَخَافُ عُقْبَٰهَا ﴿١٥﴾

ጌታቸው ተቀየመና በወንጀላቸው ሁላቸውንም በጅምላ አወደማቸው:: እርምጃዋንም ማንም ሳይቀር በሁሉም ላይ አስተካከለባቸው:: መዘዟንም ምንም አይፈራ በላቸው (ማለትም ለእነርሱ የሚበቀልላቸው፣ ጥቃትን መላሽ ወይም ደም አፋሽ አይችልምና ሊመጣላቸው::)

ሱረቱ-ለይል سورة الليل

የሌሊት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሃያ አንድ አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም በአጭሩ የምትገልጸው ስለሰው ስለተለያየው ባህሪና ተግባሩ ነው:: ከዚያም ሁሉም ሰው እንደ ዕምነትና እንደ ሥራው ወይ ወደ መጥፎ ወይም ወደ መልካም ውጤት መድረሱ የማይቀር ነው የሚልን መልዕክት እንደምትገልጽልን ነው::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰ ﴿١﴾ وَٱلنَّهَارِ إِذَا تَجَلَّىٰ ﴿٢﴾

በሌሊቱ ልማልላችሁ፤ ሁላችሁንም በጨለማው ሲሸፍናችሁ! በቀኑም እምላለሁ፤ ብርሃኑ ግልጽ ሲሆንላችሁ!!

وَمَا خَلَقَ ٱلذَّكَرَ وَٱلۡأُنثَىٰٓ ﴿٣﴾ إِنَّ سَعۡيَكُمۡ لَشَتَّىٰ ﴿٤﴾

ከዚያም በላይ ወንድና ሴትን በፈጠረው ጌታችሁ ነው የምምልላችሁ፤ በእርግጥ እያንዳንዳችሁ የተለያየ መሆኑን ተግባራችሁ ላረጋግጥላችሁ::

فَأَمَّا مَنۡ أَعۡطَىٰ وَٱتَّقَىٰ ﴿٥﴾ وَصَدَّقَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ﴿٦﴾ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡيُسۡرَىٰ ﴿٧﴾

ያማ! መስጠት ያለበትን ነገር ለአላህ ብሎ የሚችረው፣ ከመጥፎውም ሁሉ የሚጠነቀቀውና ከጌታው ዘንድ መልካም ወረታ እንደሚኖረው ከልብ የሚያምነው፣ ለመልካም ዕድል ወይም ለሰናይ ተግባራት እንደምንገራው ነው::

وَأَمَّا مَنۢ بَخِلَ وَٱسْتَغْنَىٰ ﴿٨﴾ وَكَذَّبَ بِٱلْحُسْنَىٰ ﴿٩﴾ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلْعُسْرَىٰ ﴿١٠﴾

ያማ! መስጠት ያለበትን የነፈገና ከጌታም ፀጋ የተብቃቃው፣ ውቢቷን ጀነትና ፍስሃዋንም ያስተባበለው ለከባድ ችግር እንደምንዳርገው ነው::

وَمَا يُغْنِى عَنْهُ مَالُهُۥٓ إِذَا تَرَدَّىٰٓ ﴿١١﴾

እርሱም ነገ በእሳት ጉድጓድ ውስጥ ተገፍትሮ ሲምዘገዘግ ንብረት ገንዘቡ ምንድን ነው የሚጠቅመው? ምንም ሊጠቅመው እንደማይችል ነው::

إِنَّ عَلَيْنَا لَلْهُدَىٰ ﴿١٢﴾

ቀናውን መንገድ በማመልከት መመራት በእኛ ላይ ተገቢ ነው:: (ስለዚህም ነው ነብያት የምንልክና መጽሐፍንም የምናወርደው የሆንነው::)

وَإِنَّ لَنَا لَلْءَاخِرَةَ وَٱلْأُولَىٰ ﴿١٣﴾

በመጨረሻዋም ሆነ በመጀመሪያዋ ዓለም የሚገኘው ፀጋ ሁሉ በእርግጥ የእኛ ብቻ ነው:: (ስለዚህ እኔን ችላ ብሎ ሌላን ደጅ መጥናት ከንቱ ነው ማለቱ ነው::)

فَأَنذَرْتُكُمْ نَارًا تَلَظَّىٰ ﴿١٤﴾ لَا يَصْلَىٰهَآ إِلَّا ٱلْأَشْقَى ﴿١٥﴾ ٱلَّذِى كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰ ﴿١٦﴾

(እሁንም ታዲያ የምላችሁን የማትሰሙ ከሆናችሁ!) ተንቀልቃይቷን እሳት ነው የማስጠነቅቃችሁ በላቸው:: እሷኮ ውስጥ የሚማገደው ያ! ነብዩን አስተባብሎ ከሐቅ እርቆ የሄደው መናጢ እንጂ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ነው::

وَسَيُجَنَّبُهَا ٱلۡأَتۡقَى ﴿١٧﴾ ٱلَّذِي يُؤۡتِي مَالَهُۥ يَتَزَكَّىٰ ﴿١٨﴾

ያ! ደግሞ ነፍሱን ለማፅዳት ገንዘቡን ለምፅዋት የሚለግሰው ነገ ከእሷ እንደሚጠበቅ ነው::

وَمَا لِأَحَدٍ عِندَهُۥ مِن نِّعۡمَةٖ تُجۡزَىٰٓ ﴿١٩﴾ إِلَّا ٱبۡتِغَآءَ وَجۡهِ رَبِّهِ ٱلۡأَعۡلَىٰ ﴿٢٠﴾

وَلَسَوۡفَ يَرۡضَىٰ ﴿٢١﴾

አቡበክርኮ ለማንም ሰው በእርሱ ዘንዳ፣ ምንም ውለታ የለበት የሚመነዳ:: እርሱ ግን ይህንን ያደረገው የላቀውን የጌታውን ፊት በመሻት ነው:: እርሱም ወላሂ ነገ በሥራ ውጤቱ በእርግጥ እንደሚረካ ነው:: (ይህንም ያለው አቡበክር ቢላልን ገዝተው ነፃ ሲያደርጉት ከሃዲያን ጠላቶቻቸው እሱኮ ይህን ሊያደርግ የቻለው ቀዳሚ ውለታ ስላለበት ነው ብለው ስለተቹ ነው::)

ሱረቱ-ዱሓ سورة الضحى

የረፋዷ ሰዓት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ አንድ አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷ በተለይ የምታተኩረው በነብዩ የግል ህይወት ላይ ነው:: ምንም እርሳቸው መጀመሪያ ላይ የተለያዩ ችግሮችም ቢገጥሟቸው፣ ወደ ኋላ እየቆየ ግን ቸሩ ጌታቸው ሁሉንም ነገር እንደሚያስተካክልላቸው ነው በዚህች ምዕራፍ ግልጽ ያደረገላቸው::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَٱلضُّحَىٰ ﴿١﴾ وَٱلَّيۡلِ إِذَا سَجَىٰ ﴿٢﴾

በረፋድ ሰዓት ብርሃኑ ጎልቶ ሲደምቅ፣ በሌሊቱም ጨለማው ተነባብሮ ሲደቀደቅ እምልባቸዋለሁ!!

مَا وَدَّعَكَ رَبُّكَ وَمَا قَلَىٰ ۝٣

ጠላቶችህ እንደሚሉህ አንተን ጌታህ አልተወህም፤ አልጠላህም፤ አልሃለሁ (ይህንም ያለው ነብዩ ሁለት ሦስት ቀናት አማሟቸው፣ በሌሊት ስግደት ቁርአን ሲያነቡ ስላልሰማች መጥፎዋ ጎረቤታቸው፣ መጣችና እስከቤታቸው «ሰሞኑን ሰይጣንህ ጠልቶ የተወህ ይመስለኛል፤ እንደማይመለስብህም ተስፋዬ ነው::» ስትላቸው አላህ ይህንን በማውረድ ግልጽ መልስ ሰጠላቸው::)

وَلَلْآخِرَةُ خَيْرٌ لَّكَ مِنَ الْأُولَىٰ ۝٤

የመጨረሻዋም ዕድል ከመጀመሪያዋ ይልቅ ለአንተ እጅግ የተሻለች ናት ማለትንም ነገራቸው::

وَلَسَوْفَ يُعْطِيكَ رَبُّكَ فَتَرْضَىٰ ۝٥

ያኔ ወላሂ የአንተ ጌታ በእርግጥ ይሰጥህና ልዩ ስጦታ፣ እንደምትረካ ነው ባገኘኸው ችሮታ::

أَلَمْ يَجِدْكَ يَتِيمًا فَآوَىٰ ۝٦ وَوَجَدَكَ ضَالًّا فَهَدَىٰ ۝٧ وَوَجَدَكَ

عَائِلًا فَأَغْنَىٰ ۝٨

ባለፈውም ታሪክህ አንተን እንደማይጠላና እንደማይጥልህ፣ የሟች ልጅ (የቲም) ሆነህ አግኝቶህ አላስጠጋህምን ዋቢ ወደ ሆነልህ አጎትህ?! በልጅነትህስ ሰፈርህ ጠፍቶህ ስትባዝን አግኝቶህ መርቶሃል አይደል ወደ ቤትህ?! ችግረኛስ ሆነህ አግኝቶህ አበልፅገንሃል አይደል በመንፈሳዊና በተወሰነው ንብረትህ?! ስለዚህ ከአሁን በኋላም አይደለንም የምንጥልህ፤ አለና እንዳለውም አደረገላቸው::

فَأَمَّا ٱلۡيَتِيمَ فَلَا تَقۡهَرۡ ﴿٩﴾ وَأَمَّا ٱلسَّآئِلَ فَلَا تَنۡهَرۡ ﴿١٠﴾

አንተም ደግሞ በበኩልህ የሙት ልጅን እንዳትጨቁን! ለማኙንም እንዳትገለምጥ ነው የምልህ።

وَأَمَّا بِنِعۡمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّثۡ ﴿١١﴾

ጌታህ የቸረህንም መልካም ነገር ለጉራ ሳይሆን ለማመስገን ስትል ግልጹን ተናገር አላቸው።

ሱረቱ-ሽርሕ سورة الشرح

የደረት ስፋት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ስምንት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት። እሷም እንደ (ወዱሐ) በነብዩ ጉዳይ ላይ ታተኩራለች። የአላህ መልዕክተኛ ሥራቸውን ሲጀምሩ ምንም ጠላቶቻቸው ቢያበሳጯቸው፣ ቸሩ ጌታቸው እንደሚንከባከባቸው፣ ደረጃቸውንም ከፍ እንደሚያደርግላቸው፣ ችግራቸውንም በማስወገድ የተሻለ ዕድል እንደሚያመጣላቸው አበሰራቸው። (እንዳለውም አደረገ፤ ሁሉም ነገር ምንም ሳይቀር ተሳካላቸው።)

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

أَلَمۡ نَشۡرَحۡ لَكَ صَدۡرَكَ ﴿١﴾ وَوَضَعۡنَا عَنكَ وِزۡرَكَ ﴿٢﴾ ٱلَّذِيٓ أَنقَضَ ظَهۡرَكَ ﴿٣﴾ وَرَفَعۡنَا لَكَ ذِكۡرَكَ ﴿٤﴾

(አላህ ቸሩ ጌታቸው ለነብዩ ውለታውን ሲያስታውሳቸው) ደረትህን አላሰፋንልህምን?! ያን

ጀርባህን የለመጠውን ሸክምህንስ አውርደንልሃል አይደለምን?! ዝናህንስ ከፍ አድርገንልሃል አይደለምን?! አላቸው። (ደረትህን አላሰፋንልህምን የሚለው ሁለት ትርጉም ሲኖረው አንደኛ:- በፍፁም ዕምነትና በነብይነት እንዲሁም በቁርአንና በጠቃሚ እውቀት ሞላነው ለማለት ነው። ሁለተኛ:- በህፃንነታቸው መላዕክት ከልጆች መሃል ያዝ አድርገው አስተኙና ደረታቸውን ቀደው፣ አልቅት የመሰለ ነገር ጣሉ አውጥተው፣ ከዚያም በወርቅ ሰሃን ላይ አድርገው፣ በዘምዘም ውሃ አጥበው አፅድተው ወደ ቦታው መልሰው በማስገባት አሸጉላቸው። አሁን ታዲያ እንዲህ የሚለው ያን ለመጥቀስ ነው የሚሉት ብዙ ናቸው። ጀርባህን የለመጠውን ሸክም የሚለው ደግሞ አንደኛ:- ስህተት እንኳን ቢያጋጥምህ አያስጨንቅህ፤ ይቅር ነው የምንልህ ለማለት ነው። ሁለተኛ:- የሚያሳስብህን ነገር ሁሉ በቀላል ነው የምንገላግልህ ለማለት ነው። ዝናህን ከፍ አደረግንልህ የሚለው ደግሞ ገና ሳትመጣ በትንቢት ለዓለም አሳወቅንህ፤ ከመጣህም በኋላ ከሁሉም በላይ አላቅንህ። ስለዚህም ነው (በአዛን በኢቃማ በተህያም) ፀሎት ጭምር ስማቸውን ከስሙ ጋር እንዲወደስ ያደረገው።)

فَإِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرًا ۝٥ إِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرًا ۝٦

ከጭንቅ ጎን እኮ በእርግጥ ደግ ነገርም እንደሚኖር ነው። እርግጥም ከጭንቅ ጋር መገላገልም ያለ ነው (ስለዚህ ለማንም ሰው ተገቢ የሚሆነው መጥፎ ሲገጥመው በመታገስ መልካሙን ተስፋ ማድረግ ነው ማለቱ ነው።)

فَإِذَا فَرَغۡتَ فَٱنصَبۡ ۝٧ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَٱرۡغَب ۝٨

አንድን *ሥራ* ስታጠናቅቅ ሌላውን ደግሞ በመጀመር መባተል እንዳለብህ ነው። የምትመኘውን ዕድል ለማግኘ ት መጓጓት ያለብህም ወደ ጌታህ ብቻ ነው። (ማለትም ሃሳብህ እንዲሳካ ተስፋ መጣል ያለብህ በሌላ ነገር ሳይሆን በጌታህ ላይ ነው ማለቱ ነው።)

ሱረቱ-ቲን سـورة التيـن

የቲን ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ስምንት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም የምትዳስሰው ሁለት ቁም ነገሮችን ነው:: አንደኛ:- አላህ ሰውን በልዩ ቅርፅ በመፍጠር እንዳከበረው ማስታወስ ሲሆን፣ ሁለተኛ:- ከሞት ተነስቶ በሠሩት ሥራ መመንዳት ማንም ሊክደው የማይገባው መሆኑን ነው::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَٱلتِّينِ وَٱلزَّيْتُونِ ﴿١﴾ وَطُورِ سِينِينَ ﴿٢﴾ وَهَٰذَا ٱلْبَلَدِ ٱلْأَمِينِ ﴿٣﴾

በቲን እና በዘይቱን ተክሎች፣ በተባረከውም የጡሪ ሲና ተራራና ሙሉ ፀጥታ በሰፈነበት በዚህም አገር እምላለሁ!!! (አላህ እዚህ ላይ የማለው በሁለቱ ጠቃሚ ምርጥ የሆኑ ተክሎችና እንዲሁም በሁለቱ የተቀደሱ ክልሎች (ማለትም) በሲና ተራራና በመካ ከተማ ነው::)

لَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ فِىٓ أَحْسَنِ تَقْوِيمٍ ﴿٤﴾ ثُمَّ رَدَدْنَٰهُ أَسْفَلَ سَٰفِلِينَ ﴿٥﴾

ወላሂ ሰውን እኮ የፈጠርነው እጅግ ሸጋ በሆነ ተክልና ገፅታ ነው:: ከዚያም በገዛ ፀባዩ (ሲወሳለት ስላገኘነው) ከወራዶቹ ሁሉ በታች አድርገን መለስነው፤ በጌታው ሲክድ ሲያጋራ ስላገኘነው ማለቱ ነው::

إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَلَهُمْ أَجْرٌ غَيْرُ مَمْنُونٍ ﴿٦﴾

ግን እነዚያ ያመኑትና መልካም ተግባራትን የሠሩት ለጌታቸው፣ ለእነርሱ መቼም የማይቋረጥ ዘላለማዊ ምንዳ አላቸው::

فَمَا يُكَذِّبُكَ بَعْدُ بِالدِّينِ ﴿٧﴾

(የሰው ልጅ ሆይ! ይኸው ሐቁን እንደዚህ እየነገርኩህ ነው፡፡) ታዲያ ደግሞ ከአሁን ወዲያ የፍርዱን ቀን እንድታስተባብል የሚያደርግህ ምንድን ነው?

أَلَيْسَ اللَّهُ بِأَحْكَمِ الْحَاكِمِينَ ﴿٨﴾

አላህ ከፈራጆች ሁሉ የበለጠ አስተካካይ ፈራጅ አይደለምን?! ታዲያ ለምንድን ነው በላቸው፣ ፍጡራንን ከሞት በኋላ አስነስቶ ከመቃብሮቻቸው የማይጠይቅና የማይመነዳቸው በሥራቸው?!!

ሱረቱል-ዐለቅ سورة العلق

የአልቅታማዋ ደም ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ ዘጠኝ አንቀጾችን የያዘች አጭር ምዕራፍ ናት፡፡ እሷም በሚከተሉት ሦስት ነገሮች ታተኩራለች፡፡

አንደኛ:- ለመጀመሪያ ጊዜ በመደምደሚያው መልዕክተኛ በነብዩ መሀመድ ላይ የአላህ ራዕይ መውረዱን ታበስራለች፡፡

ሁለተኛ:- ማንኛውም ሰው በዛ ያለ ገንዘብ ሲኖረው በሌሎች ላይ ጫና ማድረጉ የማይቀር ነው ማለትን ትጠቁማለች፡፡

ሦስተኛ:- የመናጢውን ምቀኛ የአቡጀህልን ዕኩይ ተግባር ታወሳለች፡፡ በዚህች ምዕራፍ ከአንድ እስከ አምስት ቁጥር ድረስ ያሉት አንቀጾች በመደዳቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በነብዩ ላይ የወረዱላቸው ናቸው፡፡

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም
(እንጀምራለን::)

ٱقْرَأْ بِٱسْمِ رَبِّكَ ٱلَّذِى خَلَقَ ﴿١﴾ خَلَقَ ٱلْإِنسَٰنَ مِنْ عَلَقٍ ﴿٢﴾

(ኃያሉ አላህ ለመጀመሪያ ጊዜ ለነብዩ መለኮታዊ መመሪያውን ሲያወርድላቸው):- ሁሉን ነገር ካልነበረ ያስገኘ፣ በተለይ የሰውን ልጅ ከረጋ ደም የፈጠረ በሆነው ጌታህ ስም ጀምርና መልዕክቱን አንብብ! አላቸው::

ٱقْرَأْ وَرَبُّكَ ٱلْأَكْرَمُ ﴿٣﴾ ٱلَّذِى عَلَّمَ بِٱلْقَلَمِ ﴿٤﴾ عَلَّمَ ٱلْإِنسَٰنَ مَا لَمْ يَعْلَمْ ﴿٥﴾

አሁንም አንብብ (ምንም ልምድ እንኳ ባይኖርህ ግር አይበልህ)! ጌታህ ከሁሉም በላይ ቸር ነውና (ይህንን ቢያድልህ አያስገርምህ)! እርሱኮ ነው ያ! የሰውን ልጅ በቀለም መፃፍ ያስተማረው! በአጠቃላይም ማንም ሰው የማያውቅ የነበረውን ያሳወቀው:: (በማለት ቸሩ ጌታቸው የመጨረሻው ነብይ እንዳደረጋቸው ነገራቸው:: ይህም የሆነው ዕድሜያቸው አርባ እንደሞላ ከሰዎች ርቀው ገለልተኝነት ስላማራቸው፣ በሒራ ዋሻ ውስጥ እያሉ ለብቻቸው፣ መልዓኩ ጂብሪል ዱብ አለና ፊት ለፊታቸው «አንብብ!» ሲላቸው በመደናገጥ «እኔኮ አንባቢ አይደለሁም!» ቢሉትም የሚተዋቸው መስሏቸው፣ ጭራሽ በኃይል ያዝ አደረገና እቅፍ አድርጎ አስጨነቃቸው:: አሁንም ለቀቀና እንደገና መልሶ «አንብብ!» ሲላቸው፣ አሁንም ደግመው «እኔኮ ማንበብ አልችልም!» ሆን መልሳቸው፤ ያኔ! እርሱም በድጋሚ እቅፍ አድርጎ ጨመቃቸው፤ አሁንም ለቀቀና «በል እንግዲህ! በጌታህ ስም ጀምርና እኔ የምለውን ተከትለህ ታነባለህ!» አላቸው:: ቀጥሉም እነዚህን አምስት አንቀጾች አስነበባቸው:: ከዚያ ተመልሰው መጥተው

ተከናንበው እንደተኙ በቤታቸው፣ እስከ ቤት ድረስ መጣና አዲሱ ደንበኛቸው፣ «አንተ ተከናናቢው ሆይ! የመተኛ ጊዜ አይደለም ተነስ! አስጠንቅቅ!» በማለት ዓለም አቀፉን ግዙፍ ሥራ አስጀመራቸው:: ስለዚህ ቁርአን መውረድ የጀመረው በእነዚህ አምስት አንቀጾች ነው::)

كَلَّآ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لَيَطْغَىٰٓ ﴿٦﴾ أَن رَّءَاهُ ٱسْتَغْنَىٰٓ ﴿٧﴾ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجْعَىٰٓ ﴿٨﴾

(ያኔ የአካባቢው ሹምና ባለፀጋ አቡጀህል የጎሪጥ ማየት ሲጀምራቸው)፣ እውነቱን ልንገራችሁ ሰውኮ በእርግጥ ገንዘብ በዛ ብሎለት ካየ፣ በጥጋብ ስሜት ድንበርን ያልፋል (ነው የምላችሁ):: አየህን አንተ ጥጋበኛው ሰው? የሁሉም መመለሻ በእርግጥ ወደ ጌታህ ነው:: (ስለዚህ የሚሻለው ይልቅ ብትጠነቀቅ ነው::)

أَرَءَيْتَ ٱلَّذِى يَنْهَىٰ ﴿٩﴾ عَبْدًا إِذَا صَلَّىٰٓ ﴿١٠﴾ أَرَءَيْتَ إِن كَانَ عَلَى ٱلْهُدَىٰٓ ﴿١١﴾ أَوْ أَمَرَ بِٱلتَّقْوَىٰٓ ﴿١٢﴾

ለመሆኑ ያን ባሪያ ለጌታው በሚሰግድበት ወቅት ጣልቃ በመግባት የሚከለክለውን መጥፎ ግለሰብ አየኸውን?! እስኪ ንገረኝ ያ! ስግደት የሚከለከለው ሰው በትክክለኛ ው መስመር ላይ ከሆነ የሚጓዘው፣ ወገኖቹንም ከክህደት ከማጋራት ተጠንቀቁ እያለ ከሆነ የሚመክርና የሚያዘው፤ ይህን ዓይነት ሰው እንዳይሰግድና እንዳይመክርም መከልከልህ ተገቢ ነው?

أَرَءَيْتَ إِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰٓ ﴿١٣﴾ أَلَمْ يَعْلَم بِأَنَّ ٱللَّهَ يَرَىٰ ﴿١٤﴾

አየህን ሙሐመድ ይሄ ጥጋበኛ የሆነው ሰው አንተን ካስተባበለና ከዕምነት ከሸሸ ስትመክረው፣ አላህ የሚሠራውን የማያውቅበት መሰለው? (ይህን እንደሆነ የገመተው፣ እጅግ በጣም ነው የተሳሳተው::)

كَلَّا لَئِن لَّمْ يَنتَهِ لَنَسْفَعًۢا بِٱلنَّاصِيَةِ ﴿١٥﴾ نَاصِيَةٍ كَٰذِبَةٍ خَاطِئَةٍ ﴿١٦﴾

ይልቅ ይህን ትዕቢቱን ካሁኑ ይተው፤ አለበለዚያ ከዚህ ነገር ካልተቆጠበ እናቱን ፈጥርቀን ይዘን እንዳናፈርጠው:: ያችን ውሸታም ኃጢያተኛ የሆነች ጭንቅላት በኃይል አጥብቀን በመያዝ እንደምንከሰክሳት ነው ማለቱ ነው::

فَلْيَدْعُ نَادِيَهُۥ ﴿١٧﴾ سَنَدْعُ ٱلزَّبَانِيَةَ ﴿١٨﴾

ከፈለገም እንዳለው የሸንጎ ባልደረቦቹን ይጥራቸው:: እኛ ም ያኔ ልዩዎቹ ዘበኞችን ይሆናል የምንጠራቸው::

كَلَّا لَا تُطِعْهُ وَٱسْجُدْ وَٱقْتَرِب ۩ ﴿١٩﴾

አዎን አሁኒም ይህ ጥጋበኛ ከዕኩይ ተግባሩ ቢታረም ነው የሚሻለው:: አንተ ከእንግዲህ በኋላ እርሱ የሚለውን አትቀበለው ዝም ብለህ ስገድ ወደ እኛ ብቻ ተቃረብ፤ እርሱ ዛቻውን ሊፈፅም እንደማይችል ነው:: (ይህም የሆነው ነብዩ ሥራቸውን ሲጀምሩ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው የነበረው፣ የግል ስግደት በማብዛት ወደ ጌታቸው መቃረብ እንደነበር ነው:: በዚያም መሠረት አቡጀህል የተባለው አንጋፋው ጠላታቸው «ሙሐመድ ከአሁን በኋላ በካዕባ አካባቢ መጥተህ በአሻዋ ላይ መደፋትህን ታቆማለህ! አለበለዚያ የማደርገውን ታያለህ!» ብሎም ቢያስጠነቅቃቸው እሳቸው ግን ማስጠንቀቂያውን ችላ ብለው፣ ~~በስግደታቸው~~ ቀጠሉ በስግደታቸው ልክ እንደልማዳቸው:: ያኔ ለአሽከሮቹ እንዲያስቆሟቸው ትዕዛዝም ቢሰጣቸው፣ መጋፈጥ አልፈለጉም ዝም አሉ እንጂ እንዳላዩዋቸው፤ ያኔ አቡጀህል ማስጠንቀቂያው ሳይታፈር ትዕዛዙም ሳይከበር መቅረቱ ስላሳረረው፣ እራሱ ሄዶ እርምጃ መውሰድ አማረው:: በዚያም መሠረት እርሳቸው መሬት ላይ እንደተደፉ በግንባራቸው፣ አንገታቸው ላይ በመቆም አሸዋ ሊያቅማቸው ተንደርድሮ ወረደና ቀረብ እንዳለ አጠገባቸው፣ በቅፅበት ድንግጥ አለና ከአደጋ ሊያመልጥ እንደሚርበተበተው ሰው በደመ ነፍስ ወደ ኋላ በመቀልበስ እጁን እያውለበለበ ዱላ እንደሚከላከል ሰው

ተፍገምግሞ ሲመለስ በማየታቸው፣ ጓደኞቹ እንደደረሰ አጠገባቸው፣ ሁኔታው አስገርሟቸው «ምን ሆንክ?» ሲሉት ያየውን እንዲነግራቸው፣ «አጠገቡ እንደደረስኩኝ በእኔና በእርሱ መካከል በእሳት የተሞላ ጉድጓድ ተከፈተብኝ:: ወደ ላይ ቀጥ ስል ደግሞ ግመል የመሰለ እንስሳ አፉን ከፍቶ ሲውጠኝ በላዩ ላይ አንዣበበብኝ» አላቸው:: እነርሱ ግን ሳቁበት የሚያወራው የቁም ቅዠት መስሏቸው::)

ሱረቱል-ቀድር سورة القدر

የታላቋ ሌሊት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አምስት አንቀጾች የያዘች አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም በአጭሩ የምትገልጸው ቁርአን መወረድ የተጀመረባትን በደረጃዋም ከብዙ ወራት የምትልቀውን አንጋፋይቷን ሌሊት ነው::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

إِنَّآ أَنزَلْنَٰهُ فِى لَيْلَةِ ٱلْقَدْرِ ۝١ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا لَيْلَةُ ٱلْقَدْرِ ۝٢

እኛኮ ነን በዕውነት ይህን ቁርአን በመወሰኛይቱ ታላቋ ሌሊት ያወረድነው:: ታላቋ ሌሊት የምትባለው ምን ያህል ታላቅ እንደሆነችስ ያሳወቀህ ምንድን ነው?! (እኛ ካልነገርንህኮ) የእሷን ደረጃ ማወቅ እንደማትችል ነው ማለቱ ነው:: (እዚህ ላይ ቁርአንን በታላቋ ሌሊት አወረድነው የሚለው ሁለት ትርጉም ሲኖረው አንደኛ:- የመጀመሪያው ክፍለ ቁርአን ነብዩ ዘንድ የደረሰበት ለማለት ነው:: ሁለተኛ:- ሙሉ በሙሉ ከጥብቁ ሰሌዳ ኮፒ ተደርጎ በታችኛዋ ሰማይ በይተል-ዒዛ በተሰኘው ልዩ ቦታ በመውረድ ያረፈበት ለማለት ነው::)

لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ خَيۡرٞ مِّنۡ أَلۡفِ شَهۡرٖ ﴿٣﴾

ታላቋ ሌሊት እኮ ደረጃዋ ከሺህ ወራት የላቀ ነው:: (ማለትም እሷ በሌለችባቸው ሺህ ወራት ውስጥ ከሚሰራው ዒባዳ በዚያች ሌሊት ቆሞ ያደረው ሰው ምንዳ የላቀ ነው ማለቱ ነው::)

تَنَزَّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ فِيهَا بِإِذۡنِ رَبِّهِم مِّن كُلِّ أَمۡرٖ ﴿٤﴾

በዚያች ሌሊት የመላዕክት ህዝቦችና ጂብሪልም አለቃቸው፣ ወደ ምድር ይወርዳሉ ውሳኔ ትዕዛዝን ሁሉ በመያዝ ከጌታቸው፣ ለጉብኝት ልዩ ፈቃድ ተሰጧቸው በላቸው::

سَلَٰمٌ هِيَ حَتَّىٰ مَطۡلَعِ ٱلۡفَجۡرِ ﴿٥﴾

እሷኮ ሰላም የሰፈነባት ልዩ ሌሊት ናት፤ ጎህ እስከሚወጣ ድረስ መጥፎ ነገር የሌለባት በላቸው:: (ይህም የሆነው አላህ ለረሱል ካለፉት ወዳጆቹ ገድል ሲገልጽላቸው ለሺህ ወራት ያለማቋረጥ ሌሊት እየቆመ፣ ቀን እየፆመ፣ በዚያም ላይ ትጥቁን ሳይፈታ ጠላቶቹን የተፋለመ እንደነበረ ሲነግራቸው፣ ጀግናው በፈፀመው ጀብዱ ቅናት ስለተሰማቸው የእኔማ ህዝቦች ዕድሜያቸው አጭር አቅመ ደካማዎች ናቸው:: ታዲያ እንዴት ነው የሚችሉት እነዚያን ሊወዳደሯቸው? በማለታቸው ቸሩ ጌታቸው ይህችን ሌሊት ሰጥተንሃል:: እሷን ቆሞ ያደረ ሰው በደረጃው ሺህ ወራት ከሠራው ሰው የበለጠ ነው በማለት አስደሰታቸው:: ስለዚህም ነው እርሳቸው ለህዝቦቻቸው «ይህች ሌሊት መኖሯን አምኖ ተስፋ በማድረግ የቆማት ሰው ያለፈው ወንጀሉ ሁሉ እንደሚማርለት ነው» ማለታቸው:: ጊዜዋንም በሚመለከት «በረመዳን መጨረሻ አስርት ቀናት በነጠላ ሌሊቶች ውስጥ ተከታተሏት::» ማለታቸው የታወቀ ነው::)

ሱረቱል-ብይና سورة البينة

የግልጽ መረጃ ምዕራፍ በመዲና የወረደች፣ ስምንት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት። እሷም በአጭሩ የሚከተሉትን ሦስት ጉዳዮች ትዳስሳለች:-

አንደኛ:- የቀድሞ መጽሐፍት ባልተቤቶች ስለነብዩ ሙሐመድ የነበራቸውን አቋም ትገልፃለች።

ሁለተኛ:- አምልኮን ለአላህ ፍፁም ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን እጅግ ታሰምርበታለች።

ሦስተኛ:- የዕድለኞችና የዕድለ ቢሶች መጨረሻ ምን እንደሚሆን በግልፅ ታረጋግጥልናለች።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

لَمْ يَكُنِ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ وَٱلْمُشْرِكِينَ مُنفَكِّينَ حَتَّىٰ تَأْتِيَهُمُ ٱلْبَيِّنَةُ ﴿١﴾

እነዚያ ከቀድሞ መጽሐፍ ባለቤቶች የሆኑት ከሃዲያን እነዚያም አጋሪዎች የነበሩት በጌታቸው ግልፁ መረጃ እስከሚመጣላቸው፣ የሚላቀቁ አልነበሩም ከቆዩበት አቋማቸው። (ማለትም የሁዶችም ሆኑ ክርስቲያኖች በጣዖትና በተለያዩም ነገሮች የሚያምኑ የነበሩት አጋሪዎች በየፊናቸው በሐቅ ላይ ነን መስሏቸው፣ ከዚያ የመውጣት ምንም ሃሳብ አልነበራቸው።)

رَسُولٌ مِّنَ ٱللَّهِ يَتْلُوا۟ صُحُفًا مُّطَهَّرَةً ﴿٢﴾ فِيهَا كُتُبٌ قَيِّمَةٌ ﴿٣﴾

ግልጽ መረጃም የተባለው እንከን አልባውን ንፁህ መጽሐፍ እያነበበ የሚያስረዳቸው የሆነው የአላህ መልዕክተኛ ነው:: በዚያም መጽሐፍ ውስጥ ቀጥተኛ ውሳኔዎች ፍትሃዊ-ድንጋጌዎች ያሉበት ነው::

وَمَا تَفَرَّقَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ إِلَّا مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَتْهُمُ ٱلْبَيِّنَةُ ﴿٤﴾

እነዚያ መጽሐፍ የተሰጡት እኮ በጊዜያቸው፣ የተለያዩ አልነበሩም በአቋማቸው፤ በአንተ ተልዕኮ ሐቀኝነት በቂ መረጃ ከመጣላቸው በኋላ እንጂ በትንብዩ እንደተነገራቸው ቀድሞ ከነብዮቻቸው:: (ማለትም መደምደሚያው ነብይ ይመጣልኝ እንጂ እንከተለዋለን ሲሉ ቆይተው፣ ሲመጣ ግን የእነሱ ጐሳ ባለመሆኑ ተቆጥተው አስተባብለውት አረፉ ቃል ኪዳናቸውን በልተው:: ስለዚህ ዕውነቱ የት እንዳለ ሳይጠፋቸው፣ ምቀኝነት ነው ለክህደት የዳረጋቸው ማለቱ ነው ሚስጥር አዋቂው ጌታቸው::)

وَمَآ أُمِرُوٓا۟ إِلَّا لِيَعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤْتُوا۟ ٱلزَّكَوٰةَ ۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلْقَيِّمَةِ ﴿٥﴾

(እነርሱም እኮ እንደ እናንተው በቀዳሚው መጽሐፋቸው) ኃይማኖትን ለእርሱ ብቻ በማድረግ አላህን እንዲገዙ እንጂ ፍፁም ቀጥ ያሉ ሲሆኑ በአቋማቸው ሌላ ያልታዘዙ ናቸው:: በተለይ ስግደትን ደንቧን አሟልተው እንዲያዘወትሩና ግዴታ ምፅዋትንም እንዲቸሩ ነው ለሚገባቸው ወገኖቻቸው:: ይህም ቀደም ሲል ለእነርሱ የተነገረው ይኸው አሁንም የቀጥተኛው ኃይማኖት የኢስላም ደንብና ቋሚ መርሆ ነው:: (ማለትም እነዚህ ሶስት ተግባራት መሠረታዊ ጉዳዮች በመሆናቸው በሁሉም ነብያት የታወቁና የታወጁ ያልተሻሩ ያልተቀየሩ ደንቦች ናቸው ማለቱ ነው::)

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ وَٱلْمُشْرِكِينَ فِي نَارِ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ

فِيهَآ أُوْلَٰٓئِكَ هُمْ شَرُّ ٱلْبَرِيَّةِ ﴿٦﴾

እነዚያ ከመጽሐፉ ባለቤቶች እያወቁ የካዱትና እነዚያም ደግሞ አጋሪዎች የሆኑት በጌታቸው፣ ካልተመለሱ ከስህተታቸው በእርግጥ በጀሃነም ውስጥ ናቸው:: ያውም በእሷ ዘውታሪዎች ሲሆኑ እስከ መጨረሻቸው:: እነሱኮ በአቋማቸው ከሁሉም ፍጡር የከፉ መናጢ ሰዎች ናቸው፤ የአዋቂ አጥፊዎች በመሆናቸው::

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمْ خَيْرُ ٱلْبَرِيَّةِ ﴿٧﴾

በአንጻሩ ደግሞ እነዚያ ያመኑትና መልካም ሥራዎችን ያከናወኑት (ጌታቸው እንዳዘዛቸው) እነርሱ በእርግጥ ከፍጡራኑ ሁሉ የተሻሉ ምርጦች ናቸው::

جَزَآؤُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ جَنَّٰتُ عَدْنٍ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًا

رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُواْ عَنْهُ ذَٰلِكَ لِمَنْ خَشِيَ رَبَّهُۥ ﴿٨﴾

በመሆኑም ከቸሩ ጌታቸው ዘንድ የተዘጋጀው ምንዳቸው ቋሚ መኖሪያ የሆኑት ጀነቶች ናቸው:: በአትክልቶቻቸውም ሥር የተለያዩ ጅረቶች የሚጎርፉባቸው ናቸው:: እነርሱም በዚያች ውብ አገራቸው በተሟላው ዕድላቸው ዘላለም ነዋሪዎች ናቸው:: አላህ ጌታቸው እነርሱ ያደረጉትን ወደደላቸው:: እነርሱም ከእርሱ በሚቸራቸው ወረታ ይረካሉ ደስ ብሏቸው:: (ቸሩ አላህ ያድርገንና እኛንም ከአባሎቻቸው) ይህንም የሚታደለው ከወዲሁ ጌታውን የፈራው ሰው ነው በላቸው::

ሱረቱ-ዘልዘላ سورة الزلزلة

የከባዱ ነውጥ ምዕራፍ በመዲና የወረደች፣ ስምንት አንቀጾች የያዘች አጭር ምዕራፍ ናት። እሷም በቂያማ መባቻ በምድር ላይ የሚከሰትን ከባድ መናወጥ በሚገባ ትገልጻለች። ከዚያም በመገለባበጥ በሆዷ ያለውን ሁሉ አውጥታ ትጥለዋለች። ከዚያም በጌታዋ ፈቃድ ሰዎች የሰሩትን ሁሉ በመንገር ታጋልጣለች። ከዚያም ነዋሪዎቿ ሁሉ የሥራ ውጤታቸውን ሊያዩና ሊያስተውሉ በተለያየው አቅጣጫ ወደተመደበው ቦታ ይመለሳሉ ትላለች።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

إِذَا زُلْزِلَتِ ٱلْأَرْضُ زِلْزَالَهَا ﴿١﴾

ምድር (ከስራችሁ አይታችሁ የማታውቁትን) ከባድ መናወጥ ስትናወጥባችሁ፤

وَأَخْرَجَتِ ٱلْأَرْضُ أَثْقَالَهَا ﴿٢﴾

ምድርም ያለ ልማዷ የውስጧን ሸክም አውጥታ ስታሰጣው፣ በየፊታችሁ (ማለት አስከሬኖችና ማዕድናትን ስትተፋላችሁ)፤

وَقَالَ ٱلْإِنسَٰنُ مَا لَهَا ﴿٣﴾

እናንተም ሰዎች በክስተቱ ተደናግጣችሁ፣ ስትጠይቁ ምድር ምን ሆነች? እያላችሁ፤

يَوْمَئِذٍ تُحَدِّثُ أَخْبَارَهَا ﴿٤﴾

ያኔ ነው እሷ እራሷ ዜናዎቿን በሚገባ አብራርታ የምትነግራችሁ በላቸው::

بِأَنَّ رَبَّكَ أَوْحَىٰ لَهَا ﴿٥﴾

ጌታህ በእርግጥ ልዩ ትዕዛዙን ስለሰጣት ጉዳዩን በአንደበቷ አብራርታ እንድትገልጽላችሁ::

يَوْمَئِذٍ يَصْدُرُ ٱلنَّاسُ أَشْتَاتًا لِّيُرَوْا۟ أَعْمَٰلَهُمْ ﴿٦﴾

በዚያ ቀን ሰዎች (እንዳበቃ ምርመራቸው)፣ ሥራዎቻቸውን ሊያዩ ምን እንደሚሆን ውጤታቸው፣ ተለያይተው ይመለሳሉ (ወደ ዛላለም መኖሪያቸው) ከፊሉ ወደ ጀሀነም ሌሎች ወደ ጀነት ናቸው::

فَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَهُۥ ﴿٧﴾ وَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُۥ ﴿٨﴾

ስለዚህ ዛሬ የብናኝ ክብደት ያህል እንኳን መልካም የሠራው፣ ማንም ሰው ውጤቱን እዚያ እንደሚያየው ነው:: የብናኝ ክብደትም ያህል መጥፎ የሠራው፣ እርሱም ውጤቱን እንደዚያው ያየዋል እዚያው በላቸው::

ሱረቱል-ዓዲያት سورة العاديات

የናጣጭ ፈረሶች ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ አንድ አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም በአላህ መንገድ ላይ የሚታገሉ ወዳጆቹን ሰንጋ ፈረሶች በማድነቅ ትጀምራለች:: በማያያዝም ሰው ሲባል የጌታን ፀጋ ሽምጥጦ የሚክድ፣ ገንዘብንም አጥብቆ የሚወድ መሆኑን ትነግረናለች:: ከዚያም የሰው ልጅ ለመጭው ዓለም መዘጋጀት እንዳለበት ትጠቁማለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَٱلْعَٰدِيَٰتِ ضَبْحًا ﴿١﴾ فَٱلْمُورِيَٰتِ قَدْحًا ﴿٢﴾ فَٱلْمُغِيرَٰتِ صُبْحًا ﴿٣﴾ فَأَثَرْنَ بِهِۦ نَقْعًا ﴿٤﴾ فَوَسَطْنَ بِهِۦ جَمْعًا ﴿٥﴾

ኃይለኛ ድምፅ እያፏሩ፣ በመናጠጥ የሚበሩ፣ ድንጋይንም በኮቴያቸው እያፋጩ ቃንቄ የሚያስፈነጥሩ፣ ጠላትን በፍጥነት ከበው ገና በማለዳው የሚወሩ፣ አቧራንም በኮቴያቸው እየመነሹ የሚዘሩ፣ በጠላት መሃል ላይ ገብተው ኃይሉን የሚሰባብሩ በሆኑት ፈረሶቻችሁ እየማልኩ ነው የምነገግራችሁ፣ ከሞት መነሳትና መመንዳታችሁ እንደማይቀርላችሁ::

إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لِرَبِّهِۦ لَكَنُودٌ ﴿٦﴾ وَإِنَّهُۥ عَلَىٰ ذَٰلِكَ لَشَهِيدٌ ﴿٧﴾

ሰው ሲባል እኮ የጌታውን ውለታ እጅግ የሚክድ የለየለት ወስላታ ይሉኝታ ቢስ ነው:: በዚህም ላይ እሱ ራሱ መስካሪ ነው:: (ስለዚህም ነው መልካሙን እየረሳ መጥፎውን እያወሳ ጌታውን የሚኮንነው::)

وَإِنَّهُۥ لِحُبِّ ٱلْخَيْرِ لَشَدِيدٌ ﴿٨﴾ ۞

እርሱም ደግሞ ገንዘብን የሚወደው በጠና ነው:: (ይህም የሚጠቁመው ዓላማውን መዘንጋቱን ነው:: መንፈሱን ረስቶ ትቶ የሚጨነቀው ለአካል ብቻ ነው ማለቱ ነው::)

أَفَلَا يَعْلَمُ إِذَا بُعْثِرَ مَا فِى ٱلْقُبُورِ ﴿٩﴾ وَحُصِّلَ مَا فِى ٱلصُّدُورِ ﴿١٠﴾ إِنَّ رَبَّهُم بِهِمْ يَوْمَئِذٍ لَّخَبِيرٌۢ ﴿١١﴾

ታዲያ ይህ ተላላ ሰው እንደዚህ የሚሆነው በመቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ተገልብጠው ሲወጡ፣ በደረቶች ውስጥ የነበሩትም ሚስጥሮች ይፋ ሆነው በአደባባይ

ሲመጡ፣ ያኔ ምን እንደሚያጋጥመው የማያውቅ ነው? በእርግጥ ጌታቸው በዚያ ቀን በእነርሱ ጉዳይ ጥልቅ አዋቂ ነው::

ሱረቱል-ቃሪዓ سورة القارعة

የቆርቋሪዋ ዕለት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አስራ አንድ አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም ስለትንሳኤ ቀንና ስለመዘዟ ታስገነዝበናለች:: ሰዎች ያን ጊዜ ሚዛናቸው ከሞላላቸው ወደ አስደሳቿ ጀነት የሚጋበዙ ናቸው:: በአንፃሩ ደግሞ ሚዛን የቀለለባቸው፣ የሲዖል አዘቅት ትሆናለች መኖሪያቸው:: በማለት ነው የምታስጠነቅቃቸው::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

ٱلْقَارِعَةُ ﴿١﴾ مَا ٱلْقَارِعَةُ ﴿٢﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا ٱلْقَارِعَةُ ﴿٣﴾

ቆርቋሪዋ ዕለት ምንኛ ከባድ የሆነች ቆርቋሪ ናት! ያች ቆርቋሪ ምን እንደሆነች አንተስ ምን አሳወቀህ? ገና ስላልገለጽናት (በከባድ ድንጋጤ የሰዎችን ጭንቅላት የምትመታው ቀን እኮ ናት::

يَوْمَ يَكُونُ ٱلنَّاسُ كَٱلْفَرَاشِ ٱلْمَبْثُوثِ ﴿٤﴾ وَتَكُونُ ٱلْجِبَالُ كَٱلْعِهْنِ ٱلْمَنفُوشِ ﴿٥﴾

እሷም ዕውን የምትሆነው ሰዎች ከመቃብር ወጥተው በመደናገጥ ግራ ተጋብተው በተለያየ አቅጣጫ የሚተራመሰውን የቢራቢሮ መንጋ በሚመስሉበት ቀን እኮ ነው:: ተራራዎችም የተነደፈ ፀጉር በመምሰል አየር ላይ በነው በሚጠፉበት ዕለት ነው:: (ይህም ምሳሌያዊ

አባባል የሚጠቀመው የዚያን ቀን ክብደት እንኳን ደካማው የሰው ልጅ ሊቋቋመው ጋራ ተራራም ሊመከተው የማይችል ነው ማለትን ነው::)

فَأَمَّا مَن ثَقُلَتْ مَوَٰزِينُهُۥ ﴿٦﴾ فَهُوَ فِى عِيشَةٍ رَّاضِيَةٍ ﴿٧﴾

ያማ! መልካም ሥራዎቹ በርክተውለት ሚዛኖቹ የከበዱለት፣ እጅግ አስደሳች በሆነችው ጀነት ውስጥ ነው የእርሱ መኖሪያው በዕውነት::

وَأَمَّا مَنْ خَفَّتْ مَوَٰزِينُهُۥ ﴿٨﴾ فَأُمُّهُۥ هَاوِيَةٌ ﴿٩﴾

ያማ! ደግሞ ወንጀሉቹ በዝተውበት ሚዛኖቹ የቀለሉበት የእርሱ መጠጊያ የምትሆነው፣ አዘቅቷ ጥልቅ የሆነው ሐውያ የምትባለው የሲያል ጉድጓድ እኮ ነው::

وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا هِيَهْ ﴿١٠﴾ نَارٌ حَامِيَةٌۢ ﴿١١﴾

ታዲያ የእሷን ምንነት ምንድን ነው የሚያሳውቅህ? (እኛው እንደዚህ በራዕይ ካልገለጽንልህ) እሷኮ እጅግ የተጋጋመች ጭራሽ መብረጃ የሌላት ከባድ እሳት ናት:: የክብደቷንም መጠን ነብዩ እንደገለጹት በማብራሪያቸው፣ ይህች አሁን እዚህ የምትጠቀሙባትኮ እሳት ከዚህች አንፃር ከሰባ አንድ ብቻ ናት ማለታቸው በቂ ነው ለሚገባቸው::

ሱረቱ-ተካሡር سورة التكاثر

የመበዛዣዋ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ስምንት አንቀጾች የያዘች አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷ ደግሞ እጅግ የምታስምረው ግብዝ ተላላ የሆነው ሰው ዘላቂ ዕድሉን ችላ ብሎ የጊዜያዊውን ጥቅማ ጥቅሞች እኔ ብዙ ሰብስቤያለሁ እያለ የሚደነፋ ጉረኛ ነው ትላለች:: ከዚያም በቂ ስንቅ ሳይዝ ወደዛችኛይቱ አገር ቶሎ በልና ተሻገር የሚል ጥሪ የሚደርሰው ነው:: ስለዚህ ፀፀት ላይ ሳይወድቅ ማረሚያው እህን ጊዜ ነው እንደምትል

ነው። ይህን ያልተረዱት ደግሞ ሲያልን እንደሚያዩዋት ነው። ከዚያም የሰው ልጅ ያኔ ነው ዛሬ ከባከነው ፀጋ ተጠያቂ የሚሆነው።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

أَلْهَىٰكُمُ ٱلتَّكَاثُرُ ﴿١﴾ حَتَّىٰ زُرْتُمُ ٱلْمَقَابِرَ ﴿٢﴾

እናንተ ሰዎች!. አያችሁ? እንዳትገዙ ለጌታችሁ፣ በገንዘብና በልጆች በወገንም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያላችሁ፣ መፎካከሩ ከቁም ነገሩ አዘናጋችሁ። ደግሞኮ የሚያሳዝነው ይህ ስህተት የሚቀጥለው ዕድሜያችሁ አልቆ በሞት ተሰናብታችሁ መቃብሮችን እስከምትጎበኙ ነው።

كَلَّا سَوْفَ تَعْلَمُونَ ﴿٣﴾ ثُمَّ كَلَّا سَوْفَ تَعْلَمُونَ ﴿٤﴾

ይልቅ ተው ታረሙ! ይህ ነገር የማይበጅ ነው። እምቢም ካላችሁ ውጤቱን ቆያይታችሁ ታውቁታላችሁ። አሁንም ተው! ይህ ነገር ይቅርባችሁ (የማትሰሙ ከሆናችሁ)! ውጤቱን ሰነባብታችሁ ታውቁታላችሁ።

كَلَّا لَوْ تَعْلَمُونَ عِلْمَ ٱلْيَقِينِ ﴿٥﴾

አሁንም ተው! መዘናጋቱ ይቅርባችሁ። የዚህን ውጤት የምታውቁ ብትሆኑኮ እርግጠኞች ሆናችሁ (ጊዜያዊው ቁሳቁሳችሁ አይችልም ነበር ከዘላለሚ ዕድላችሁ ሊያታልላችሁ።)

لَتَرَوُنَّ ٱلْجَحِيمَ ﴿٦﴾ ثُمَّ لَتَرَوُنَّهَا عَيْنَ ٱلْيَقِينِ ﴿٧﴾

ይህ ማስጠንቀቂያ ሲደርሳችሁ አንቀበልም እምቢ ካላችሁ፣ ወላሂ በእርግጥ ጋማዋን እሳት ታዩዋታላችሁ። አሁንም በድጋሚ የማረጋግጥላችሁ

እሷን በእርግጥ በዓይን ፍሬዎቻችሁ ትመለከቷታላችሁ::

ثُمَّ لَتُسْـَٔلُنَّ يَوْمَئِذٍ عَنِ ٱلنَّعِيمِ ﴿٨﴾

ከዚያም በዚያ ቀን ካታለላችሁ ፀጋችሁ፣ ወላሂ በእርግጥ የምትጠየቁ ናችሁ በላቸው:: (እዚህ ላይ ቲርሚዚይ በዘገቡት ሐዲስ ዓብደላህ ኢብኑ ሺኺር እንዳወሩት አንድ ቀን ነብዩ ዘንድ ስሄድ ልዘይራቸው፣ ይችን ምዕራፍ እያነበቡ አገኘኋቸው:: ከዚያም አንቀጾቿን በማስተዋል «የአደም ልጅኮ ሁል ጊዜ ገንዘቤ! ገንዘቤ! ይላል:: ለመሆኑ ከገንዘቡ እስካሁን በልቶ የጨረሰው፣ ወይም ለብሶ ያበሰበሰው፣ ወይም መፅውቶ በታ ያስያዘው ቢሆን እንጂ ሌላ አለውን? ከዚያማ ሌላ ያለው እኮ ለሌሎች ትቶት የሚሄደው ነው::» ብለው ሲተቹ ሰማኋቸው)

ሱረቱል-ዓስር سورة العصر

የዘመን ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሦስት አንቀጾች ብቻ ያሏት በጣም አጭር ምዕራፍ ናት:: ይሁንና ለኢስላም መሠረት የሆኑን ዓበይት ነጥቦች አካታ ትገኛለች:: በመሆኑም ለማንም ሰው ኪሳራና ውጤታማነት መለኪያ ትሆናለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَٱلْعَصْرِ ﴿١﴾ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لَفِى خُسْرٍ ﴿٢﴾ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟

ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلْحَقِّ وَتَوَاصَوْا۟ بِٱلصَّبْرِ ﴿٣﴾

በዘመኑ እምላለሁ፤ ሰው ሲባል በከባድ ኪሳራ ውስጥ እንደሆነ በዕማኝነት አረጋግጥላችኋለሁ:: ዳሩ ግን ከዚያ ኪሳራ የመዳን ዕድል ያላቸው እነዚያ ያመኑትና መልካም የሆኑን ተግባራት የሠሩት፣ በህይወታቸው በሐቁም መንገድ ለመጓዝ አደራ የሚባባሉት፣ እርስ በርሳቸው ችግርም ሲያጋጥማቸው በትዕግስት ለመወጣት አይዞህ በርታ የሚባባሉት ብቻ ናቸው:: (እነዚህ አራት ነጥቦች ጥቂት ቢሆኑም በቃላቸው በመልዕክታቸው ኢስላምን ሙሉ በሙሉ የሚወክሉ ናቸው::

ለምሳሌ «ያመኑት» የሚለው ቃል በአላህና በመላዕክቱ፣ በነብያትና በመጽሐፍትም፣ በመጨረሻው ቀንና በቀደርም፣ ከእነሱም ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ መቀበልን ያካትታል:: «መልካም የሆኑ ተግባራትን የሠሩ» የሚለው ደግሞ አምስቱን የኢስላም መሠረተ ነጥቦችና ኢሕሳንንም ይጠቁማል:: ከእነሱም ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ተግባራት ሁሉ ይጨምራል:: በውስጠ ሃሳቡ ደግሞ የእነሱን ተቃራኒዎች ማለትም ወንጀሎችን መራቅንም ያመለክታል:: «በሐቁ መንገድ ለመጓዝ አደራ የሚባባሉት» የሚለውም መማር፣ ማስተማር፣ ማስታወስና መገሰፅ፣ በአጠቃላይም ሰዎችን በመልካም ተግባር ማስተባበርን ያጠቃልላል:: «ችግርም ሲያጋጥማቸው በትዕግስት ለመወጣት አይዞህ! በርታ! የሚባባሉት ናቸው::» የሚለው ደግሞ ምንጊዜም ሰዎች በሐቅ ሲተባበሩ፣ በአንፃሩም ደግሞ የሐቅ ጠላቶች ስለሚኖሩ፣ በዕውነት ጓዶች ላይ ችግርን ስለሚፈጥሩ፣ ዓላማቸው ሊሰምር አይችልም አንዱ ሌላውን በማፅናናት ካልተመካከሩና እርስ በርሳቸው በመደጋገፍ «አይዞህ! አይዞህ!» በመባባል ካልተባበሩ:: «ትዕግስት» ደግሞ የሚገለጸው የታዘዙትን ተግቶ በመሥራት፣ የተከለከሉትን ቆርጦ በመተው፣ አስደንጋጭ ሰቅጣጭ የሆነም ችግር ሲከሰት እራሱን በመግዛትና በመዳኘት ነው::)

የሀሜተኞች ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ዘጠኝ አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም ስለሀሜተኞችና በሰው አሿፊ ቀላጆች፣ ገንዘብ አከማቾችና ምፅዋትን ከልካይ ንፉጎች የሆኑትን በማውሳት ትገስፃለች:: ፍፃሜያቸውም ምን እንደሚሆን በማስጠንቀቅ ወየውላቸው ጥፋታቸው እያለች ትገስጻለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

وَيْلٌ لِّكُلِّ هُمَزَةٍ لُّمَزَةٍ ﴿١﴾ ٱلَّذِى جَمَعَ مَالًا وَعَدَّدَهُۥ ﴿٢﴾

يَحْسَبُ أَنَّ مَالَهُۥٓ أَخْلَدَهُۥ ﴿٣﴾

ሀሜተኛና አሽሟጣኝ ሰው አነዋሪ የሆነው ሁሉ (በትችቱ) ወየውለት! ወይ ጥፋቱ! (በዓይን ጥቅሻ በከንፈር ንክሻ ሰውን የሚለክፍ የሆነው ሁሉ በየዕለቱ፣) ያ! ገንዘቡን ሰብስቦ እየቆጠረ ማካበቱ ዘላለም ያኖረው የሚመስለው ሃብቱ መብዛቱ፣ ከእነዚህ ስህተቶች ቀፀፆ ካልተመለሰ በወቅቱ፣ አሳር ነውኮ የሚጠብቀው ወይ ጥፋቱ::

كَلَّا ۖ لَيُنۢبَذَنَّ فِى ٱلْحُطَمَةِ ﴿٤﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا ٱلْحُطَمَةُ ﴿٥﴾

ይልቅ ይህ ሰው እህን ጊዜ ይህን መጥፎ ባህሪ ይተው! አለበለዚያ ወላሂ በሑጠማ ውስጥ እንደሚወረወር ነው:: ሑጠማስ ምን እንደሆነች እኛ ካልነገርንህ በቀር የሚያሳውቅህ ምንድን ነው?

نَارُ ٱللَّهِ ٱلْمُوقَدَةُ ﴿٦﴾ ٱلَّتِى تَطَّلِعُ عَلَى ٱلْأَفْـِٔدَةِ ﴿٧﴾ إِنَّهَا عَلَيْهِم مُّؤْصَدَةٌ ﴿٨﴾

فِى عَمَدٍ مُّمَدَّدَةٍۭ ﴿٩﴾

እሷኮ ከነደደች ምንም መብረጃ የሌላት፣ አንድ ጊዜ አድቅቃ የምትጥል ልዩ የአላህ እሳት ናት:: ያችም እሳት በቀጥታ በልቦች ውስጥ የምትዘልቅ ናት:: እሷም በእርግጥ በእነርሱ ላይ በረጃጅም አጉራዎች ተሸንጉራ የምትዘጋ አስከፊ እሳት ናት በላቸው::

ሱረቱል-ፊል سورة الفيل

የዝሆን ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አምስት አንቀጾች ብቻ ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: አል-ፊል ነቢዩ በተወለዱበት ዓመት መጀመሪያ ላይ ካዕባን ለመናድ ዘምቶ በመጣው የአብረሃ ጦር ላይ የወረደበትን መዓት ትገልጻለች:: (ይህም ተዓምር የተከሰተው በአምስት መቶ ሰባ ዓመተ-ልደት ላይ ነው:: እርምጃውም የተወሰደው ታይተው ተሰምተው የማያውቁ አዕዋፋት ባዘነቧቸው መርዛማ ጠጠሮች ነው::)

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

أَلَمْ تَرَ كَيْفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِأَصْحَٰبِ ٱلْفِيلِ ﴿١﴾ أَلَمْ يَجْعَلْ كَيْدَهُمْ

فِى تَضْلِيلٍ ﴿٢﴾

(ኃያሉ አላህ ካዕባን ሊያፈርሱ በመጡት ወራሪዎች ላይ የወሰደውን እርምጃ ለነብዩ ሲገልጽላቸው):- ጌታህ የዝሆኑን ባልደረቦች እንዴት እንዳደረጋቸው አላወቅክም? አላቸው:: ተንኮላቸውን በከንቱ አይደለምን አምክኖ ያስቀረባቸው?

وَأَرْسَلَ عَلَيْهِمْ طَيْرًا أَبَابِيلَ ﴿٣﴾ تَرْمِيهِم بِحِجَارَةٍ مِّن سِجِّيلٍ ﴿٤﴾

فَجَعَلَهُمْ كَعَصْفٍ مَّأْكُولٍ ﴿٥﴾

በእነርሱም ላይ ከተጠበሰ ጭቃ የተዘጋጁን ድንጋዮች የሚያወርዱ የወፍ መንጋዎች ላከባቸው:: ከዚያም ወዲያው በድቀታቸው ከብቶች የሰነቱበት የአገዳ ቁረን አስመሰላቸው:: (ማለትም እንዳልነበሩ ሰባብሮ አመሰቃቅሉ ጣላቸው:: (እዚህ ላይ የተፍሲር ሊቆች እንደገለጹት በማብራሪያቸው፣ በዚያ ወቅት የመን አገርን ሲገዛ የነበረው ኢትዮጵያዊው አንባገነኑ አብረሃ ዓረቦቹ ካዓባን በአክብሮት ሲጎበኙ ሲያያቸው፣ ቅናት ተሰማውና በአድራጎታቸው፣ ሰንዓ ላይ ውብ የሆነች ቤተ-ክርስቲያን ገንብቶ እሷን እንዲጎበኙ ሲያቅድላቸው፣ የካዕባ አፍቃሪ የነበረው ኪናናዊ ግለሰብ በሌሊት መጥቶ መቅደሷን በኩሱ ቀብቶ ሲያረክስባቸው፣ ያኔ አንባገነኑ አብረሃ «ይህን ያደረጉት መኮች ናቸው» አለና ቆርጦ ተነሳ ሊበቀላቸው:: በዝሆን ኃይል የሚመራ ብዙ ሺህ ጦር አስከትሉ ወደ መካ ፈጥኖ አመራ እያቅራራ:: ያኔ አንዳንድ የዓረብ ጥቃቅን ብሔረሰቦች በየመንገዱ ግዙፉን ወራሪ ጦር ሊያደናቅፉም ቢወጡ፣ በቀላሉ መገደል መማረክ እንጂ ምንም ውጤት አላመጡ:: መኮችም ያንን ከባድ ጦር መቋቋም እንደማይችሉ ተስፋ ሲቆርጡ፣ ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ ተራራዎች ወጡ:: ደግነቱ ወዲያውኑ ያልተጠበቁት የአላህ ኃይሎች ጥቃቅን ድንጋዮች ይዘው አየሩን ሸፍነው መጡ:: ከዚያም ፍልሚያው ተጀመረ፣ አዲሱም ልዩ መሳሪያ በእነአብረሃ ሰራዊት ላይ ተነጣጥሮ ተሞከረ:: ያኔ እንኳን ሊቋቋሙት ለማምለጥ ማሰቡም ቀረ:: ከትንሽ ጊዜም በኋላ ቆሞ መሄድም ቸገረ:: መርዛማው የወፎች ድንጋይም ሰውን ዝሆኑን በጣጥሶ መሬት ላይ ማረፍ ጀመረ:: ዝሆኑ እስከ ሰራዊቱ ተልዕኮውን ሳይወጣ ኬላ ላይ ረግፎ ቀረ::

ሱረቱ ቁረይሽ سورة قريش

የቁረይሽ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አራት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም በዚያ ወቅት አላህ ለመካ ህዝቦች የቸራቸውን ፀጥታና ብልፅግና እያስታወሰች፣ እነርሱም ደግሞ በአፀፋው እርሱን ብቻ እንዲያመልኩና በፈቃዱ እንዲመሩ ትጠይቃለች::

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም
(እንጀምራለን::)

لِإِيلَافِ قُرَيْشٍ ﴿١﴾ إِيلَافِهِمْ رِحْلَةَ الشِّتَاءِ وَالصَّيْفِ ﴿٢﴾

ቁረይሾችን ጌታቸው በተለመደው ባህላዊ ክብራቸው እንዲቀጥሉ ስላስቻላቸው፤ የብርድና የሙቀትንም ወራት ንግዳዊ እንቅስቃሴ እንደለመዱ ይቀጥሉ ዘንድ ይበልጥ ስላመቻቸላቸው (ማለትም በብርድ ወራት ወደ የመን በሙቀት ጊዜ ወደ ሶሪያ የሚያደርጉትን ንግዳዊ እንቅስቃሴ ማንም እንዳይገታባቸው ስላደረገላቸው):-

فَلْيَعْبُدُوا رَبَّ هَٰذَا الْبَيْتِ ﴿٣﴾ الَّذِي أَطْعَمَهُم مِّن جُوعٍ

وَآمَنَهُم مِّنْ خَوْفٍ ﴿٤﴾

ሌላው ቢቀር ስለዚህ እንኳ ስጦታ የዚህን ታሪካዊ ቤት የካዕባን ጌታ ብቸኛ አድርገው መገዛት አለባቸው:: እርሱ እኮ ነው ረሃብ እንዳያጠቃቸው የመገባቸው፣ ፀጥታውንም በማስፈን ከፍርሃት ያረጋጋቸው በማለት ሐቀኛው ፈጣሪያቸው ጣዖቶቻቸውን ጥለው እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ ጠየቃቸው:: በተለይ እነአብረሃን በማድቀቅ ይበልጥ ክብር ስለጨመረላቸው፤ ሆኖም ለዚህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ መስጠት ባለመቻላቸው ዱላው ለእነርሱም ደረሳቸው::

ሱረቱል-ማዑን سورة الماعون

የቁሳቁስ ትውስት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሰባት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም በአጭሩ ስለሁለት መጥፎ ቡድኖች ትገልጻለች (ማለትም ስለከሃዲያንና ስለይዩልኝ ባዮች አስመሳዮች::)

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

أَرَءَيْتَ ٱلَّذِى يُكَذِّبُ بِٱلدِّينِ ﴿١﴾ فَذَٰلِكَ ٱلَّذِى يَدُعُّ ٱلْيَتِيمَ ﴿٢﴾ وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلْمِسْكِينِ ﴿٣﴾

አላህ ለነብዩ (ዐለይሂ ሶላቱ ወሰላም) ስለጠላታቸው መጥፎ ባህሪያት ሲገልጽላቸው ያንን ከባድ የምርመራ ቀን የሚያስተባብለውን ወስላታ ሰው አየኸውን? አላቸው:: እሱ ያ! ድሃ አደጉን የሙት ልጅ በጭካኔ የሚገፈትር ምስኪንንም በመመገብ ላይ የማያግባባ የሆነው ስብዓዊ ርህራሄ እንኳ የሌው መናጢ ነው:: (እርሱም የተፍሲር ሰዎች በማብራሪያቸው እንደገለጹት ዓስ ኢብኑ ዋኢል ወይም ነድር ኢብኑል ሓሪስ የተባለው ግለሰብ ነው::)

فَوَيْلٌ لِّلْمُصَلِّينَ ﴿٤﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ عَن صَلَاتِهِمْ سَاهُونَ ﴿٥﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ يُرَآءُونَ ﴿٦﴾ وَيَمْنَعُونَ ٱلْمَاعُونَ ﴿٧﴾

እነዚያ ደግሞ ከስግደታቸው የሚዘነጉ የሆኑት ሰጋጅ ነን ባዮች ወየውላቸው:: እነርሱኮ በሥራቸው አስመሳዮች የሆኑ ይዩልኝ ባዮች ናቸው:: ጥቃቅን

ዕቃዎች እንኳ ሰዎች ለትውስት ሲጠይቋቸው የሚከለክሉ ጨካኞች ናቸው። (ለሌሎች የማያስቡ ራስን ብቻ ወዳጆች በመሆናቸው።)

ሱረቱል-ከውሠር سورة الكوثر

የልዩ ጅረት ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ሦስት አንቀጾች ብቻ ያሏት እጅግ አጭር ምዕራፍ ናት። እሷም አላህ ለነብዩ የለገሰውን በርካታ ስጦታና ልዩ የሆነውን የከውሰር ጅረት ታወሳለች።

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

إِنَّا أَعْطَيْنَاكَ الْكَوْثَرَ ﴿١﴾ فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَانْحَرْ ﴿٢﴾ إِنَّ

شَانِئَكَ هُوَ الْأَبْتَرُ ﴿٣﴾

[(እጅግ ቸሩ አላህ ለመልዕክተኛው (ዓለይሂ-ሶላቱ ወሰላም) ዋቢነቱን ለማረጋገጥ ምቀኞች ጠላቶቻቸው በተናገሩት ትችት ላይ መልስ ሲሰጥላቸው:-] እኛኮ በእርግጥ በርካታ ዕድልን ቸረንሀል። በተለይም ሐውድ የተሰኘውን ልዩ ጅረት አድለንሃል አላቸው። ግድ የለም እነርሱ ለጊዜው ይዘባርቁማ ተዋቸው! ብቻ አንተ ለጌታህ ስገድ። ምፅዋትንም ለእርሱ ብቻ እረድ። አንተንኮ የሚጠላህ ሰው (በእርግጥ ዕድለ ቆራጣ ነው) አላቸው። [ይህንም ያለው ነብዩ (ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም) ቃሲም የተባለው ልጃቸው ሲሞትባቸው ጠላቶቻቸው ደስታ ተሰምቷቸው፣ በተለይ ዐሲና ወሊድ ነድርም አብሯቸው ሌሎቹን ሲያበስሯቸው፣ «ከእንግዲህ ወዲያ ስለ ሙሐመድ አታስቡ። ዘሩ ተቆርጧልና ከሞተ ወዲያ ብዙ ሳይቆይ የሚረሳ ነው።» ስላሉ ነው ጌታቸው ይህን ዓይነት መልስ የሰጠላቸው። ሐውድ ማለት አላህ

ለነብዩና ለሐቀኞቹ የሱና ሰዎች የደገሰው ታላቅ ጅረት ነው:: መልኩ ከወተት የነጣ ጣዕሙም ከማር የላቀ ነው:: የኩባያዎቹም ብዛት ልክ እንደ ሰማይ ኮኮብ ነው:: የሚጎርፈውም በንፁህ ወርቅ ወንዝ ላይ ነው:: ሽታው ደግሞ ልክ እንደ ምርጡ ሚስክ ነው:: ይህም ማብራሪያ በትክክለኛው ሐዲስ የተረጋገጠ ነው::]

ሱረቱል-ካፊሩን سورة الكافرون

የከሃዲያን ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ስድስት አንቀጾች ብቻ ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም ነብዩን በጥብቅ የምታስጠነቅቀው መርዛማውን የከሃዲያን ጥያቄ እንዳይቀበሉ ነው::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

قُلْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿١﴾ لَآ أَعْبُدُ مَا تَعْبُدُونَ ﴿٢﴾ وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٣﴾

እናንተ ከሃዲያን ሆይ! እናንተ የምትግገዙትን ነገር እኔ ጭራሽ አልግገዛውም በላቸው:: እኔ የማመልከውንም አላህ (እናንተ በእርሱ አጋሪዎች እስከሆናችሁ በዚህ አስተሳሰባችሁ) እንደተፈለገባችሁ ልትግገዙት የማትችሉ ናችሁ:: (ብታደርጉትም አይቆጠርላችሁ) አጋሪዎች በመሆናችሁ በላቸው::

وَلَآ أَنَا۠ عَابِدٌ مَّا عَبَدتُّمْ ﴿٤﴾ وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٥﴾ لَكُمْ دِينُكُمْ وَلِىَ دِينِ ﴿٦﴾

(አሁንም በድጋሚ የምለው) ለወደፊትም እናንተ የምትግገዙትን የሀሰት አምላክ እኔ በምንም እንደማልግገዛው ነው:: እናንተም እኔ የማመልከውን አላህ (በምትሉት መልክ) ልትግገዙት እንደማትችሉ ነው:: ስለዚህ ኃይማኖታችሁ ለእናንተው ብቻ ነውላችሁ:: ለእኔም ኃይማኖቴ አለኝ:: እውነት ከሀሰት መዋሐድ አያስፈልግም በላቸው:: (ይህንም ያለው ሚስጥር አዋቂው ጌታቸው ጣዖታውያን ነብዩን በድርድር ሊያታልሏቸው «ሙሐመድ ሆይ! አንተ ከእኛ ጋር ሁንና ለአንድ ዓመት ያህል ጣዖቶቹን ተሳለማቸው:: እኛም ደግሞ በቀጣዩ ዓመት አንተ ጋር ሆነን እንስግዳለን:: በተጨማሪም አንተ የምትሻውን ሁሉ እናሟላለን:: ለምሳሌ ሥልጣን ከፈለግክ ልናነግስህ እንችላለን:: ገንዘብም ከሻህ ከሁሉም በላይ ሃብታም እናደርግሃለን:: ሴትም ካማረህ የመረጥካትን ቆንጆ ልጅ እንድርሃለን::» ሲሏቸው አላህ ይህን መመሪያ አወረደና ቁርጡን እንዲያውቁት አደረጋቸው::)

ሱረቱ-ነስር سورة النصر

የድል ምዕራፍ በመዲና በነብዩ ዕድሜ መጨረሻ ላይ የወረደች፣ ሦስት አንቀጾች ብቻ ያሏት በጣም አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷ ደግሞ አበክራ ስለመካ መከፈትና ስለታላቁ ኢስላማዊ ድል ትንቢት ትናገራለች:: በዚያም ጊዜ የሰው ልጆች በገፍ ወደ አላህ ኃይማኖት ይገባሉ ትላለች:: እንዳለችውም ትንብዩ በመፈፀሙ የነብዩን ሐቀኝነት ልታረጋግጥ ችላለች:: በተጓዳኝም ዕድሜያቸው መገባደዱን ጠቁማለች::

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም
(እንጀምራለን::)

إِذَا جَآءَ نَصۡرُ ٱللَّهِ وَٱلۡفَتۡحُ ۝١ وَرَأَيۡتَ ٱلنَّاسَ يَدۡخُلُونَ فِي دِينِ ٱللَّهِ أَفۡوَاجٗا ۝٢ فَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ وَٱسۡتَغۡفِرۡهُۚ إِنَّهُۥ كَانَ تَوَّابَۢا ۝٣

የአላህ ዕርዳታ ሲመጣና መካ ተከፍታ (ድሉን ስታበስራቸው)፣ ሰዎችንም በጅምላ ወደ ኢስላማዊው የአላህ ኃይማኖት ሲገቡ ስታያቸው (ዓላማህ ግቡ ሊደርስ ተቃርቧልና) ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው አላቸው:: ምህረትንም ለምነው:: እርሱኮ ለአገልጋዮቹ ይቅር ባይ መላሳ ነው (ሲለምኑት እሽ ብሉ የሚሰማቸው:: በማለት ቸሩ ጌታቸው የተሟላ ድልና ዕድል እንደሚለግሳቸው ተስፋ ቃል ገባላቸው:: እንዳለውም በገቢር አረጋገጠላቸው:: ከዚያ በኋላ ነብዩ እስከ ዕለተ ህልፈታቸው «ሱብሐነከ አላሁመ ረቢ ወቢሐምዲከ አስተግፊሩከ ወአቱቡ ኢለይከ ማለት ሆን ዜማቸው::) ያኔ አቡበከር ይህን ሲሰሙ፣ አለቀሱ ስለገባቸው የነብዩ ዕድሜ መደምደሙ::

ሱረቱል-መሰድ - سورة المسد

የሹርብ ገመድ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አምስት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷ ደግሞ የአቡለሃብን ደባና አስከፊውን ውድቀቱን ትገልጻለች:: ሚስቱም እንደርሱ ተንኮለኛ ስለነበረች በብረቱ የጥፋት ገመድ መጠለፏን ታወሳለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

تَبَّتْ يَدَآ أَبِى لَهَبٍ وَتَبَّ ﴿١﴾ مَآ أَغْنَىٰ عَنْهُ مَالُهُۥ وَمَا كَسَبَ ﴿٢﴾

(ነብዩን «ዓብዱል ዑዛ» የተባለው አጎታቸው በተልዕኳቸው የከፋ እንቅፋት ሆኖ ሲያስቸግርና ጉዳዩ ሲያሳስባቸው፣ ኃያሉ ጌታ እልባት ሊሰጥላቸው):- የአቡለሃብ እጆች ይጥፉ፤ እንዲያውም እራሱ ጠፋ በማለት አበሰራቸው:: (በቅድሚያ እጆቹን የጠቀሰው ይህ አደጋ የመጣበት እጆቹ በፈፀሙት ወንጀል ሳቢያ ነው ማለትን ለመጠቆም ነው::) ከዚህም ውድቀት ድልብ ገንዘቡ፣ ጀግኖች ልጆቹ የሰበሰበውም ክብርና ዝናው አላዳነው::

سَيَصْلَىٰ نَارًا ذَاتَ لَهَبٍ ﴿٣﴾ وَٱمْرَأَتُهُۥ حَمَّالَةَ ٱلْحَطَبِ ﴿٤﴾ فِى جِيدِهَا حَبْلٌ مِّن مَّسَدٍۭ ﴿٥﴾

ቆይቶ ደግሞ በቀጣዩ ዓለም የሚጠብቀው ተንቀልቃይቷ እሳት ውስጥ ተማግዶ መርመጥመጥ ነው:: ነገር ቆስቋሽ ባለቤቱም እንጨት እንደተሸከመች አብራው እንደምትወርድ ነው:: በአንገቷ ላይም ጠንካራ ከሆነው ሹርብ ገመድ እንደሚጠለፍላት ነው:: (ይህን መሰል ሜዳለያም ያገኘችው «የአንገቴን ሃብል እስከምሸጥ ሙሐመድን ከመዋጋት ወደ ኋላ እንደማልል ነው» በማለቷ ነው:: በተጨማሪም በረሃ ሄዳ እሾካም እንጨት ሰብስባ ታመጣና ሌሊት ጨለማ በመልበስ በነብዩ መተላለፊያ ላይ በመከስከስ ለማስወጋት ትጥር ስለነበር ነው:: ይህም የሆነው ነብዩ (ዐለሂ ሶላቱ ወሰላም) ከጌታቸው «ወአንዚር ዐሺይረተከል አቅረቢይን» (አቅራቢያ ወገኖችህን አስጠንቅቃቸው) የሚለው አንቀጽ ሲወርድላቸው፣

በማለዳ ሰዓት ሰፋ ኮረብታ ላይ ወጥተው «ወገኖቼ ሆይ! ቶሎ ብሏችሁ ኑ!» በማለት ሲጠሯቸው፤ ወዲያው ተሰባስበው መጥተው ከበቡና «ምን ሆንህ ነው?» ሲሏቸው መልዕክቱን በአጭር ለማስተላለፍ በስልታዊው ዘዴያቸው «አሁን እኔ ወንድማችሁ፣ በአካባቢያችሁ የጠላት ጦር ሲከማች አየሁ ሊወራችሁ፤ ብላችሁ ታምኑኛላችሁ?» በማለት ሲጠይቋቸው ሁላቸውም «እንዴታ ከአንተ ውሸትን አናውቅምና!» አሏቸው:: «እንግዲያውስ አያችሁ! ከዚህ የባሰ ጉዳይ ነው የምነግራችሁ፤ እኔ ለእናንተ መካሪ አስጠንቃቂም ነኝ ቶሎ እንድታምኑ በጌታችሁ፤ እህን ጊዜ ብርቱ ቅጣት ሳይደርስባችሁ» ሲሏቸው አቡለሃብ ተነሳና ከመሃላቸው «አሁን ለዚህ ነው በጧቱ ያስደነገጥከን? ያጥፋህና! በማለት ሲጮህባቸው፣ ያኔ ጌታ እርጉሙን እኛ እናውቃለን፤ አቡለሃብ የእጁን ያገኛል፤ አሁን ጠፊ ነው» የሚል ውሳኔ በዚህች ምዕራፍ ላከላቸው:: እንዳለውም ወዲያው ሳይቆይ በቁርባ በሽታ ተቃጥሎ ሞተላቸው::)

ሱረቱል-ኢኽላስ سورة الإخلاص

የመለኮታዊ ፍፁምነት መግለጫ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አራት አንቀጾች ብቻ ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: ከመሆኑም ጋር ስለአላህ ምንነትና ማንነት በሚገባ ቁልጭ አድርጋ ትገልጻለች::

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ ﴿١﴾ اللَّهُ الصَّمَدُ ﴿٢﴾

(እኔ የማመልከውና እናንተም ፍፁም ሆናችሁ እንድትገዙት የምመክራችሁ) እርሱ ያ! አጋር የሌለው ፍፁም ብቸኛ የሆነው አላህ እኮ ነው:: እርሱም አላህ ለፍጡራት ሁሉ አስተማማኝ መሸሸና መጠጊያ የሆነ አምላክ ነው::

لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ﴿٣﴾ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ﴿٤﴾

እርሱም ጭራሽ ያልወለደ፣ ከማንም ያልተወለደ፣ ፍፁም ኃያል ነው:: ለእርሱም አንድም አቻ፣ ቢጤ፣ ተመሳሳይ፣ ወደረኛም የሌለው ነው በላቸው ሲል ነብዩን አዘዛቸው:: (ይህንም ያለው ከሃዲያን የተለያዩን ፅላቶች እንደ አምላክ አድርገው ሲገዟቸው፣ ነብዩ መጥተው «እነዚህ ሁሉ አላስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: ይልቅ እነሱን ተውና አላህን ብቻ አምልኩ!» ብለው ሲገስጿቸው «እኛኮ አላህን ስላላየነው ስለእሱ አናውቅምና እስኪ ምን እንደሚመስል ግለጽልን» ሲሏቸው አላህ እራሱ ይችን ምዕራፍ በማውረድ ፍፁም ብቸኛ፣ የሁሉ መጠጊያ ዳኛ፣ ወላጅ ተወላጅ ሚስትም ሆነ ወይም አምሳያ ጓደኛ የሌለው መሆኑን ገለጸላቸው:: በማያያዝም አይሁድና ክርስቲያኖችም በየፊናቸው ዑዘይርና እየሱስን የአምላክ ልጆች በማለታቸው ዐረቦቹም በበኩላቸው መላዕክትን የአላህ ሴት ልጆች በማድረጋቸው የሁላቸውም አባባል መሠረተ-ቢስ ከንቱ መሆኑን አረጋገጠላቸው::)

ሱረቱል-ፈለቅ سورة الفلق

የተፈልቃቂው ጎህ ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ አምስት አንቀጾች ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷም ሰዎች መጥፎ ነገር ሲሰማቸው በመሸሽ ወደ ጌታቸው፣ «ጠብቀን» ማለት እንዳለባቸው ታስተምራለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን።)

قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلْفَلَقِ ﴿١﴾ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ﴿٢﴾ وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ﴿٣﴾

(ነብዩ ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም ሳያውቁ በፊት ምን እንዳጋጠማቸው፣ የሃሳብ መረበሽ ሲሰማቸው ሚስጥር አዋቂው ጌታቸው) በተፈልቃቂው ወጋገን ጌታ ከፈጠረው ነገር ሁሉ ተንኮልና ጦስ እጠበቃለሁ በል አላቸው። በሌሊትም ከሚያጋጥመው አደጋ ጨለማው ከብዶ ሲመጣና ፍጥረታትን ሲሸፍናቸው።

وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِى ٱلْعُقَدِ ﴿٤﴾ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ﴿٥﴾

ሟርትን እያነበነቡ በተቋጠሩ ክሮች ላይ ከሚተፉትም ሴቶች ተንኮል አንተን ሊያጠፉ በመሻት አባታቸው እንዳዘዛቸው ከምቀኛውም ሰው ደባ አንተን ሊያጠቃ ሲያደባ ጌታዬ እባክህ አንተ ጠብቀኝ በል አላቸው። (ይህችና ቀጣይዋ ምዕራፍ የወረዱበትም ምክንያት ነብዩ ተልዕኳቸውን ሲያደርስ በትጋት ሲንቀሳቀሱ ጠላቶቻቸው ከዓላማቸው ለማደናቀፍ ሲቀለብሱ በመዛት፣ በማስፈራራት፣ በማባበልም በማግባባት፣ በማዕቀብም፣ እንዲሁም ስም በማጥፋት ቢያዋክቧቸው አልበገርም በማለታቸው፣ ለቢድ ኢብኑል አዕሶም የተባለውን ሟርተኛ በድግምት እንዲያጠፋቸው ተመሳጥረው ቀጠሩባቸው። ያኔ ሟርቱን በሰም አሻንጉሊት ላይ አቀናብሮ፣ አስራ አንድ መርፌዎችን ዙሪያውን ተክሎ፣ በክር አዋቅሮ አስተሳስሮ፣ ሴት

ልጆቹን በዚሁ ተንኮል ስላሰለጠናቸው፣ ዜማውን እያነበቡ በሰሙ ላይ «እትፍ እትፍ» እንዲሉበት አዘዛቸው:: በወጣት ሴቶች የተሠራ ሟርት አደገኛ ነውና ጭራሹን ሲያጠፋቸው፤ ከዚያም እንዳይገኝበት በተምር ቅርፊት ጠቅልሎ ዘርዋን በተሰኘች ውሃ ጉድጓድ ውስጥ ቀበረባቸው:: ያኔ ነብዩ ድካም ድካም አላቸው:: ብስጭትም ተሰማቸው:: ደግነቱ አንድ ነገር ሲያጋጥማቸው አላህ ነውና መሸሻቸው፣ ዱዓ አድርገው ጋደም እንዳሉ እቤታቸው፣ ሁለት እንግዶች መጡና አጠገባቸው፣ ቃለ-ምልልስ ጀመሩ ስለእርሳቸው:: ከግርጌ በኩል ያለው ራስጌ ላለው ጓደኛው «አሁን ይሄ ሰው ምን ሆኖ ነው እባክህ እዚህ የተኛው?» በማለት ሲጠይቀው «አሞት ነዋ!» አለው:: «ህመሙስ ምንድን ነው?» ሲለው «ሟርት ተደርጎበት::» አለው:: «ያደረገውስ ማን ነው?» ሲለው «ለቢድ ኢብኑል አዕሶም» አለው:: «ሟርቱስ የት ይገኛል?» ሲለው «ዘርዋን ምንጭ ጉድጓድ» አለው:: «ታዲያ አሁን ምን ይበጀዋል?» ሲለው «አሁንማ እነዚህን ምዕራፎች ያንብብ» አለና ሁለቱን ምዕራፎች አስተማራቸው:: ከዚያም ተነስተው እንደ ሄዱ ከአጠገባቸው፣ እርሳቸውም ተነሱና ከመኝታቸው፣ ዓኢሻ ስለነበሩ በአጠገባቸው «ይኸውልሽ ዓኢሻ! ጌታዬ እኮ ለችግሬ መፍትሄ ላከልኝ:: በሉ! አሁን ኀበዝ ሂዱና ሟርቱን ከጉድጓዱ አምጡልኝ!» በማለት ሰሓቦቹን ሲልኳቸው ወዲያው ሄደው ከጉድጓዱ በማውጣት አመጡላቸው:: ያኔ እርሳቸው አንቀጾቹን ሲያነቡባቸው፣ መርፌዎቹ ይበሩ ጀመር በመንቃቀል ከቦታቸው:: አስራ አንዱም አንቀጾች ተነበው ሲጠቃለሉ፣ አስራ አንዱም መርፌዎች ረገፉ በሙሉ:: ያኔ እርሳቸው፣ ወዲያው ተሟላ ጤንነታቸው::

በመሆኑም እነዚህ ምዕራፎች ቁል ሁወላሁ አሐድን በመጨመር ሟት ማታ ለሚያነባቸው፣ ከመጥፎ ሁሉ ይጠብቃሉ ከልብ ለሚያነባቸው በተለይ ከሟርት ተንኮል ፍቱን መድሃኒቶች ናቸው::)

ሱረቱ-ናስ سورة النــاس

የሰዎች ምዕራፍ በመካ የወረደች፣ ስድስት አንቀጾች ብቻ ያሏት አጭር ምዕራፍ ናት:: እሷ ደግሞ ከጠላት ሁሉ ከከፋው አደገኛ ጠላታችን እንድንሸሽ ወደ ጌታችን ትመክረናለች::

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እጅግ ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው አላህ ስም (እንጀምራለን::)

قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ﴿١﴾ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ﴿٢﴾ إِلَٰهِ ٱلنَّاسِ ﴿٣﴾ مِن شَرِّ ٱلْوَسْوَاسِ ٱلْخَنَّاسِ ﴿٤﴾ ٱلَّذِى يُوَسْوِسُ فِى صُدُورِ ٱلنَّاسِ ﴿٥﴾ مِنَ ٱلْجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ﴿٦﴾

ለነብዩ (አላህ ጌታቸው ከሁሉም በላይ የከፋውን ጠላታቸውን እንዴት መመከት እንዳለባቸው ሲመክራቸው):-

ሰዎችን ፈጥሮ ካልነበሩ ያስገኛቸው፣ ለሁሉም ሰዎች ፍፁም ንጉሥ የሆነላቸው፣ ለሁሉም ሰዎች ብቸኛ ሐቀኛ አምላክ በሆነው ኃያል ጌታቸው፣ ብቅ እልም እያለ በመጥፎ ጎትጓች ከሆነው ሰይጣን ደባ እጠበቃለሁ በል አላቸው:: (እሱ ነውና) በሰዎችና በጋኔኖች ደረቶች ውስጥ መጥፎ ስሜትእያሰራጨ ወደ ወንጀል በመጋበዝ የሚጎተጉታቸው፣ ለማጣላት ከጌታቸው::

إصــدار

المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالمعذر وأم الحمام تحت

إشراف وزارة الشؤون الإسلامية والأوقاف والدعوة والإرشاد

ت: ٤٨٨٤٤٩٦ — ٤٨٢٦٤٦٦ فاكس: ٤٨٢٧٤٨٩ ص ب ٣١٠٢١ الرياض ١١٤٩٧

رقم الحساب للكتب والأشرطة ٢٥١٦٠٨٠١٠١٧٧٧٧٨

شركة الراجحي المصرفية فرع أم الحمام (٢٥١)

ترجمة معاني القرآن الكريم

باللغة الأمهرية

المترجم

الشيخ : سعيد أحمد مصطفى

جزء عمّ